# 7

# ኃይል ለኃይል አገልግሎት

የኃይል አገልግሎት ለመስጠት ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት መኖር አስፈላጊ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል ብሎ ተነበየ /ማቴ. 3፡11/። የጰንጠቆስጤው እሳት የመጣበት ዋናው ምክንያት ክርስቶስ የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን እሻለሁ ብሎ የተናገረውን ለማቀጣጠልና ለማንደድ ነው /ሉቃ.12፡49/።

በመሰረቱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን ክርስቲያን ዲያቢሎስ በግልም ሆነ አገልግሎቱን ጭምር ይቃወማል። የአገልጋዩን ዝክረ ስም ከምድር ላይ ለማጥፋት የማያደርገው ጥረት የለም። ለዚህ ነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሁል ጊዜ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት። አምላካችን ደግሞ ኃይልን እንደሚሰጥ አያሌ ጊዜ ተስፋ ሰጥቷል /መዝ. 29፡11፣ ኢሳ. 40፡29/።

የኃይል ሙላት ድንገተኛ ከመሆኑም በላይ ሲመጣ ደግሞ ይታወቃል። በአገልጋዩ መንፈስ ላይም ሆነ በሰውነቱ ላይ የሚሰማው የሰው ያልሆነ ኃይል ይከሰታል። ይህ ሲሆን በአገልግሎት ሊያስችል መንፈስ ቅዱስ ቅባቱን ለቅቋል ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ኃይሉን በሚያስ ፈልጋቸው ጊዜ ይሰጣቸው ነበር። ያለነው በመንፈስ ቅዱስ ዘመን

ነው። ስለሆነም ለእኛም በውስጣችን ለዘላለም ለመኖር የመጣው ጰራቅሊጦስ ለአገልግሎት ኃይሉን ይሰጠናል ማለት ነው።

## 7.1 በመንፈሳዊ ኃይል መሞላት

በቅድሚያ "ኃይል" የሚለውን ቃል በትርጉም ወደ በለጸገው የግሪክ ቃል ሄደን ማየት ይኖርብናል። ቃሉ በግሪክ "Dunamis" (ዱናሚስ) ነው የሚለው። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግሪክ ቋንቋ በመጻፉ ምክንያት ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት ወደ ቃላት መፍቻ መሄድ በጣም አስፈላጊ ነው። ትርጉሙም ገደብ የለሽ ኃይል ማለት ሲሆን የዚህ ዓይነቱ ኃይል መለኮታዊ፣ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሁም የመላእክት ኃይል ነው።[5] የዚህ ዓይነቱ ኃይል በሰው አእምሮ የማይገመትና ተመጣጣኝ የሌለው ጉልበት ማለት ነው። ሰው የሚሠራው ኃይለኛ መሳሪያ በፈረስ ጉልበት ይለካል፣ መለኮታዊ ኃይል ግን ሚዛን አይገኝለትም። ከደማሚት፣ ከአቶሚክ ቦምብና አለ ከተባለ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰብአዊ ኃይል እጅጉን ይበልጣል።

ዘካርያስ "*በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር*" ብሎ ይናገራል (4:6)። ትንቢቱ ከሁለት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት ቢነገርም ዛሬ ላለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያንም ከፍተኛ መልእክት አለው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ምንም ማድረግ ስለማንችል ሊያስችለን የመጣውን ኃይል በሕይወታችንም ሆነ በአገልግሎት ቢሮአችን ሥፍራ ልንሰጠው ይገባል።

ሰዎች በተፈጥሮ ከአምላክ የታደሉት ችሎታ ይኖራቸዋል። በትምህርትና በሥራም ብዙ ችሎታና ልምድ ማካበት ይችላሉ።

[5] Vine's, 878.





ይሁን እንጂ የሰይጣንን ሥራ እያፈራረሱ፣ በሽተኞችን እየፈወሱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያስፋፉበት አይቻላቸውም። ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ብንመለከት ያደረገውን ሁሉ ሊያደርግ የቻለው በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ስለተቀባ ነው /ሐ.ሥ. 10:38/።

የፈውስን አገልግሎት እንኳ ሲያካሂድ ኃይል በላዩ ላይ ይመጣ ነበር። ያኔ ነው ድውያንን ለመፈወስ ይንቀሳቀስ የነበረው /ሉቃ. 5:17/። ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች "*የእግዚ አብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና ይላቸዋል*" (1ቆሮ. 4:20)።

ወገኖቼ ያለን ሥጋዊ ችሎታና ዕውቀት እንዲሁም ልምድ ጥሩ ነው። ይሁን እንጂ በክፋትና በጸረ ክርስቶስ ፍልስፍና የተበ ከለውን ዓለም በወንጌል ለመድረስ የሚያስፈልገን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። እንግዲህ መለኮታዊ ኃይል በአገልግሎት የሚረዳንና ከዲያቢሎስ ጋር እየተፋለምን ነፍሳትን ወደ መንግሥቱ እንድ ንጨምር እገዛ የሚሰጠን መለኮታዊ ጉልበት መሆኑን አንዘንጋ።

ጌታ ደቀመዛሙርቱን ሲለናበት የሰጣቸው ማጠቃለያ ሀሳብ "*ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ*" ነው *ያላቸው (ሉቃ 24:49)*። ይህን ኃይል የምንለብሰው የወንጌልን ሥርጭት በኃይል አገልግሎት ወደፊት እንድናራምድ ነው። ኃይል የሚያስፈልገን በፈውስ፣ በታምራትና እርነት በማውጣት እንድ ናገለግል ነው። ጰራቅሊጦስ የኃይልን አገልግሎት ወደ ፊት ለማ ራመድ በሚከተሉት አቅጣጫዎች ይሠራል።

- በግል ሕይወታችን ውስጥ።
- በምእመናን አምልኮ ውስጥ በመሳተፍ።

- በወንጌል ስርጭት እገዛ በመስጠት።
- በመንፈሳዊ ጦርነት ላይ በመርዳት

መለኮታዊ ኃይል በሰዎች ላይ እየመጣ የኤሎሂምን አሳብ እንዲያገለግሉ ያደርጋቸዋል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በርካታ ምሳሌዎች ሊሆኑን የሚችሉ ግለሰቦች አሉ። ለምሳሌ ጌዴዎንን አገሩ በምድያማውያን በተወረረ ጊዜ በፍረሃት የተመታ ሰው እንደሆነ ከታሪኩ እንረዳለን። አንድ ቀን እንኳ ለምንም ጥቅም እበቃለሁ ብሎ አስቦ አያውቅም። የተገለጠለት መልአክ የሚነግረውን ለመቀበል በውስጡ የሚያበረታታው ኃይል አልነበረውም።

የጌዴዎንን ታሪክ ሊለውጥ የቻለው የእግዚአብሔር መንፈስ ሊገባበት ነው። ያኔ ነው ብድግ ብሎ መለከት በመንፋት የክተት አዋጅ አውጆ ሕዝቡን ለጦርነት ያዘጋጀው /መሳ.6፡ 34/። ከዚያ የኃይል ልምምድ በፊት አንድ ሰው እንኳ የማይከተለው በኋላ ግን ቢያንስ ቢያንስ 32000 ሕዝብ ሚሊሽያ ሆኖ ለመዝመት ተከትሎት ወጣ። ጌዴዎን በተቀበለው ኃይል ጠላቶቹን ድል አድርጎ ምድሪቱን ለአርባ ዓመታት ሊያሳርፈ ቻለ። መንፈስ ቅዱስ ሲወርድብን ውስጣችንን በኃይል ይሞላና ለወገን፤ ለሕዝብ፤ ለአገር በረከትና ለላም አምጪዎች ያደርገናል።

ነቢዩ ሳሙኤል ሳኦልን በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን ከቀባው በኋላ በመንገድ ላይ ስትሄድ የነቢያት ጉባኤ ያገኙሃል አለው። ምልክትም ሲሰጠው የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል እንደሚወርድበት፣ ከእነርሱም ጋር ትንቢት እንደሚናገር፣ ልቡ እንደሚለወጥና እንደሌላ ሰው እንደሚሆን ነገረው /1ሳሙ.10፡6-7/። ሳሙኤል እንደ ተናገረው የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት። ለራሱ ለሳኦልም ቢሆን ይህ የሚያስደንቅ አዲስ ልምምድ ነበር።





ኤሎሂም እንደ ተናገረው ሳኦል በእስራኤል ላይ የመጀመሪያው ንጉሥ ሆነ። የሚያሳዝነው ግን በዚህ ሁኔታ የተቀባ ሰው ቅባቱን ጠብቆ አምላኩን እያከበረ አለመኖሩና በውርደት ሞት ዙፋኑን መልቀቁ ነው። እንግዲህ ኃይል በላያችን ሲመጣ ሳኦልን እንደተሰማው እኛም አዲስ ልምምድ ይሰማናል። የመጣውም ኃይል በውስጣችን ለውጥን ያስከትላል ማለት ነው። አሜን!

ዳዊት በቤተ ሰቡ የሁሉ ታናሽ ለጦርነት ያልተመለመለ፣ በግ ጠባቂ፣ በወንድሙ አንተ ኩራተኛ፣ ክፉ የተባለ ነበር። በንጉሥ ሳኦል ገና ልጅ ነህ ይህን ሰው እንኳን አንተ እኛም ልንገጥመው አንችልም የተባለ፤ በጎልያድም ቢሆን የተጥላላና የተናቀ ወጣት ነበር። ሳሙኤል ሲቀባው መንፈስ ቅዱስ በኃይል ወረደበት ነበር /1ሳሙ. 16፡13/። የእስራኤል የጦር አለቆች ንጉሡም ጭምር የተሸነፉለትን ጎልያድን ያጋደመውና በራሱ ሰይፍ አንገቱን ቆርጦ የማረከው፣ በተቀባበት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

ወገኖቼ መንፈሳዊ ፍልሚያ እያካሄድን ወንጌል እንድናሰራጭ ለእኛም ይህ ኃይል (Dunamis) ያስፈልገናል። አኛንም ዳዊትን ከተፈታተኑት አንበሳና ድብ፣ ጎልያድና ፍልስጥኤማውያን ይልቅ እጅግ የከፉ ተዋጊዎች አሉብን። የምናሸንፋቸው በመለኮታዊ ኃይል ብቻ ነው።

ሶምሶን ግንዛቤ ሊገኝላቸው የማይቻለውን ብዙ ድርጊቶች ሊፈጽም የበቃው በመለኮታዊ ኃይል ነው። ሰው ማድረግ የማይችለውን ከፍተኛ ነገር ከማድረጉ በፊት አምላኩን ይጠራል፤ ያኔ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይወርድበታል /መሳ. 14፡6፣ 19፤ 15፡14/ ። ወገኖቼ ጌታን በጸሎት ስንጠይቅ ኃይል ይሰጠናል። ግን የተሰጠንን ኃይል ምን እናደርግበታለን? ነው ጥያቄው። የተሰጠህን

ኃይል በሚገባ ማስተናገድ ከቻልክ ጌታ ቸር ነው ያስታጥቅሃል። ሃሌ ሉያ!

አገልግሎት ለማካሄድና የተቸገሩ ሰዎችን ቋጠሮ ለመፍታት የሚያስፈልገን መለኮታዊ ኃይል ለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት በቂ ማስረጃዎች ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ እያልን ያለ ኃይል የምንንቀሳቀስ ወገኖች ልንኖር እንችላለን። ወይም አንድ ጊዜ ድሮ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋም ያኔ ነበር እንጂ አሁን አልጸልይም፣ ወይም አንዲት ቃል ብቻ ነው ደጋግሜ የምናገረው የምትሉ ብትኖሩ ብርቱ ጥንቃቄ እንድታደርጉ እመክራችኋለሁ። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ በተጠሙ ላይ ይፈስሳል። ሃሌ ሉያ!

ሐዋርያት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሽባውን ሰው ከፈወሱት በኋላ ብዙ ሰዎች ጌታን አከበሩ። ድንጋጤ የወረደባቸው የሃይማኖት መሪዎች ሁለተኛ በዚህ ስም እንዳታስተምሩ ብለው አስጠንቅቀው ለቀቋቸው። እነርሱ ግን ሄደው ከወገኖቻቸው ጋር ጌታ ሆይ! ብለው ጮሁ። ጩኸታቸው በጌታ ዘንድ ስለ ተሰማ ወዲያው መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፣ ተሰብስበው የነበረበትም ሥፍራ ተናወጠ /ሐ.ሥ. 4፡31/። ወገኖቼ ከትዝታ ሕይወት እንውጣና እኛም እንደ ሐዋርያት ለመለኮታዊ ኃይል መምጣት እንጨኽ።

## 7.2 ለመንፈሳዊ ፍልሚያ

መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊ ፍልሚያ ረገድ የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። ጰራቅሊጦስ ዓለምን ወደ ከበረው የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ለማምጣት ስለ ኃጢአት፣ ስለ ፍርድ እንዲሁም ስለ ጽድቅ እየወቀሰ ይጣራል። ውጊያችን በየትኛውም





የሥልጣን መሰላል ላይ ካሉ መናፍስት ጋር እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል። ውጊያችንም የሚያነጣጥርባቸውን ኢላማዎች በኤፌሶን መልእክቱ ሲጠቅስ እንደዚህ ይላል /ኤፌ.6፡12/።

- አለቆች
- ሥልጣናት
- የጨለማ ዓለም ገዦች
- በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር

መለኮታዊ ኃይል ሲወርድብህ በውስጥህ ልዩ የሆነ ለውጥ ይሰማሃል። የመጣው ኃይል በግልህ ማድረግ የማትችለውን ማድረግ ያስችልሃል። ያኔ ነው የመንፈስን ሰይፍ በሚገባ ሥራ ላይ ማዋል የምትችለው /ኤፌ. 6፡17/። መናፍስትን መፋለም ብቻ አይደለም ገና በርቀት መናፍስትን መርምረህ ታውቃቸዋለህ። አመለካከተህ ለመምታትም ይህ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርልሃል ማለት ነው። በመለኮታዊ ኃይል ተሞልቶ የሚመላለስን ሰው ሰይጣን በጣም ይፈራዋል። ምክንያቱም ሥራውን አጋልጦ ለመቅሰፍት የሚዳርገው እርሱ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው።

በመናፍስት ከተለከፉ ሰዎች ውስጥ አጋንንትን ሳወጣ ይህን ሰው ማየት አልችልም፣ አቤት ዓይኑ ሲያስፈራ እያሉ ሲወተውቱ ብዙ ጊዜ ሰምቻቸዋለሁ። የማስፈራቸው እኔ ሁኜ ሳይሆን በውስጤ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው የሚያርበደብዳቸው። አባባላቸው በእኔ ውስጥ ትእቢት ለመስደድ እንደሆነ ስለማውቅ ነገሩን ወደ ውስጤ አላስገባውም። እንዲያውም አብሮኝ የሚሠራው አምላኬ ነው ያስፈራህ እሁንም ተንቀጥቀጥ እለዋለሁ።

በመለኮታዊ ኃይል ውስጥ ሆኖ ማገልገል እንዴት ድል ያስታጥቅ መሰላችሁ? በቅርቡ ከአንድ አሜሪካዊ ውስጥ አጋንንት ሳወጣ ለውዬው በጣም ግዙፍ፣ ቁመቱም በጣም ረጅም ነበር።

ያንን ሰው ብዙ ሳነጋግረው ከቆየሁ በኋላ ሳላስበው በአማርኛ፣ አጋንንት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውደቅ ስለው ተወረወረና ወደቀ። እኔም በሁኔታው ተገርሜ ያሜሪካ አጋንንት አማርኛ ይሰማል እንዴ? አልኩኝ።

ወደ ሁለተኛው ክፍል ፍልሚያ ላይ ደረስንና ስሙን እንዲነግረኝ ጠየቅሁት። የተሰከፈውን ሰው እያስጓራው ለመሆኑ አንተ ማን ነህ ብሎ መንፈሱ እኔን ጠየቀኝ? አሰብ አደረግሁና፤ ይሄስ የሰለጠነ አጋንንት ነው ብዬ፣ አንተ አሁን ማወቅ የፈለግኸው ሥልጣኔን ነው፤ ስማ! የእኔን ሥልጣን ማወቅ መብትህ ነው። እኔ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ! ብዬ በታላቅ ድምጽ ጮኽኩበት። ያኔ በጣም አስቀዘፈውና በእኔ ትእዛዝ ሰባት አለቆች ሰባት ጭፍሮች ተጋልጠው በየተራቸው እየሰፈሰፉ ወጡ። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን!

ይህን የመሳሰሉ ጌታ ያደረጋቸው ብዙ ሥራዎች አሉ። ሁል ጊዜ የሚያስደንቀኝ ጌታ በውስጣችን ያስቀመጠው ታላቅ ኃይል ነው። የኤሎሂም ቃል *"በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን"* ይላል (ሮሜ. 8:37)። እንደገናም ሐዋርያው *"ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን"* ይላል (1ቆሮ. 15:57) ሃሌሉያ!

የእግዚአብሔርን ዓላማ አገልግሎ ለማለፍ በመለኮታዊ ኃይል ላይ መደገፍ ያስፈልጋል። የእምነት አባቶች ታሪክ የቆየ ቢሆንም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዴት እንደረዳቸው መገንዘብ ለእኛም እምነት ይጨምርልናል። ስለሆነም የጥቂት የብሉይም የአዲስ ኪዳንንም ተፋላሚዎች በአጭሩ እንመልከት።





የእግዚአብሔር ሰው ሙሴን የፈርኦን ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ ቃላተኞች እርሱ የሚያደርጋቸውን ታምራት እናደርጋለን ብለው ሲገዳደሩት መጡ። እስከ ተወሰነ ድረስ ሙሴ የሚያደርገውን ዓይነት ታምራት አደረጉ። በመጨረሻው ላይ ግን አቃታቸውና ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው ሲሉ መሸነፋቸውን አረጋገጡ /ዘጸ. 8:19/።

ዮፍታሄ የተባለው ሰው የሚያስከብር ታሪክ አልነበረውም። ሕይወቱ የጋለሞታ ሴት ልጅ በመባል ይጀምራል። በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ወንድሞቹ አገር ሁሉ እያወቀ ከእኛ ጋር አይወርስም ብለው አሳደውታል። በሄደበትም አካባቢ የተከተሉት እንደ እርሱ ያሉ ምናምንቴ ሰዎች ብቻ ነበሩ ። በአሁኑ አነጋገር ዮፍታሄ የጋንግ (የወሮ በላዎች) መሪ ነበር ማለት ነው /መሳ. 11:3/።

እንደዚህ ያለው የማኅበራዊ ኑሮ ችግር ያለበትን ሰው ነው አሞናውያን እስራኤላውያንን ባስጨነቁ ጊዜ የገለአድ ሽማግሌዎች ለመሪነት አጭተውት ለምነው ይዘውት የመጡት። ያንን ታሪክ ብልሹ የሆነ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ላይ ሲወርድበት ታሪኩ ተለወጠ /መሳ. 11:29-33/። አሞናውያንን ተዋግቶ በሀያ ከተሞቻቸው ውስጥ በታላቅ አገዳደል መትቶ አሸነፋቸው። ምድሪቱም ለስድስት ዓመታት እረፍት አገኘች።

መንፈሳዊ ኃይል እንደዚህ የተናቀውንና ይረባል ያልተባለውን የዱርዬ መሪ በመንፈሱ ለውጦ የዓላማው ፈጻሚ ያደርገዋል። የእኔና የእናንተስ ታሪክ እንዴት አስከፊ ይሆን? ታሪካችን ምንም ይሁን አንድ የማበስርላችሁ ምስራች አለኝ፣ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ሲወርድብን እንለወጣለን። ከዚያም በኋላ ለሕዝብ በረከት፣ ለአገር በረከት፣ ለዓለም በረከት ለቤተ ክርስቲያን በረከት እንሆናለን።

ጰራቅሊጦስ የመጣው ያልሆነውን እንድንሆን፣ ያላደረግነውን እንድናደርግ ሲያስችለን ነው። ሃሌ ሉያ!

ወገኖቼ መንፈሳዊ ኃይል የቱን ያህል በሰው ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ከላይ ባቀረብኳቸው ምሳሌዎች አሳይቻለሁ። የጌታ ቃል *"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው"* ይላል (ዕብ. 13፡8)። መንፈሳዊ ኃይል እኛንም ሲያገኘን እንደዚህ ነው ለውጦ የሚጠቀምብን። ማን ስለመሆንህ አታስብ የሚያስፈልግህ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። መንፈሳዊ ጦርነትን ለማካሄድ ኃይል ያስፈልገናል። ጌታ በታላቅ ኃይል እንዲሞላችሁ አጥብቃችሁ ጸልዩ።

## 7.3 በሽተኞችን ለመፈወስ

በሽተኞችን ለመፈወስ መለኮታዊ ኃይል የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። በፈውስ አገልግሎት ለረጅም ዘመናት ጌታን አገልግያለሁ። በሕክምናም በኩል ያለውን ከበሽታ መዳን ተመል ክቻለሁ። መለኮታዊ ፈውስን ከመድኃኒት ጋር ማወዳደር ፈጽሞ አይቻልም። መለኮታዊ ፈውስ የሚካሄደው ሁሉን ቻይ በሆነው በሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኃይል ነው። ሕክምና ግን በተለምዶና በዕውቀት ላይ ተመርኩዞ ነው።

መለኮታዊ ፈውስ ቀጠሮ አይሰጥም። ምናልባት በሽታህ እንዲህና እንዲህ ሊሆን ይችላል በማለት ተስፋ ዐልባ አስተያየት አይሰነዝርም። የሞት ቀጠሮም በጭራሽ አይሰጥም። ሃሌ ሉያ! ይህን ስል ሕክምና አያስፈልግም ለማለት እንዳልሆነ አንባቢዎቼ እንድትረዱልኝ እወዳለሁ። የሕክምና ዕደ ጥበብ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ከፍተኛ በረከት ነው። ይሁን እንጂ በመገረፉ





ቁስል ከሚገኘው መለኮታዊ ፈውስ ጋር ማወዳደር ጨርሶ አይቻልም ነው የምለው።

በቅርቡ ጌታ የሠራውን አንድ አስደናቂ የፈውስ ታምር ልንገራችሁ። ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ የወንጌል አገልግሎት ስሰጥ፣ በፈውስ ሰዓት ላይ አንድ መገለጥ መጣ። መገለጡም ስለ አንዲት በጡትዋ ውስጥ የካንሰር ዕጢ ስላለባት ሴት ነበር የተነገረው። አንቺ ሴት ሐኪምሽ የጡት ካንሰር አለብሽ ብሎ ለኪሞ ቴራፒ ቀጠሮ ሰጥቶሻል፣ ጌታ እንዲህ ይልሻል ካንሰሩን ውኃ አድር ጌዋለሁ፤ ለማሽ እቴ ሂጂና ሐኪምሽን እዩ፣ ካንሰርሽ ወዴት ሄደ ይልሻል የሚል ነበር።

እህታችንም ዶክተሯ ዘንድ ሄዳ ከኪሞ በፊት የመጨረሻ ምርመራ ሲያደርግላት በታላቅ ድንጋጤ ካንሰርሽ ወዴት ሄደ አላት? ጡትዋን ሲመረምረው በፊት እንደ ድንጋይ ይሰማው ነበር አሁን ግን እንደ ውኃ ሆኖ አገኘው። እርሷም ጌታ የተናገረውን ነገረቻው። በመጨረሻም ውኃውን በስሪንጅና መርፌ ቀድቶ አወጣው። ልዩ ምርመራ ቢያደርግላትም ካንሰሩን ሲያገኘው አል ቻለም። እንዲያውም የደም ብዛትና የስኳር በሽታም ነበረባት ሁሉም በአንዱ መገለጥ ተጠራርገው ጠፉ። ሃሌ ሉያ!

### 1) እንዲፈውስ ኃይል ሆነለት

የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ጌታ እንኳ ኃይል በእርሱ ላይ ካልመጣ በስተቀር ምንም ማድረግ አይችልም ነበር። እንዲፈውስ ኃይል ሲሆንለት ግን በአልጋ ተሸክመው ያመጡትን ሰው አልጋ አሸክሞ ወደ ቤቱ ሰደደው /ሉቃ 5፡17/። አሜን! ጌታ ያንን ኃይል በመንፈስ ቅዱስ በኩል ወደ እኛ እንዲያደርስና በእርሱ ውስጥ ያደረገውን እንዲያደርግ ነው የላከው። ለዚህም ማረጋገጫ እንዲ

ሆነን "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የማደር ገውን ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ሲል ጌታ የተ ናገረው ነው (ዮሐ. 14:12)።

አስራ ሁለት ዓመት ደም የሚፈሳት ሴት ለመፈወስ ብዙ ሙከራዎች አድርጋለች። የማረካት ዜና ግን የየሱስ ዝና ነበር። ከቤቷ ሳትነሳ የምታደርገውን ነገር አልማ ጌታ ወደሚገኝበት ስፍራ በአሰሳ ደረሰች። ደም ከውስጧ ሲጎርፍ ማየት ያሰለቻት ሴት ይህ ነው ቀኔ ብላ የእምነት ጣቶቿን በኢየሱስ ልብስ ላይ አሳ ረፈቻቸው። ወዲያውም ከጌታ ኃይል ወጣና ፈወሳት። ጌታም ኃይል ከእርሱ መውጣቱን ሲያውቅ ሴቲቱ ደግሞ መፈወሷን በራሷ ሰውነት አወቀች /ማር. 5:30-34/።

ዛሬም ቢሆን በፈውስ አገልግሎት የተቀቡ አገልጋዮች የሚጸልዩላቸው ህመምተኞች መፈወሳቸውን እንዲያውቁ ጌታ ከአገልጋዩ ውስጥ ኃይል እንዲወጣ ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ የተፈወሱትም ልዩ የሆነ ኃይል በውስጣቸው ሲገባ ይሰማቸዋል። እንዲህ ያለው ሁኔታ፣ ለፈዋሹ ምልክት ሲሆን ለተፈዋሹም የመለኮታዊ ፈውስ ማረጋገጫ ነው። አሜን!

ጌታን የታመሙ ሰዎች ሁሉ ይፈልጉት ነበር። ምክንያቱም የሚፈውስ ኃይል በእርሱ ውስጥ ነበር። በሉቃስ ወንጌል 6:17-18 ድረስ ያለውን ቃል ብናነብ፣ ከተለያየ ስፍራ በሽተኞች ይመጡ ነበር። በተለያየ በሽታ የሚሰቃዩት ሲዳስሱት ይፈወሱ ነበር ከእርሱም ኃይል እየወጣ ይፈውሳቸው ነበር። መለኮታዊ ኃይል ያለበትን ሰው ብዙዎች ይፈልጉታል። አንተም በዚሁ ኃይል ብትሞላ ለሰዎች በረከት ትሆናለህ። በጸሎትህ ጌታን ጠይቀው በኃይሉ ይሞላሃል።





### 2) ኃይል ለአስራ ሁለቱ

ጌታ ለአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ኃይል ሰጣቸውና ሁለት ሁለት እያደረገ ላካቸው። በእርኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን ሰጣቸው እነርሱም ወጥተው ሰበኩ፣ አጋንንት አወጡ፣ ዘይት እየቀቡ ህመምተኞችን ፈወሱ /ማር. 6:7-13/። ለሰባውም ሥልጣን ሰጣቸውና ላካቸው እነርሱም ሄደው ብዙ ውጤት ያለውን አገልግሎት አገለገሉ። ያስደነቃቸው ግን በጌታ በኢየሱስ ስም አጋንንት ለእነርሱ መታዘዛቸው ነበር።

### 3) የፈውስ ኃይል ከእሳቱ በኋላ

ጴጥሮስ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት በኋላ ጌታን ያገለገለው በአስደናቂ የፈውስ ኃይል ነበር። የመጀመሪያው ፈውስ ቤተ መቅደስ አጠገብ በሽባው ሰው ላይ ተፈጸመ። መምህራቸው ሞቶ ቀርቷል ያሉትን ተቃዋሚዎች ሁሉ በሚያሳፈር ሁኔታ በስሙ ኃይል የአርባውን ዓመት ጎልማሳ ተረተረና አዘለለው። ፈሪሳውያን ተደናገጡ እነዚህ ደግሞ በምን ኃይል፣ ወይስ በማን ስም ነው ይህን የሚያደርጉት ብለው ሊመልሱት የማይችሉት ውዝግብ ውስጥ ሰጠሙ። መለኮታዊ ኃይል ይህን አደረገ /ሐ.ሥ. 3:4-6/። ዛሬ በውስጣችን የሚሠራውን ኃይል መረዳት ያልቻሉ ሁሉ በከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ለመሆናቸው አጠያያቂ አይደለም። የኃይል አገልግሎት ደግሞ በመጨረሻው ዘመን ላይ እየጨመረ የሚሄድ እንጂ ጨርሶ አይቀንስም።

መንፈስ ቅዱስ ደጋግሞ ሲወርድብን ኃይላችን እየጨመረ መሄዱ እውን ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ በድጋሚ ተሞልቷል /ሐ. ሥ. 4:31/። ይህ ሁኔታ ነው በእጁ ታላላቅ የፈውስ ታምራት እንዲደረግ ምክንያት የሆነው። ለፈውስ ወደርሱ የመጡ ሁሉ ይፈወሱ ነበር። ሌሎች ደግሞ ህመምተኞችን

እንዲፈወሱ በጴጥሮስ ጥላ ስር ያኖሯቸው ነበር /ሐ. ሥ. 5፡15/። ወገኖቼ እኛም በጸሎታችን ጊዜ ሁሉ ጌታን ደጋግመህ አፍስስልን እንበለው። ጌታም መንፈሱን ፈስስስስ....ስ ያደርገዋል። አሜን ይፍሰስ!

በጳውሎስ እጅም የተከናወነው የሚያስደንቅ የፈውስ ሥራ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስና ኃይል ደንግጎ የጻፈልን እርሱ ነው። አጋንንትን በማውጣትም ሆነ የፈውስ መገለጦችን በማስተላለፍ ጥርት ባለ ሁኔታ ነው ያገለገለው። ለዚህም የተደረጉትን ፈውሶች በሚከተሉት ክፍሎች ማንበብ ይቻላል /ሐ.ሥ. 14፡9-10፣ 16፡18፣ 28፡8-10/። ሌላው ቀርቶ አካሉን የነካ ጨርቅ እንኳ ወደ በሽተኞች እየተላከ የታመሙ ይፈወሱ ነበር። የመላጥያ ደሴት ባለቤት አባቱንና በደሴቲቱ የሚኖሩ በሽተኞች ሁሉ ነው ፈውሶ ወደ ሮም ጉዞውን የቀጠለው።

በዚህ ሁሉ ድርጊቱ፣ ሁላችንም ልንል የሚገባውን ነገር እንዲህ ሲል ተናገረ *"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም ... ሰብኬአለሁ"* ይላል (ሮሜ. 15፡18-19)። ጌታችን ኢየሱስ እንዳገለገለ እኛም እንድ ናገለግል መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። ይሁን እንጂ ማመንና መጓዝ ይኖርብናል። በሐዋርያት መሰረት ላይ ቆመናል ካልን እኛም ማድረግ ያለብን ከላይ ኃይል መልበስና መለማራት ነው።

የሐዋርያት ቅባት የከተሞችን ሁኔታ ከለወጠ በእኛም ውስጥ ያለው ኃይል የሚያደርገው እንዲሁ ነው። በተለይም ለይጣናዊ ሥራ በገነነበት በዚህ ዘመን እያንዳንዳችን በመለኮታዊ ኃይል መሞላት አለብን። በከተሞቻችን ውስጥ ለውጥ ማምጣት የሚችል መንፈስ ቅዱስ ነው። ወገኖቼ ለመኖር ኃይል፣ ለማገልገል ኃይል፣





ለማምለክ ኃይል፣ ለፍልሚያ ኃይል እንዲሁም ለፈውስ ኃይል ያስፈልገናል። አቤቱ አምላካችን ሆይ ኃይልህን አልብሰን።

## 7.4 የአዲስ ኪዳን አገልግሎት

ሐዋርያው የብሉይና የአዲስ ኪዳንን አገልግሎት ሲያነፃፅር የቀደመውን የፊደል አገልግሎት ሲለው ሁለተኛውን ደግሞ የመንፈስ አገልግሎት ይለዋል /2ቆሮ. 3፡6/። ጨምሮም ሲያብረራም *"ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል"* ይላል። ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው እንግዲህ ሕይወት የሚሰ ጠውን የመንፈስ አገልግሎት ነው። ስለ ፊደል አገልግሎት ሲተርክ ያ! የፊደል አገልግሎት በክብር ከሆነ የመንፈስ አገልግሎት የሚበልጥ መሆኑን ሐዋርያው ገጸልናል /2ቆሮ. 3፡7-11/። ያኛው አገልግሎት ተሽሮ በመንፈስ አገልግሎት ተተክቷል። ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ለዘላለም በውስጣችን ሊኖርና ከእኛ ጋር ሊሆን የመጣው ጰራቅሊጦስ ነው።

በኤሎሂም መንፈስ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን ከታየው የበለጠ ክብር ውስጥ መግባት ትችላለች። ስለዚህ ቅዱሳን ለበለጠ መለኮታዊ ኃይል መቃተት አለብን ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን መደበኛ ፕሮግራም ከማካሄድ ውስጥ ወጥታ፣ ክብር ወደ ሞላበት አገልግሎት መሸጋገር አለባት። ይህንንም ማድረግ የምትችለው እንደሙሴ እባክህ ክብርህን አሳየኝ ብላ በመጸለይ ነው /ዘጸ. 33፡18/። የጌታን ክብር ያየ ክብሩን አይጠግብም። ለዚህ ነው ደጋግሞ ክብሩን ያየው ሙሴ እንደገና አሳየኝ ብሎ የሚጠይቀው። ጌታ ሆይ ክብርህን አሳየን! ኃይልህን በውስጣችን ግለጠው! አሜን! ከዚህ ቀጥለን ሕይወት የሚሰጠውን የመንፈስ አገልግሎት በአጭሩ እንመልከት።

## 1) ጌታ ኢየሱስ

ጌታ የሰጠው አገልግሎት ሁሉ እምባን የሚያብስ ሞትን በትንሣኤ፣ እውርነትን በዓይናማነት፣ አንካሳን በመዝለል፣ ማዕበልን በፀጥታ፣ ረሃብን በጥጋብ፣ ውርደትን በክብር የሚተካ አገልግሎት ነበር። ለዚህ ዓይነት አገልግሎት መሰረቱ በላዩ ላይ ያረፈው መንፈስ ቅዱስ ነው /ማቴ 3:16/። ጌታ ታምራትን ለማድረግ ሲያስፈልገው ኃይል በላዩ ላይ ይመጣ ነበር /ሉቃ 5:17/። ያለ ኤሎሂም ኃይል አንዳች አላደረገም። ሐዋርያው ጴጥሮስ በጴንጠቆስጤ ቀን ስብከቱ ስለ መሲሁ መገደልና በግድያውም የአይሁድ መሪዎች ስለመሳተፋቸው እየገለጸ እግዚአብሔር በታምራት፣ በድንቆችና በምልክቶች ሥራ የገለጠው ሰው እንደነበረ ተናገረ።

ዮሐንስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ አንተ ነህ የምትመጣው መሲሀ ወይስ ሌላ እንጠብቅ ብሎ አስጠይቆ ነበር። ጌታም ለመልእክተኞቹ የሰጠው ምላሽ የኃይልን አገልግሎት በተግባር እያሳየ ነበር። እንደዚህም አላቸው። *"ሄዳችሁ ያያችሁትንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ አውሩለት"* (ሉቃ 7:22)።

- ✓ አንካሶች ይሄዳሉ
- ✓ ለምጻሞች ይነጻሉ
- ✓ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ
- ✓ ሙታንም ይነሳሉ
- ✓ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል

ወገኖቼ እኛስ ምን የምንተርከው የኃይል አገልግሎት አለን? ጌታ የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት ሂዱና ያያችሁትን አውሩለት ብሎ ያዘዛቸው ድንቆችና ታምራትን እንዲነግሩት ብሎ ነው። ሐዋርያትም በበኩላቸው ያወሩት ጌታ ያደረገውንና በእነርሱም እጅ የተደረጉትን ነበር። በቤተ ክርስቲያናችን ይህ ተደረገ ብለን የምናወራው መኖር አለበት። ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ዛሬም





ሕያው ነው ይሠራል። የምናወራው ድንቅና ታምር ከሌለ ወደ ጥንቱ መመለስ እንድንችል አጥብቀን እንጸልይ።

ከጌታ ዕርገት በኋላ ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ ሲናገሩ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ቀብቶ የተጠቀመበት እንደሆነ ሰበኩ። እርሱም በተቀበለው ኃይል አጋንንትን አወጣ፣ ለህምምተኞች ፈውስን ሰጠ ብለው ተረኩ /ሐ.ሥ. 10:38/። እንግዲህ ለጌታ ኃይል ካስፈለገው ለእኛም በጣም ያስፈልገናል። ስለዚህ እንጸልይ ጌታ ይሰጠናል።

## 2) ሐዋርያት

የኢየሱስ ምስክሮች ለሆኑትና የመንግሥቱን ሥራ ከእርሱ ተረክበው ለሚያራምዱ ኃይል እንደሚያስፈልጋቸው ተነገራቸው /ሐ.ሥ. 1:5/። የተነገራቸው የጸራቅሊጦስ ኃይል ከመጣ በኋላ ግንዛቤ የማይገኝለት ብዙ ድርጊት በሕይወታቸው ተከናወነ።

- ✓ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሽባውን አስነሱት /ሐ.ሥ. 3:6፤16/
- ✓ የጴጥሮስ ጥላ ሰዎች ላይ ሲያርፍ ይፈወሱ ነበር /ሐ.ሥ. 5:15/
- ✓ እስጢፋኖስ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ ታምራት አደረገ /ሥራ. 6:8 /
- ✓ ጳውሎስ ጨርቁ እየተላከ ሰዎች ይፈወሱ ነበር /ሐ.ሥ. 19:11-12/
- ✓ ከተሞች በመንፈስ ቅደስ ኃይል ተነዋወጡ /ሐ.ሥ. 13:44፣48/።
- ✓ የኢየሩሳሌም ከተማ በኢየሱስ ትምህርት ተሞላች /ሐ.ሥ. 5:28/።
- ✓ በሰማርያ ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ /ሐ.ሥ. 8:8/።
- ✓ በአንጾኪያ ከተማ ሕዝቡ ሁሉ ሊሰሙ ወጡ /ሐ.ሥ. 13:44/ ።

- ✓ በፊልጵስዮስ ከተማ እዚህ ከተማችንን ያናውጣሉ ተባሉ /ሐ.ሥ. 16:20/፡፡
- ✓ በተሰሎንቄ ከተማ ዓለምን ያወኩ ወደዚህ መጥተዋል ተባሉ /ሐ.ሥ. 17:6/፡፡
- ✓ የኤፌሶን ከተማ በሙሉ ተደባለቀ /ሐ.ሥ. 19:29/፡፡

## 3) እኛ

በአገራችን በኢትዮጵያም የተነሳው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይዘቱ ይህን ይመስል ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ቃል *"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"* ተብሎ የተነገረው ትንቢት ያን ጊዜ ተፈጽሟል ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 1958 አካባቢ ነበር መንፈስ ቅዱስ በአንዳንድ ከተሞች ውስጥ ወጣቶች ላይ መፍሰሱ መሰማት የጀመረው፡፡ ከእነዚህም ከተሞች ውስጥ እኔ የማስታውሳቸው ሐረር፣ ናዝሬት፣ ደብረዘይት፣ ባሕር ዳርና አዲስ አበባ፣ ይገኙባቸዋል፡፡ እኔንም የመንፈስ ቅዱስ እሳት እልሳተኝም፡፡ ወደምኖርበት አምቦ ከተማ የእሳቱ ትሩፋት የደረሰኝ ዓመት ያህል ዘግይቶ ነበር፡፡

በእሳቱ የተለኮሱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በታላቅ ደስታ እሳቱን እያራገቡ በየከተማው መዞር ጀመሩ፡፡ የተማረ አዲስ ትውልድ፣ አረጋውያንና ጎልማሶች በእሳቱ ወላፈን ተዳስሰው ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ተመሰረተች፡፡ ወንጌላውያን በታላቅ ኃይል እየሰበኩ፣ አጋንንት እያወጡና በሽተኞችን እየፈወሱ መዞር ጀመሩ፡፡ መንፈስን የሚያድሱ፣ የጌታን ምፅአት የሚያበስሩ አዳዲስ ዝማሬዎች በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ተሰጡ፡፡ እርኩሳን መናፍስት የያዛቸው ሰዎች ገና እጥራችን አጠገብ ሲደርሱ ይጮኹ ነበር፡፡





በኢየሩሳሌምና ሌሎች ከተሞች ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እሳት ላይ ውኃ ሊጨምሩ እንደጣሩ ሁሉ ጌታ ወደ ምድራችን የላከውንም ረድኤት የገጠመው የዚያኑ ዓይነት ፈተና ነበር፡፡ በየከተማው ወንድሞችና እህቶች ተደበደቡ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም ተዘጉ፣ መእመናን እየታፈሱ በወህኒ ተጣሉ፡፡ በጊዜው የነበሩ የአገር መሪዎች ለአቤቱታችን የሰጡን ምላሽ ተጨማሪ ስደት ማዘዝ ነበር፡፡

እሳትን ቢመቱት ይበተንና ብዙ ቦታ መቀጣጠል ይጀምራል፡፡ በኦሮምኛ እንዲህ የሚል አባባል አለ "ኢቢዲፍ ኢዬሲ ቱቱቃ ኢንጃላቱ" ትርጉሙም እሳትና ድሃ ሲነኩት አይወድም ማለት ነው፡፡ በአገራችንም በተደጋጋሚ ተነስቶ የነበረው ስደት የመንፈስ ቅዱስን እሳት ያጠፋ መሰለው እንጂ እሳቱስ እንደ ሰደድ እየተቀጣጠለ በየቤተ እምነቱ ሰርጎ ገባ፡፡ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ዛሬ አለችበት ሥፍራ ደረሰች፡፡ የደረሰችውም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሙላት በውስጧ ስለሠራና ድንቆችና ምልክቶችም ስለ ሚደረጉ ነው፡፡ በዓለም ውስጥ ያሉ የእሳት አደጋ መኪኖች ሁሉ ቢሰበሰቡ የመንፈስ ቅዱስን እሳት ማጥፋት አይችሉም!!!

ዛሬም ይኸው ኃይል ለምእመናን ሁሉ ያስፈልጋል፡፡ በዓለማችን ውስጥ ብዙ ሪቫይቫሎች ተነስተው ነበር፡፡ ያ! በያንዳንዱ አገልጋይ ላይ የነበረው ቅባትና እሳት ወራሽ አጥቶ ይሁን አውራሽ እልም ብሎ ጠፍቷል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈስ አገልግሎት ወደ ፊደል አገልግሎት ዝቅ ብላለች፡፡ ይህን ክፍል ስጽፍ እንድ የተሰፋ ጭላንጭል ያዘለ መገለጥ በውስጤ አለፈ፡፡

ይኸውም ጌታ ለምድራችን አንድ ሌላ እድል ይሰጣታል፡፡ የሚቀጥለው የኃይል አገልግሎት ክተራው ቤት እስከ ቤተ መንግ

ሥት፣ ካልተማረው እስከ ሊቁ፣ ከድኃው እስከ ንጉሡ፣ በእምነትም በኩል የትኛውንም የእምነት ክፍል የሚዳስስ ይሆናል:: ያልተቆጠበ የእግዚአብሔር ክንድ ይገለጣል:: ድኅነት ለብልጽግና፣ በሽታ ለጤና፣ ጦርነት ለሰላም፣ ጸብ ለፍቅር፣ ልመና ለመስገስ፣ ጨለማ ለብርሃን፣ ጣኦት አምልኮ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሥፍራ ይለቃሉ:: ምድራችን ትፈወሳለች:: አሜን ይሁንልን!

### 4) ወንጌልን በኃይል ስበኩ

ዓለም የሃይማኖትን ነገር ስምታ ስምታ በተሰላቸችበት ዘመን ላይ ነው ያለነው:: የዓለም ፈላስፎች የሃይማኖትን አላስፈላጊነት እያጣጣሉ በተቀናጀ ሁኔታ ያስተምራሉ:: ዓለም የምትፈልገው አዲስ ነገር ነው:: ለመሆኑ በወንጌል ስብከት አዲስ ነገር ልናመጣ እንችላለን? አዎን በኃይል አገልግሎት እርኩሳን መናፍስትን እያወጣን፣ በሕክምና ረገድ ምንም መልስ ያልተገኘላቸውን በሽታዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየፈወስን፣ የተፈጥሮ ሕጎችን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመቋቋም የሚገኙት ውጤቶች ፈላስፎችንም ጭምር ያንበረክካሉ::

የወንጌል ስርጭት በኃይል ካልሆነ በስተቀር ለውጥን ሊያመጣ አይችልም:: ሐዋርያው ጳውሎስ *"የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና"* ሲል ይነግረናል (1ቆሮ. 4:20):: እንዲያውም ስለ አገልግሎቱ ያለውን ትምክህት በመለኮታዊ ኃይል ላይ ሲያኖረው እንዲህ ይላል *"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም"* (ሮሜ 15:18-9):: ወንጌል ሰባኪ ሆይ! ነፍሳትን መማረክ የሚያስችል መለኮታዊ ኃይል ስለሆነ ዘወትር እርሱን ተራብ ተጠማ:: ጌታ በኃይሉ ይሞላሃል::



# 8

# የመንፈስ ቅዱስ ልምምዶቼ

የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ በአንድ ምሽት የሚመጣ አይደለም:: መንፈሳዊ ስጦታን ከመለማመድ በፊት ከሰጪው ጋር በግል መተዋወቅ አስፈላጊ ነው:: አምላካችንን በሰው ቴሌስኮፕና ላቦራቶሪ ማወቅ ጨርሶ አይቻልም:: እንዲያውም እንዲህ ባለ ሁኔታ እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚሞክሩ በመጨረሻው ራሳቸውን አምላክ አድርገው ይቀመጣሉ:: መዝሙረኛው እንደዚህ ይላል *"ጌታችን ታላቅ ነው፣ ኃይሉም ታላቅ ነው ለጥበቡም ቁጥር የለውም"* (መዝ. 147:5)::

ልንመረምረው የምንሞክረው አምላክ የህዋውንና በውስጣቸው ያሉትን የምናያቸውንና የማናያቸው ፍጥረታት ሁሉ የፈጠረ ነው /መዝ. 33:6-11/:: እርሱን ማወቅ የሚቻለው በቀጥተኛ ው በር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመምጣት ብቻ ነው:: እስቲ ከዚህ ቀጥሎ የመጀመሪያ የሕይወቴን ሁኔታ ልተርክላችሁ::

## 8.1 ቅድመ ደኅንነት ሕይወቴ

እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገር ባህል የወላጆቼን ሃይማኖት እከተል ነበር:: እንዲያውም ለሶስት ዓመታት ሙሉ

በባህላችን የሚሰጠውን የሃይማኖት ትምህርት በመማር መሰስተኛ ዕውቀት ለማግኘት በቅቻለሁ:: ይሁን እንጂ እርካታ የሚባል ነገር ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ ከእኔ ርቆ ነበር:: ምክንያቱም እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ ብሎ ያለውን ጌታ ኢየሱስን በግል አላወቅሁትም ነበርና ነው::

በወጣትነት ዕደሜዬ በእስራ ውስጥ እያለሁ ጠያቂ በሆነው ጨቅላ አእምሮዬ ስለ እግዚአብሔር መኖር ወይም አለመኖር እመራመር ነበር:: ለረዳት ሕክምና ኮርስ ወደ ባፕቲስት ሚሽን አምቦ ከተማ ውስጥ ትምህርት ቤት ለመግባት ከፍተኛ ውጤት አገኘሁና የሁለት ዓመት ኮርስ ጀመርኩኝ:: በሞያ ትምህርት ቤቴ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንደማንኛውም ኮርስ ይሰጥ ስለ ነበረ የመውሰድ ግዴታ ነበረብኝ:: ከዚህ በፊት በግዕዝ ለሶስት ዓመት አጠናሁ አሁን ደግሞ ሌላ የሁለት ዓመት የሃይማኖት ትምህርት ገጠመኝ::

ከተወለድሁባት ጌዶ ከምትባል ከተማ ተለይቼ ወደ ሚሲዮኖቹ ትምህርት ቤት ሳመራ እናቴ ስትሸኘኝ አንድ አደራ ጣለችብኝ:: አደራዋንም ስትገልጽልኝ የጥንት እናቶች ከሚያጠልቁትና በመቀነት ከሚታጠቁት ቀሚሷ ውስጥ ሁለት ጡቶቿን አውጥታ ልጄ አደራህን በጠባሃቸው ጡቶች ይዤሃለሁ ካቶሊክ እንዳትሆንብኝ (ፎቶሊክ ነበር እርሷ የምትለው) እያለች ለመነችኝ:: በእነዚያ ዘመናት በምኖርበት አካባቢ ከኦርቶዶክስ እምነት ውጭ የሆነ ሌላው የክርስትና እምነት ሁሉ ካቶሊክ ነበር የሚባለው:: ይህ የእናቴ አደራ በባፕቲስት ሚሽን ለሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቶሎ እጅ እንዳልሰጥ አደረገኝ:: እውነታው ቢገባኝም እንኳ ሁሌ ትዝ የሚለኝ የእናቴ ጡቶች ስለ ነበሩ ክርስቶስን ከመቀበል ወደ ኋላ አዘገየኝ::





ዶ/ር. ዴኒስ ካርልሰን የተባሉ በባፕቲስት ሚሽን የሕክምና ሚሽነሪ ነበሩ መጀመሪያ ወደ ጌታ የመሩኝ:: ሚሽነሪው ወጣቶችን ወደ ክርስቶስ የሚመሩት እምባ በተቀላቀለበት የወንጌል ስብከታቸው ነበር:: ከእለታት አንድ ቀን ተማሪዎቻቸው የሆኑትን ሁሉ ይዘው ወደ ወንጪ ሃይቅ ለሽርሽር ወሰዱን:: እንደ ደረስንም ጓደኞቼ ሁሉ ሃይቁ ላይ በታንኳ ይዝናኑ ነበር:: እኔ ግን ሃይቁ ዳር ቆሜ ተፈጥሮን እያደነቅሁ ዓይኖቼን በውኃውና አካባቢው መልክአ ምድር ላይ አሳርፌ እቃኝ ነበር::

ያኔ ነበር ዶ/ር. ካርልስን ወደኔ መጥተው ልጄ ሰይፉ በጣም እወድሃለሁ ሲሉ ረጅም እጃቸውን ትከሻዬ ላይ በማሳረፍ ፍቅራቸውን የገለጹልኝ:: እኔም መልሼ እንደምወዳቸው ገለጽኩላቸው:: በመቀጠልም ላልፈው የማልችለውን አንድ ጥያቄ ጠየቁኝ:: ጥያቄውም "ስመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝና ጌታ አድርገህ ተቀብለሃል?" የሚል ነበር:: ለጥቂት ጊዜ እስብ አደረግሁና አልተቀበልሁም የሚል ምላሽ ሰጠኋቸው:: አሁን ልትቀበለው ትፈልጋለህ አሉኝ? ጥያቄአቸውን ለመመለስ የእናቴ ጡቶች ትዝታ ውልብ አለብኝና በሃሳብ ተወስጄ ዝም አልኩኝ:: ምላሼን ለመስማት ዶክተሩ በትዕግስት ይጠባበቁ ነበር:: እኔም ከጥቂት የዝምታ ሽለብታዬ አምልጬ በመውጣት አዎን እቀበላለሁ አልሁ:: ወዲያው የሽርሽሩ እንግዳ ስባኪአችን ከሆኑ አቶ ላቀው ተሰማ ጋር በጸሎት ወደ ጌታ መሩኝ::

የእናቴ ጡቶች አደራ ከትዝታ ማህደሬ ውስጥ የደወል ድምጻቸውን ቢያሰሙኝም ከጡቶቿ የሚበልጠውን፣ በመስቀል ላይ የሞተልኝን፣ እርሷንም ጡቶቿንም የፈጠረውን ጌታ እንድቀበል በድንገት የውስጥ ዓይኖቼ በሩልኝና በምስጋና ተሞላሁ:: የዘላለም ሕይወት ማግኘቴ በትክክል ተሰማኝ፤ ደስታና ሰላም ውስጤን ሞላው:: የይሉኝታ ሰንሰለት ከሕይወቴ ተሰባብሮ ወደቀና እውነት

ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው ብዬ በውስጤ አረጋገጥሁ:: እውነት ነው ብዬ ላመንሁበት ነገር መስጠት እንጂ ሰውን እየፈሩ መመላለስ ትክክል እንዳልሆነ ተረዳሁ::

ለምወዳት እናቴ የሚያስፈልጋት ኢየሱስ ነው ብዬ በውስጤ ማብላላትና መጸለይ ቀጠልሁ:: ስላገኘሁት ጌታ ለእናቴ ለመመስከር ጊዜም አልወሰደብኝ:: በክርስቶስ የሚገኘው መዳን ለወላጅ እናቴም ሆነ ለቤተ ዘመዱ ሁሉ አስፈላጊ ነው ብዬ በማመን የደኅንነት መልእክት ያዘለ አራት ገጽ ደብዳቤ በመጻፍ እርሷም፣ ቤተሰቡም፣ ጎረቤቱም ደብዳቤው ሲነበብ ሰምቶ ጌታን እዲቀበሉ አደራ በማለት ከአምቦ ወደ ጌዶ ላከሁ::

የመጀመሪያ ዓመት እጋማሽ ትምህርቴን ጨርሼ እናቴን ለማየት ለእረፍት ብሄድ የእናቴ ፍቅር ያው ሆኖ አገኘሁት:: ያቀረበችልኝን ምግብ ተመገብኩና እማማ ለመሆኑ ደብዳቤዬ ደረሰሽ እልኂት:: እርሷም አዎን ደርሶኛል አለችኝ:: ታዲያ ጌታን ተቀበላችሁ ስል ተከታይ ጥያቄዬን አቀረብሁላት:: እናቴም፣ ለጄ አንተ አብደሃል በጡቶቼ ይዤህ አልነበረም፣ ለምን ኮቶሊክ ሆንክ? እኔ እወድሃለሁ፣ ግን ከዚህ በኂላ ከአንተ ጋር መሶብ ላይ አል ቀርብም፣ አንተ ያረድከውንም አልበላም አለች:: አንድ ፈጣሪና አንድ አዳኝ እያለን እውነቱን ባለመረዳት ለረጅም ዘመናት በማዕድ ላይ ተለያየን:: ይሁን እንጂ ከሰላሳ ሁለት ዓመት ጸሎት በኂላ እናቴ ጌታን ተቀብላ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሄደች:: ወገኖቼ ጌታ ቢቆይም እንኳ ጸሎታችንን ይመልሳል:: ለቤተ ሰባችሁ ደኅንነት አጥብቃችሁ ወደ ጌታ ጩኹ፣ ጸሎታችሁ ሁኔታን ይለውጣል::

በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ያሳለፍሁት ሕይወት የመጀመ ሪያው ክፍል ደስ ያሰኝ ነበር:: በሕይወቴ ይታይ የነበረው ለውጥ ለሚስዮኖቹም ሆነ በጊዜው ለነበሩ ጥቂት ምእመናን ከፍተኛ ደስታ





ሆነ:: እኔንም ተስፋ የሚጣልበት ልጅ ነው፣ በእርግጥም ጥሩ አገልጋይ ይሆናል ብለው ስላሰቡ የስብከት አገልግሎት ያስጀመሩኝ ደኅንነትን በተቀበልሁ በመጀመሪያው ወር ነበር::

ገና ያልረካ ውስጠኛው ክፍሌ ከዚህ ሌላ ሃይማኖት ይኖር ይሆን በማለት እንድጠይቅ ገፋፋኝ:: ጊዜ ሳላባክን በከተማዬ ውስጥ ያሉ ቤተ እምነቶችን ማሰስ ጀመርሁ:: መቼም በዚያ ዘመን እንደዛሬው ብዙ ቤተ ክርስቲያን አልነበረም:: በጊዜው ያገኘኂቸው የሰባተኛው ቀን አክባሪ ካህን የነበሩትን ሰው ነበር:: ካህኑን ከተዋወቅኂቸው በኂላ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች በቃላቸው ማነብነባቸው እጅጉን ያስደንቀኝ ነበር:: ደጋግሜ ላያቸው እናፍቅ ነበር ምክንያቱም እንደ እሳቸው ጥቅስ አዋቂ መሆን ስለ አማረኝ ብልሃቱን ያሳዩኛል ብዬ ተስፋ ስላደረግሁ ነበር::

በአንድ የሰንበት ዕለት ዋናው አለቃቸው ከአዲስ አበባ መጥቶ ይሰብክ ነበር:: በእርሱ ጥያቄ እኔ ስብከቱን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ እተረጉምለት ነበር:: ብዙ ከሰበከ በኂላ በመስኮት ወደ ገበያ እየተመለከተ እነዚያ ሰዎች ሁሉ ይጠፋሉ ምክንያቱም ሰንበትን አላከበሩም ሲል ውስጤ በጣም ተቆጣ:: አከታተለና እኛ አድቬንቲስቶች ብቻ ነን መንግሥተ ሰማይን የምንወርሰው አለ:: መተርጎሙን ትቼ ከየትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ነው ያነበብከው ብዬ ጥያቄ ሰነዘርሁለት:: እርሱም ዝም ብለህ ተርጉም አለበለዚያ ሌላ ተርጓሚ እጠራለሁ አለኝ:: እኔም ዛሬ ልተረጉም የመጣሁት ከመስሪያ ቤቴ ፈቃድ ወስጄ ስለሆነ ሌላ ተርጓሚ ልትሰይም አትችልም፣ ይልቅስ በገበያተኞቹ ላይ መፍረዱን ተውና ቃሉን ስበክ አልሁት:: ከዕለቱ ሰባኪ ጋር ከጉባኤውም መካከል ብዙ ጥያቄና ክርክር ተነሳና ስብከቱ በስምምነት ተቋረጠ:: እኔም እውነትን እዚህም አላገኘሁም በማለት መለየት ግዴታ ሆነብኝ::

ካህኑ ግን አድቬንቲስት ይሁኑ እንጂ የሚከተሉት የዋች ታወርን (ራሳቸውን የይሆዋ ምስክር ብለው የሚጠሩትን) ትምህርት እንደሆነ ዘግይተው ገልጠውልኛል:: ሊያስተምሩኝም ፈቃደኝነታቸውን ስለ ገለጹልኝ አውነትን በስህተት ትምህርት ውስጥ መፈለግ ጀመርሁ:: አዬ መንከራተት! የተሰጠኝን ጥናት ሁሉ እያጠናቀቅሁ ካህኑ ዘንድ እየሄድሁ ተጨማሪ የቤት ሥራ እወስድ ነበር:: ለጥቂት ወራት በተሳተፍሁበት በዚህ የስህተት ትምህርት፣ ውስጤ መረበሽ ጀመረ፤ የሚሰማኝ ባዶነት እየሰፋ ሄደ፣ ሁኔታው የበለጠ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ከተተኝ:: ምክንያቱም ዋች ታወሮች እንደሚያስተምሩት የመጨረሻ የአማኞቹ ወሮታ መንግሥተ ሰማይ መግባት ሳይሆን የሚወረሰው ምድር እንደሆነ መሰፈፍ ስለሆነ ነው::

ከእለታት አንድ ቀን ሚስጥር እናሳይሃለን በማለት ሁለት የዋች ታወር እምነት መሪዎች ከአዲስ አበባ አምቦ ድረስ መጥተው በእንግድነት ተቀብያቸው እኔ ዘንድ አደሩ:: እኔም በሚገባ ካስተናገድኋቸው በኋላ የውሸት ትምህርታቸውን ሲግቱኝ አደሩ:: በማግስቱ የተባለውን ሚስጥር ለማየት ወደ አዲስ አበባ ይዘውኝ ሄዱ:: አዲስ አበባ እንደደረስን ከመርካቶ በታክሲ ወደ ቤተ መንግሥት አካባቢ መጣን:: በእግር ባደረግነው ጥቂት ጉዞ ያኔ እስገራሚ የተባሉ ሁለት ሕንጻዎች ይሠሩ ወደ ነበረበት አካባቢ ደረስን:: አንዱ ዛሬ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ያን ጊዜ የመሬት ይዞታ ይባል ነበር::

አንድኛው ሚስጥር ገላጭ ነኝ ባይ በሕንጻው ውበት በመገረም እመልካች ጣቱን ወደ ሕንጻዎቹ ቀስሮ ወንድማችን እየህ አሕዛብ ደክመው የሚሠሩልንን ቤት አለኝ? ይኸው ነው እንዴ ተስፋችሁ? ብዬ ጠየቅሁ:: ገሮች ምድርን ይወርሳሉ የተባለውን አላነበብህም?





መልሼ መንግሥተ ሰማይ ማን ሊገባ? እርሱማ ለተወሰኑላቸው ለመቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች ብቻ ነው፤ ከእነዚህም አንዱ ኢትዮጵያዊ ሲሆን እርሱም ኤርትራ ውስጥ ነው የሚገኘው አሉኝ:: የምድር ኑሮ አሁንም ሰልችቶኛል ልታሳዩኝ ያመጣችሁኝ ሚስጥር ይህ ከሆነ ከዛሬ ጀምሮ ትምህርታችሁን ክጃለሁ አልኋቸው:: አንተ ከመንጋው ተለይተህ ወድቀሃል ሲሉ ሁለቱም ረገሙኝ:: እኔም ከመንጋው ተለይታችሁ የወደቃችሁት እናንተ ራሳችሁ ናችሁ በማለት መልስ ሰጥቼ ተዘላልፈን ተለያየን::

ወዲያው በጥድፊያ ወደ አምቦ በብዙ ቁጭት ተመለስሁ:: ለዚህ ሁሉ መንከራተት የዳረጉኝን የአድቬንቲስት ካህን ለማግኘት ውስጤ በጣም ቸኮለ:: እንደደረስሁም የሰጡኝን መጻሕፍትና መጽሔቶች ሰብስቤ ካህኑ ቤት በመውሰድ አስረከብኋቸው:: ካህኑንም እርስዎ ሚስጥር ያሳዩሃል ብለው እንዲወስዱኝ ያመጧቸው ሰዎች ግንብ ትወርሳለህ ብለውኝ በሃሳብ ሳንጣጣም ትምህርታቸውን ክጄ ወዲያው ተለያየን በማለት ነገርኋቸው:: ይህ ሁሉ ድካምና ጉዞም ግንብ ቤት ለመውረስ ከሆነ ይቅርብኝ እምነታችሁን ክጃለሁ በማለት አቋሜን ግልጽ አደረግሁላቸው::

ካህኑንም በተግሳጽ ለመሆኑ እርስዎ አድቬንቲስት ሲሆኑ ለሚበሉት እንጀራ እንዴት ታማኝ አልሆኑም? ለራስዎ የስህተት ትምህርት ውስጥ ገብተው እኔንም በማሳሳትዎ በጣም ነው የታዘብኩዎ ብዬ በጥሞና ኃዘኔን ገለጽሁላቸው:: እርሳቸውም ልጅ ሰይፉ፣ ከዛሬ ጀምሮ የዋች ታወርን እምነት እኔም ክጃለሁ አሉኝ:: የእርስዎ መካድ እኔን አይጠቅመኝም፣ እንዲያውም እግዚአብሔር የሚባል የለም ብዬ ተለየኋቸው::

ከዚሁ ውሳኔ በኋላ አገኘሁ ያልሁትም የባፕቲስቱ እምነት ከውስጤ ደብዛው ጠፋብኝ። የማዋያቸውም እንደኔው ግራ የተጋቡ ሰዎች ስለ ነበሩ ሊረዱኝ አልቻሉም። እውነትን እፈልጋለሁ ግን እውነት አሁንም በብዙ ሚልዮን ማይልስ ከእኔ ርቋል። ተስፋ መቁረጥና ጨለማ ውስጤን ከበበው። እንደኔው ግራ ከተጋባ ከጓደኛዬ ጋር ወደ ድሮው የመጠጥ ልማድ ተመለስን። ይሁን እንጂ ያም እንኳ እረፍት ሊሰጠኝ አልቻለም። እውነትን ፈልጌ ስላጣሁ ከነአካቴው እግዚአብሔር የለም ማለቱ ቀለለኝ። በዚህም በክህደት እምነት ያለ ምንም ተስፋ ጥቂት ቀናት አሳለፍሁ።

## 8.2 ዜና ጸንጠቆስጤ

ጸንጠቆስጤ የተባለ እምነት የመምጣቱ ወሬ ይነፍስ ጀመረ። ዜናው ግራ ወደ ተጋባሁት ሰው ጆሮም ገስግሶ ደረሰ። እንዲያውም ሃይማኖታቸው በር ዘግቶ ማልቀስ ነው፣ ሰው እንፈውሳለን እያሉ በሽተኛው ላይ ተቀምጠው ይደበድቡታል፣ በማያውቁት ቋንቋ ይናገራሉ የሚል ወሬ ሰማሁ። ይህን አዲስ እምነት በአምቦ ከተማ ውስጥ ከሚያካሂዱ ሰዎች መካከል አቶ መኮንን ጌታሁን ያን ጊዜ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህር የነበረ አሁን ግን በአሜሪካ አገር የሚኖር፣ ተማሪ መርዕድ ለማ ያሁኑ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ዋና ፓስተር ነበሩ።

### 1) አልቃሻው ወንድሜ

ታላቅ ወንድሜ አቶ ፈቃዱ ከበደ እንዲህ ባለ ምድረበዳ ሕይወት ውስጥ ስንከራተት ጎንደር የላቦራቶሪ ቴክኒሽያን ትምህርቱን አጠናቆ መጣ። ያኔ የመንፈስ ቅዱስ እሳት የጎንደር ሕክምና ሞያ ወጣቶችን ጎብኝቷቸው ነበር። ወንድሜም የልቅሶ ሃይማኖት የተባለው የጸንጠቆስጤው እሳት ዳሰስ አድርጎት ነበር የተመለሰው። እንጸልይ እያለ ይሰበስበንና ተንበርክከን ሳለን





ያለቅሳል። እኔና ጓደኛዬም ይህ ሰው ተበላሽቶ ነው የመጣው። በሰላም ምድር ምን ያስለቅሰዋል? ልቅሶ ምንድነው ሟርት ካልሆነ በስተቀር እንባባል ነበር።

በአካባቢያችን የልቅሶ ሃይማኖት መጥቷልና ተጠንቀቁ የሚል ወሬ ይነፍሳል። ወንድሜን በጣም የምወደው ቢሆንም የልቅሶው ጉዳይ ያስቸግረኝ ጀመር። እኔና ጓደኛዬ ከጸሎቱ ወጥተን መለኪያችንን እንጨብጥና ወንድማችን ፍቃዱ ምን እያለቀሰ ያሟርታል? ይልቅ እንደ እኛ አይደሰትም እያልን እናሾፍበት ነበር። በየምክንያቱ እንሰብሰብ እያለ ተንበርክኮ ልቅሶውን ይለዋል። ስን በረከክ ደግሞ መብራት ያጠፋል፣ ምንም አልገባንም፤ እንዲያ ውም ሊያብድ ነው እንዴ? እያልን እንፈራለት ነበር። ደግነቱ በልሳን አይጸልይም ነበር እንጂ ያንንማ ሰምተን ቢሆን ኖሮ ብዙ እንሰናከል ነበር።

### 2) የተቃውሞ ስብከት

እግዚአብሔር የለም ልበል እንጂ ቤተ ክርስቲያን መሄድ አላቆምኩም። ስለ ጴንጤዎች የምሰማው ሁሉ ያስቆጣኝ ጀመር እንዲያውም በባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተቃወምሁ መስበክ ጀመርሁ። በአንድ ወቅት ላይ ዕሁድ ጧት ለመስበክ ተረኛ ስለ ነበርሁ፣ ጓደኛዬ ሊሰብክ የሚወስደው ድፍረት የሚሰጥ ነገር እንዳለ ገልጦልኝ እኔም ያን ፈለግ እንድከተል አበረታታኝ። በእርሱ ግብዣ ማለዳ ወደ ቡና ቤት ሄድንና ሁለት ቀንዶ አረቄ አዘዘልኝ። እኔ በጧት ያውም በምሰብክበት ቀን አልወስድም አልሁት። ጓደኛዬ የተቀዳውን ድቡል ቀንዶ አንስቶ ጅው አደረገው። ፈተናው ጽኑ ስለነበረ እኔም አንስቼ ጅው አደረግሁት። ሰማይና መሬት ይገለ ባበጥብኝ ጀመረ። የአፍ ሽታ ለማጥፋት በቅድሚያ በሃርዛፍ አኝክና

ትፋው አለኝ ቀጥሎም ሜንታ ከረሜላ ብላበት ብሎ ሰጠኝ ያዘዘኝን ሁሉ አደረግሁ።

የፀሎቱ ሰባኪ እንደ ጨዋ ሰው የተቃውሞ ስብከቴን ይዤ ቀረብሁ። የፀሎቱ መልእክቴ "ሀሳዊ መሲሆችና ትምህርታቸው" በሚል ርዕስ ነበር የቀረበው። በከተማችን ገና ማልቀስ የጀመሩ እነ አቶ መኮንንና መሰሎቻቸውን ለመወንጀል ሆን ብዬ ነበር ያዘጋጀሁት። እነዚያን ወገኖች አይቻቸው እንኳን አላውቅም ነበር። በጳንጠቆስጤዎች ላይ ስድቡን አወረድሁት። እነዚያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚሰብኩትን በአረቄ ኃይል ያውም በቀንደ ተገዳደርኋቸው።

በዚያ መልእክት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን በተለይም በሚሽነሪዎች ዘንድ ብዙ አድናቆትን አተረፍሁ። እንዲያውም ቀኑ እግዚአብሔር መሬት የወረደበት ቀን ተብሎ ተለየመ። እኔ ግን የወረደውን ስለማውቅ የሚሉት ውስጤ አይገባም ነበር። ለእኔ ልዩ የማበረታቻ ግብዣ በየሚሲዮኖች ቤት ተጧጧፈ። እግዚአብሔር እንደጠራኝ ሲነግሩኝ በልቤ ያላወቃችሁት ነገር አለ እላለሁ። እንዲያውም አንተ ጌታ ጠርቶሃልና አሜሪካ አገር ልከን እናስ ተምርህና ተመልሰህ በባፕቲስት አብያተ ክርስቲያናት ፓስተር ሆነህ ታገለግላለህ ይሉኝ ጀመር። ድፍረት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ከመምጣቱ በፊት ሕይወት እንዲህ ነበር።

ቀድሞ ባፕቲስት ሚሽን አብረን እንሠራ የነበርን በኢትዮጵያ የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል ጅማሬና እድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ አገልጋይ ረጋሳ ፈይሳ (አባባ ረጋሣ እኔ ጋሼ ነው የምላቸው) ነበሩ። እርሳቸውም በዚሁ አዲስ ትምህርት ተለክፈዋል ማለትን ሰምቼ ባገኘኋቸው ጊዜ በጣም ተጣላኋቸው። ከአዲስ አበባም ሲያስተምሩ ወደ አምቦ ሲመጡ በትር ይዤ በመጠበቅ





አሳድጄ ከሰፈር አባርራቸው ነበር። በዚያን ጊዜ እኔ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሽማግሌዎች ሰበሳቢ ስለ ነበርሁ ኃላፊነትን የምወጣው በእንደዚህ ያለ መንገድ ይመስለኝ ነበር። ባደረስሁባቸው ስደት ሁሉ አገልጋይ ረጋሣ ጌታ ይባርክህ እያሉ ነበር የሚሄዱት።

ከእለታት አንድ ቀን ሰው ፖም ሰጥቶኝ ልበላ ስዘጋጅ አገልጋይ ረጋሣ አጠገቤ ስለነበሩ ለይፊ አካፍለኝ ብለው በእጃቸው ነኩብኝ። አንተ ሃሳዊ መሲህ ከዚህ አትጠፋም ብዬ በበትር አባረርኋቸው። ፖሙንም ረክሷል ብዬ በማሰብ ልጥለው ፈልጌ ነበር፣ ግን ልተካው ስለማልችል በሳሙና ሙልጭ አድርጌ አጠብሁና በላሁት። ፈሪሳዊነት ይኋችኋል ይሄ ነው።

ሥጋዊ ረሃብን በምግብ ማርካት ይቻላል፣ መንፈሳዊ ረሃብን ግን ያለ ጌታ መንፈስ በምን እናረካዋለን? እየተቃወምኩ በማስተምረው ትምህርት ሌሎች ያድንቁኝ እንጂ እኔ ውስጤ ባዶ ነበር። በተለይም መጨረሻው ላይ ፍጹም ተስፋ መቁረጥ ሕይወት ውስጥ ገባሁ። ያኔ ነበር የሃይማኖት ነገር በቃኝ ብዬ ዓለምን መቃኘት የጀመርሁት። ለሶስት ቀናት ያህል ያለ ጌታ ኖርሁ። ዓለምም ተመልሶ መጣልኝ ብላ እጇን ከፍታ ተቀበለችኝ። ሕይወት ምንም አልጥም አለኝ። በሰላም ፋንታ ረብሻ፣ በደስታ ፋንታ ኃዘን፣ በብልጽግና ፋንታ ድኅነት እንዲሁም በተስፋ ፋንታ ተስፋ መቁረጥ የዕለት ቀለቤ ሆነ። እንዲህ ባለ ቀውጢ ጊዜ ነበር መፍትሄ ፍለጋ ወደ እግዚአብሔር መለስ ብዬ እውነት ካለህ እባክህ ራስህን ግለጥልኝ እያልሁ መቃተት የጀመርሁት።

አንድ ቀን እንደኔው ግራ የተጋባ ጓደኛዬን ፍለጋ ወደ ቤቱ ብሄድ በብርቱ የማሳድዳቸው አገልጋይ ረጋሣ ሳሎን ተቀምጠው አገኘኋቸው። ሕይወቴ በመከራ ውስጥ ስለነበረች "ጋሼ ዛሬ እርስዎ ያስፈልጉኛል" አልኋቸው። ጌታ ይመስገን ብለው አገላብጠው

ከሳሙኝ በኋላ አጠገባቸው እንድቀመጥ ጋበዙኝ:: ወዲያው አልቃሻው ወንድሜ ሌሎች ሁለት ወንድሞች መጡ:: አገልጋይ ረጋሣም ለአስር ሰዓት ያህል ያለማቋረጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተማሩን:: ውስጤ በትምህርታቸው ተነካ:: በመጨረሻም ጋሼ በመንፈስ ቅዱስ እንዳልሞላ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ? ብዬ ጠየቅሁ:: በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል አሉኝ:: ወዲያው ተንበርክከን እጃቸውን ጭነው ጸለዩልን:: እውነተኛ ለውጥ በውስጤ ሲቀጣጠል ተሰማኝ:: ድንገትም የእንባ ዘለላዎች በጉንጮቼ ላይ ፈሰሱ:: የማላውቀው ደስታና ሰላም በውስጤ ፈሰሰ ነፍሴ ተረጋጋች:: ተስፋዬ በውስጤ ታደሰ ለአዲስ ነገርም ልቤ ተዘጋጀ:: ይሁን እንጂ በዕለቱ ማናችንም በልሳን አልጸለይንም::

አገልጋይ ረጋሣ የመጡበትን ሁኔታ እንዲህ ሲሉ ተረኩልን:: ትናንት ማታ ተኝቼ ሕልም አለምሁ:: ያየሁትም በአራት ጠርሙሶች ውስጥ ውኃ ስሞላ ነበር:: ሕልሙ አስጨነቀኝና በሌሊት ተነስቼ ስጸልይ፣ ጌታ ሆይ ትርጉሙ ምንድነው? ስለው ተነሳና ወደ አምቦ ሂድ አራት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ አለኝ:: እኔም መልሼ ኧ! ኡ ! ጌታ ሆይ ያ ሰይፉ እንዴት በተደጋጋሚ እንዳዋረደኝ ታውቃለህ፣ ሌላ ሰው ላክ እንጂ እኔ አልሄድም አልሁት አሉ:: ጌታም ተነሳና ሂድ እንዲያውም አንዱ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው እርሱ ነው አለኝና መጣሁ አሉ:: ወንድሜና እኔ ምንም ጊዜ ሳንወስድ በቤታችን ውስጥ ፕሮገራም አዘጋጅተን ከወገኖች ጋር መጸለይ ጀመርን::

## 8.3 የእሳት ጥምቀትና ውጤቱ

የአልቃሻው ወንድሜ ልቅሶ እኔንም ይሞካክረኝ ጀመር፣ በልቅሶው እርሱ የቀደመ ልምድ ስለነበረው ልደርስበት አል ቻልሁም:: አንድ ቀን አንድ ወንጌላዊ ከአዲስ አበባ መጥቶ





በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በልሳን ስለ መጸለይ አስተማረን:: ለሁለት ሰዓት ያህል ካስተማረን በኋላ ተንበርከኩና ልጸልይላችሁ አለ:: ብዙ ወዲያ ወዲህ እየተዘዋወረ ለሃያ ሁለት ሰዎች ጸለየልን:: እኔ ዘንድ ተመላልሶ ጸለየና ጌታ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ስለ ላክህለት አመሰግንሃለሁ ሲል እሰማዋለሁ::

### 1) የመንፈስ ቅዱስና የእሳት ጥምቀት

ወንጌላዊው ደጋግሞ በላዬ ላይ ሲጸልይና ሲያመሰግን ድንገት ተመስጦ ውስጥ ገባሁ፤ ሰውነቴንም ውርር የሚያደርግ ነገር ተሰማኝ:: ሰማይ ተከፍቶ እሳት ወደ ታች ሲመጣ በዓይኖቼ አየሁ:: እሳቱ በፍጥነት ወደታች ይገሰግሳል:: እኔም ዝም ብዬ በመደነቅ እመለከታለሁ:: የት ሊያርፍ ነው ብዬ ስጠብቅ መጥቶ አፌ ላይ አረፈ:: እኔም ወየው ተቃጠልኩ ብዬ በሁለት እጆቼ እሳቱን ለማጥፋት አፌን መጥረግ ጀመርሁ:: ብጠርግ፣ ብጠርግ የራሴ ኃይል እየከዳኝ ሄደ:: በመሬት ላይ ወድቄ ቤቱ ውስጥ እየተንከባሰልሁ መጮኽ ጀመርሁ:: ለሃያ ደቂቃ ያህል ያለ ራሴ ኃይል ነበርሁ:: ራሴን እያወቅሁ ስመጣ በልሳን እጮኽ እንደ ነበረ ተገነዘብሁ:: ሃሌ ሉያ! ልሳኑም ዲ! ዲ! ዲ! ዲ! ብቻ ነበር:: ዲ! ዲም! በእግዚአብሔር ጆሮ ትርጉም አለው ብዬ ስላመንሁ ውስጤ ሃሴት አደረገ:: ከወደቅሁበት ስነሳ ወንበርና ጠረጴዛ ሁሉ ተገለባብጦ አየሁ::

ነቅቼ ስነሳ አብረውኝ የነበሩት ሁኔታው አስደንግጧቸው ወጥተው ከአጥር ውጭ ቆመው የሚሆነውን ያዳምጡ ነበር:: እንዲህ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ለሁላችንም እንግዳ ነገር ነበር:: አንዳንዶቹም ያበድሁ መስሏቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ጸጥታ መሆኑን ሲያረጋግጡ፣ ከውጭ ወደ ቤት በመግባት ስሰጨኸቴና መንከባለሌ በጣም ተጣሉኝ:: የዚህ ዓይነት ሁኔታ ታይቶ ስለ ማይታወቅ ማንንም ያስደነግጥ ነበር:: እኔም እነዚህ ሰዎች

በወጡልኝና ያቺ ዲ! ዲ! እንዳትጠፋብኝ ጸሎት በቀጠልሁ ብዬ በልቤ አሰላስልሁ:: ጸሎቴ ተሰማ እነርሱም ከቤቱ አንድ በአንድ ወጥተው ሄዱ::

ጸሎት ክፍሌ ገብቼ ያቺ ዲ! ዲ! አለች ወይስ ጠፍታለች ብዬ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ መጸለይ ጀመርሁ:: ትንሽ እንደቃተትሁ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ተንቀሳቀሰ ዲ! ዲዋ! መጣች:: ሃሌ ሉያ! ከሶስት ሰዓት ጸሎት በኋላ እኩለ ሌሊት ላይ ዲ! ዲ! ተለውጣ *ፕራስኮራሀ ማሳ! ሃዶናይ! ኪለይዳ! ሁ ማሬይስ!* ማለት ጀመርሁ:: እንዲሁ በልሳን ስጸልይ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሆነ:: ሃሌ ሉያ! የውስጤ ደስታና ሰላም ልገልጸው ከምችለው በላይ ከፍ ያለ ሆነ::

እውነትም ጰራቅሊጦስ በአጠገብ የሚቆም የእውነት መንፈስ መሆኑን ተረዳሁ:: የጸሎት ሕይወቴ በአንድ ጊዜ ከማደጉ የተነሳ ሌሊት ተንበርክኬ ማደር አዘወትር ጀመር:: የነፍሳት ፍቅር በውስጤ እንደ እሳት ተቀጣጠለ:: በጸሎቴም ውስጥ እነዚያ ወገኖቼን እሳት ሲወርድብኝ ሁኔታዬን መረዳት ያቃታቸውን ጌታ ሆይ በእሳትህ አጥምቃቸው እያልሁ ስለ እነርሱ መቃተት ቀጠልሁ:: ለእኔ እግዚአብሔር መሬት የወረደበት ቀን ሚሽነሪዎቹ እንደመሰላቸው ቀንዶ ጠጥቼ በጴንጤዎች ላይ በለበክሁበት ቀን አልነበረም:: በእርግጥ እግዚአብሔር መሬት የወረደልኝ የመንፈስ ቅዱስ እሳት በላዬ ላይ በፈሰሰ ቀን ነበር:: ሃሌ ሉያ! ዛሬም ባለመረዳት የምታሳድዱን ወዳችሁ አይደለም፣ እውነቱ ስላል በራላችሁ ነው:: እኛ ደግሞ ለእናንተ ያለን አንድ ነገር ብቻ ነው:: እንወዳችኋለን! እንወዳችኋለን! እንወዳችኋለን! ይኸው ነው::

አንድ ቀን ስለወገኖቼ ስጸልይ ጌታ ሰብስባቸውና ስለመንፈስ ቅዱስ አስተምራቸው እኔ እሞላቸዋለሁ አለኝ:: በእኔ ሁኔታ የተደናገጡ ወገኖቼ ሁሉ በአንድ ሳምንት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ





ተሞሉ:: የጰንጠቆስጤው እሳት ተዛመተ ሁላችንም ማልቀስ ቀጠልን:: በአውራጃችን በየትምህርት ቤት ተቋማት የእሳቱ ወላፈን ብዙ ወጣቶችን አቀጣጠለ:: ሃሌ ሉያ! የቃልቻ የማምለኪያ ሥፍራዎች ሁሉ ኃይላቸውን አጡ:: የገጠሩ ሕዝብ ሁሉ ምርመራ አድርጉልንና ሰይጣን አውጡልን ብሎ የሚመጣው እኛ ዘንድ ሆነ:: ወንጌላችን በኃይልና በሥልጣን አካባቢአችንን አዳረሰ:: የጌታ ዝና በየሥፍራው ወጣ:: ሃሌ ሉያ!

## 2) አጋንንት ማባረር

አንድ ዕሁድ ከሰዓት በኋላ አስራ ሁለት ወንድሞችና እህቶች በትንሽ ክፍል ውስጥ ተሰብስበን እንጸልይ ነበር:: የጸሎቱ ጊዜ ለእኛ ው እንጂ ለውጪ ሰው አልነበረም:: ጸሎታችንን ጨርሰን ስንነሳ ሁለት ከገጠር የመጡ በዕድሜአቸው ጠና ያሉ፣ ወንድና ሴት መካከላችን ተቀምጠው አየን:: እኛም መዝሙር እየዘመርን እያለን አጋንንት ከሰውየው ውስጥ ጮኸ:: ከዚያ በፊት አጋንንት አው ጥተን አናውቅም ሌላም ሰው ሲያስወጣ አላየንም:: መንፈስ ቅዱስ ወንድሜንና እኔን ሰውየው አጠገብ ወሰደንና ራሱ ላይ እጃችንን ጭነን ማን ነህ አንተ? ስንለው የሰይጣን ስም ነገረን:: ስንት ናችሁ? ብንለው ሁለት ነን አለ::

ወዲያው ሚስቱ ውስጥ ያለው ጮኸ:: ሰውየውን ትተን ወደርሷ ሮጥን በጣም ያስቀዝፉት ነበር:: ስንት ናችሁ? ብንል አምስት መቶ ነን አለ፤ ሌላ ተጨማሪ አጋንንት አለመኖሩን በመሃላ አረጋግጠን አምስት መቶውን ወደ ጥልቁ እንዲሄዱ አዘዝናቸውና ሴቲቱ ተፈወሰች:: ወደ ባሏ ተመልሰን አጋንንቱን ማነጋገር ጀመርን:: ሚስቱ ውስጥ ያሉት በሙሉ ወጥተዋል አንተም ቁጥርህን ተናገርና ውጣ አልነው:: መናፍስቱም አርባ ነን ሲሉ ለፈለፉና በታላቅ ኃይል ጮኸው ወጡ::

በኋላ ነፃ የወጡትን ሰዎች ከየት እንደመጡ፣ ወደየ ማን እንደመራቸው ጠየቅናቸው። ሰውየው ቃልቻ እንደነበረና ሰይጣን የነበረውን በጎችና ፍየሎች እያሳረደ ከጨረሰ በኋላ እግሩንና እጁን አስሮት በአልጋ ላይ እንዳስቀረው ተረከልን። በኋላ ሰው የሚፈውሱ አሉ ብለው ስለነገሩን ጎረቤቶች በፈረስ ላይ አስቀምጠው አምጥተውን ተመልሰው ሄዱ አሉን። ስለ እኛ ለእነርሱ የነገራቸው ማን ነው ብለን ብንጠይቅ? ማን እንደነገራቸው አናውቅም ብቻ ሰው የሚያድኑ አሉ አሉን ብለው ተረኩልን። ሰዎቹም ወደ ቤታቸው እንደማይመለሱና እኛ ዘንድ መኖር እንደሚፈልጉ ነግረውን ቤት ተከራይተን አስቀመጥናቸው። በሌላ ጊዜም ሠፈራቸው ድረስ በመሄድ ሰይጣንን የሚያመልኩበትንና የሚሰዉለትን ጎጆ አፈ ራርሰን ተመለስን። ሁለቱም ወገኖቻችን በጌታ አድገው ላልዳኑ ሰዎችም ምስክርነታቸውን እየሰጡ ኖሩ። ጌታ ይመስገን!

## 3) ተሰቦው አጋንንት ሆኖ ተገኘ

በነበረን ጨቅላ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ላይ ሆነን አንዲት ሴት በከፍተኛ ትኩሳት ታመመችና ወደ ሆስፒታል አምጥተዋት ተስቦ እንዳለባት በደም ምርመራ ተረጋገጠ። ሐኪሙም ለተስቦ የሚሆን መድኃኒት ሰጥተዋት ወደ ቤቷ ሄደች። በጠና ታማ ስለነበረ ማታ ልንጠይቃት ቤቷ ሄድንና ጸሎት ተጀመረ። ወዲያው ከውስጧ አጋንንት ጮኸ። እኛም በኢየሱስ ስም ተፋልመን ቁጥሩንም ጠይቀን አስወጣነው። ወዲያው ትኩሳቱና የህመም ስሜቶች በሙሉ ለቀቃትና ተነስታ መዘዋወር ጀመረች። ጌታ ጤናዋን እኛ እዚያ እያለን መለሰላት። አሜን! ሃሌ ሉያ!

በማግስቱም መድኃኒቱን ሳትወስድ ሄዳ ብትመረመር ተስቦው ከሴቲቱ ውስጥ ተነቅሎ ሄዷል። አሜን! የጥንቱን ሃይማኖት ስጠን! ሐኪሙም በጣም ተገርመው በተስቦና በአጋንንት መካከል ያለውን



ግንኙነት ጠየቁን። እኛም በጊዜው በገባን መጠን በሽታ ያው የአጋንንት ሥራ ነው አልናቸው። ሐኪሙ ቤተ እምነታቸው ባይቀበለውም ጌታ በእኛ ውስጥ የሚሠራውን ነገር በአክብሮትና በሰላም ማስተናገድ ጀመሩ።

## 4) ዲዳዋ ተናገረች

ዲዳዋን ወጣት ወላጆቿ ወደ ፈውስ ፕሮግራማችን ይዘዋት መጡ። በጸሎት ሰዓት ችግሯን ሲነግሩን ለዓመታት ተናግራ እንደማታውቅ ገለጹልንና እባካችሁ ፈውሱልን አሉ። አገልጋዮች ተሰብስበን ጸለይንላት። አጋንንት እንደብራቅ ከውስጧ ጮኸ። ተናግራ የማታውቀውን ከረዳ ይዟት የነበረው ለካስ አጅሬ ነበር። በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ቀንድ ቀንዱን ሰባብረን አወጣነው። ዲዳዋም በቅጽበት ተናገረች። አፍላ ጴንጤ በነበርሁበት ጊዜ የታምራት ክስተቶች እንዲህ ይመስሉ ነበር። ጌታን በጣም አመሰግናለሁ አሁንም ከአፍላው ሕይወት የበለጠ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። የመንፈስ ቅዱስ እሳት እየጋለ እንጂ እየቀዘቀዘ አይሄድም! ለማጋልም ሆነ ለማብረድ ውሳኔው የየግለሰቡ ነው!

## 5) ምርመራ አድርጉልን

የጌታ ዝና በየከተማውና በየገጠሩ ወጣ። ሕዝብ እየጎረፈ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በመምጣት ሰይጣን እንዳለብንና እንደሌለብን ምርመራ አድርጉልን ይሉን ጀመር። ምርመራ ማድረጉና አጋንንት መፋለሙ ዕለታዊ ተግባራችን ሆነ። ጌታም በተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች ስለባረከን የሚታየው ታምር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ሄደ።

በአውራጃችን ውስጥ የራሱን የደመራ በዓል በዓመት አንዴ ያከብር የነበረ በጣም የታወቀ ቃልቻ ነበር። በዚያ በዓል ላይ ስፍር

ቀጥር የሌለው ሕዝብ በዓሉን ለማክበር እንደሚሰበሰብ ይነገራል። እኛም የደመራው ጊዜ ሲቃረብ አንድ ሳምንት ያለምንም ምግብና ውኃ በጾምና ጸሎት ላይ ቆየን። ፍልሚያችን የሚያከትመው ቃልቻው የሚያመልክበት ሥፍራ ድረስ በመሄድና ከውስጡ አጋንንት በማውጣት ነው ብለን ወሰንን። በጾማችን ማብቂያ ቀን ላይ እሁድ ጧት አስራ ሁለት የምንሆን የጾሙ ተሳታፊዎች፣ ሶስት ሰዓት የእግር ጉዞ በማድረግ ቃልቻው ማምለኪያ ሥፍራ ደረስን።

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመንፈሳዊ ጦርነት ላይ ያስልፋል። እዚያ እንደደረስንም በር ጠባቂው ትልቅ ጦር ይዞ መጣና ምን ትፈልጋላችሁ ከማን ጋር ተጣልታችሁ መጣችሁ? አለን። እኛም የግለ ሰቡን ስም በመጥቀስ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣሉትን ልናስታርቅ ነው የመጣነው ብለን መለስን። እርሳቸው በቅርቡ ከንጉሡ ሹመት ስላገኙ ግብር ሊያገቡ ሌላ ማምለኪያቸው ዘንድ ሄደዋል አለን። ተስፋ መቁረጥ በውስጣችን ተሰማን። ይህ ሁሉ ጾምና ጸሎት፣ ይህ ሁሉ የእግር መንገድ ብለን ስንተክዝ ጌታ በመገለጥ ከመናፍስቱ እንጂ ከሰውዬው ምን አላችሁ? ሲል ተናገረን። ዘበኛውን ቤቱ ውስጥ እንዲያስገባን ፈቃድ ጠየቅንና እየተዘዋወርን ለረጅም ሰዓት በልሳን ጸለይን። አጋንንት ሁለተኛ እንዳይመጣ በሰውዬው ላይም እንዳያርፍ አዘዝንና ወደ ቤታችን ሄድን።

ባለ ውቃቢው በደመራ በዓሉ አከባበር ላይ በብዙ ሺህ ከሚቆጠር ሕዝብ ጋር በዓሉን ለማክበር ተሰብስበዋል። እለቱ ሳምንታዊ የሪቫይቫል ስበሰባችን ምሽት ቅዳሜ ማታ ነበር። እኔ በብዙ ሕዝብ መካከል ቆሜ እየሰበክሁ እንዳለሁ ድንገት የቤተ ክርስቲያናችን ግቢ በፈረሰኛ ተጥለቀለቀ። ሁኔታውን በመስኮት





እየቃኘሁ ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ጀመረ። አልዋሽም ሰውዬው ሊያሳፍነን ነው ብዬ ፍርሃት ይዞኛል።

ከፈረሰኞቹ አንዱ በዕድሜ የገፉ አዛውንት መንገድ ልቀቁላቸው እየተባለ በሩን አልፈው ገቡና ከፊት ስፊቴ ለጥ ብለው መሬት ሳሙ። ጥቂት ተራምደው በመደጋገም ሶስት ጊዜ መሬቱን ሳሙ። እኔም ስብከቴን አቁሜ ሁኔታውን እከታተል ነበር። አጠገቤ ደረሱና አቶ ሰይፉ ማለት አንተ ነህ አሉኝ እኔም አዎን አለሁ። ፍቀድልኝ አምላካችሁ ያደረገውን ልናገር አሉ። ትንፋሼ መለስ አለና ቆዩ ስብከቴን ልጨርስ አልኋቸው። አጭር የደህንነት መልእክት ካቀረብሁ በኋላ አዛውንቱን ይምጡ ይናገሩ አልኋቸው።

በዓሉን ለማክበር ሄደው የነበሩ እኚሁ የሰማንያ ዓመት አዛውንት ስሜ አባ ተንኮል ይባላል ብለው አስተዋወቁ። በመቀጠልም በስይጣን በዓል ላይ የደረሰውን ቅሌት ሲተርኩ፣ የውቃቢው መንፈስ በቃልቻው ላይ አልወርድበትም አለ። እርሱም ብዙ በሬዎችን አሳርዶ እምቢ ቢለው ተነስቶ ረገመን። ኮቶሊኮች ዘንድ ስለሄዳችሁ አምላካችሁ ከዚህ በኋላ ሊፈርድላችሁ አይመጣም ብሎ አሰናብቶናል። አሁንም የእናንተ አምላክ ማሸነፉን በገዛ አፉ ስለመሰከረ ይህን ሁሉ ሕዝብ ይዤ ለምርመራ መጥተናል። አሁንም ምርመራ አድርጉልንና ሰይጣን ካገኛችሁብን አውጡልን፣ ነጻ ናችሁ ካላችሁንም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንደምናምን ንገሩንና እንሄዳለን አሉ።

አባባላቸው በጣም እየደነቀን ምርመራው በብዙ ውንድሞች ተሳትፎ መካሄድ ጀመረ። ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ የጀመርን ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ጨረስን። በዚያ ሌሊት ብዙ ሰዎች ከአጋንንት እስራት ተፈቱ። ሃሌ ሉያ! ከዚያ በኋላ ከገጠር ወደ ቤተ

ክርስቲያኖችን የሚመጡ ሁሉ ለምርመራ ነው የመጣነው ይሉን ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እኔም እስከዛሬ ድረስ በተለይም ገና ጌታን በተቀበሉት ላይ ምርመራ አካሄዳለሁ:: ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን:: ሃሌ ሉያ!

## 6) የሰይጣን መድኃኒት

ወንጌላችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሰበክ የጌታ ዝና በየገጠሩ ወጣ:: በተለይም አንድ ማንበብና መጻፍ የማይችል ግን የሚመሰክር ሰው በወንጌላዊነት ላክን:: እርሱም ካስተማረ በኋላ ኑ ምርመራ ላድርግላችሁ ይልና አንበርክኮ በእያንዳንዱ ሰው ራስ ላይ መጽሐፍ ቅዱሱን ያስቀምጣል:: በእንዲህ ያለ የሞኝነት ሥራ አጋንንት ራሳቸውን እየገለጡ ይወጣሉ:: ወንጌላዊው መናፍስትን ከሰዎች ውስጥ ሲያባርር ብዙ የገጠር ሰዎች አዩ:: እነርሱም በበኩላቸው በየክልላቸው በታመሙ ሰዎች ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ራሳቸው ላይ ማስቀመጥ ጀመሩ ህመምተኞቹ ይፈወሱ፣ አጋንንትም ይወጣላቸው ጀመር::

ከእለታት አንድ ቀን በከተማው ውስጥ ብቸኛ ወደሆነው የክርስቲያን መጽሐፍት ቤት መጡና የሰይጣን መድኃኒት እንፈልጋለን ሽጡልን አሉ":: የመጽሐፍት ቤቱ ባለቤትና እኔ በአንድ ላይ ምንድ ነው የሰይጣን መድኃኒት? ብለን ጠየቅን:: እነርሱም ይኼ ዙሪያውን ቀይ የሆነ ትልቅ መጽሐፍ ነው አሉ:: ያኔ ቀይ ቅቡ ቀርቶ ነጭ ነበር የነበረው:: ባለ ሱቁም ያሰውን መጽሐፍ አምጥቶ ሰጣቸው:: አይ ይሄ አይደለም ያኛው ዙሪያውን ቀይ ነው አሉ:: ማንበብ ስለማይችሉ አንድነቱን ሲያውቁ አልቻሉም:: ለመሆኑ ምን ልታደርጉበት ነው የፈለጋችሁት አልናቸው፣ የሰጡን ምላሽ አስገራሚ ነበር:-

- ✓ በሰው ራስ ላይ አስቀምጠን ሰይጣንን እናባርርበታለን::





- ✓ ማታ ራስጌ እናስቀምጥና እንተኛለን ቅዠት ወደ እኛ አይደርስም::
- ✓ ከብቶች ሲታመሙ ራሳቸው ላይ አስቀምጠን "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" እንላለን ከብቶቻችን ይፈወሳሉ::
- ✓ ጎተራ ውስጥ እናስቀምጠዋለን አይጥ እህላችንን ሲበላ አይመጣም አሉ::

ይህን የሰይጣን መድኃኒት ካገኘን ወዲህ ሰላም አገኘን በልተን ጠገብን:: ለሰፈሩ ያሰን አንድ ብቻ ነው እባካችሁ አሁንም እርሱን ስጡን አሉ:: በውስጡ ያለው ቃል አንድ ነው ውሰዱና ይህን ሞክሩት፣ ከዚህ በፊት ያኛው ያደረገውን ካላደረገ መልሱና አምጡ ገንዘባችሁን እንመልሳለን አልናቸው እነርሱም እሺ ብለው ሄዱ::

ከዚያ በኋላ በአካባቢያችን የመጽሐፍ ቅዱስ ስም "የሰይጣን መድኃኒት" ይባል ጀመር:: ይህን ሁሉ ያደርግ የነበረው የሞኝነት እምነታችን ነበር:: በዚያ ጨቅላነትና የሞኝነት እምነት ጊዜ ጳራቅሊጦስ እንዲህ የመሳሰሉ ሥራዎችን ያደርግ ነበር:: አሜን! ጌታ ዛሬም ወደዚያ የሞኝነት እምነት መልሰን!

## 7) በመንፈስ መነዳት

ጳራቅሊጦስ ወደ ልባችን የመጣው ለዘላለም በውስጣችን ከእኛ ጋር ሰመኖር ነው /ዮሐ. 14:17/:: በውስጣችን ሲኖር ደግሞ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚሠራው በምዕራፍ አራት ላይ በሰፊው ተጠቅሷል:: ከእነዚህም አንዱ መምራት ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስ መንፈስ የሚሄድበትንና መሄድ የሌለበትን አቅጣጫ ይነግረው ነበር /ሐ.ሥ. 16:6-7፣ 9-10/:: በመንፈስ ስንመላለስ እኛ ንም መንፈስ ቅዱስ ይመራናል:: እኛ የማናየውን እርሱ ያያል፣ አሜን ዛሬም ይንዳን!

## ተመለሱና ጸልዩ

ከእለታት አንድ ቀን ተሰብስበን ቃሉን ስናጠና ስንጸልይ ዋልን፡፡ ደክምክም አለንና ነፋስ እንቀበል ብለን በከተማችን ባለቸው አንድ ብቸኛ መንገድ ከወንድሞች ጋር እየተጨዋወትን ወደ መሃል ከተማ ሄድን፡፡ ድንገትም እንደ መብረቅ ብልጭ አለና ሰማይ ሲከፈት አየሁ፡፡ እዚያው መንገድ ላይ በጊዜው በነበረኝ የልዩ ዓይነት ልሳን ስጦታ ጮኽኩና ተናገርሁ፡፡ ትርጉሙም "ሰማይ ተከፍቶ አያለሁ ተመለሱና ጸልዩ ብዙ በረከት ይጠብቃችኋል" የሚል ነበር፡፡ ወዲያውም አቶ ረጋሳ ሰይፈ ዛሬ ጌታ የጸጋ ስጦታ ሊሸልመን ነው እንሂድ አሉና ተመልሰን ጸሎት ቀጠልን፡፡

ጸሎታችን በታላቅ ተመስጦ ረዘም ላለ ጊዜ ተካሄደ፡፡ በመሃከላችን ራእይ የምታይ ትንቢትም የምትናገር እህት ነበረች፡፡ ተነስታም ጌታ ለአንተ እንዲህ ያለ ስጦታ ሰጥቶሃል እያለች የምታየውን ራእይ እየተነተነች ለእያንዳንዳችን ተናገረች፡፡ የዚያን ዕለት የተቀበልኋቸው ሶስት የጸጋ ስጦታዎች ነበሩ፡፡ እነርሱም እስከዛሬ ድረስ ከተጨመሩልኝ ሌሎች ካሪዝማታ ጋር በውስጤ ይሠራሉ፡፡ ወገኖቼ፣ ዛሬም ጸራቅሊጦስ ይንዳን! ይቀባንም! አሜን!

## ልብሴን ሌባ ወስዶታል

ያን ጊዜ በምኖርበት ከተማ አምቦ ውስጥ ላውንደሪ አልነበረም ልብስ የማሳጥበው አዲስ አበባ እየላክሁ ነበር፡፡ አገልጋይ ረጋሳ ሊያገለግሉን መጥተው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ላውንደሪ እንዲያስገቡልኝ ሁለት ሙሉ የሱፍ ልብስ ሰጠኋቸው፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስ ልብስህን ሌባ ወስዶታል ሂድና ልብስ ግዛ አለኝ፡፡ ይህ ዕውቀትን መናገር የሚባለው የመገለጥ ስጦታ ነው፡፡





እንዲህ ያለው ሁኔታ ጉድለት ቢሆንም፣ ያኔ ደስ የሚለን መንፈስ ቅዱስ መናገሩ ነበር፡፡ እኔም ሁኔታውን በጣም ተቀራርበን ስምንሠራ ሚሽነሪ ነገርኋቸው፡፡ እርሳቸውም በጣም ተቆጡና እኔ የእናንተ የጰንጠቆስጤዎች ነገር ነው የሚያናድደኝ፡፡ አንድን ሁኔታ ሳታረጋግጡ እንዲህ ሆነ ጌታ ነግሮኛል ትላላችሁ ብለው በማ በሻቀጥ ተናገሩኝ፡፡ እኔም የጌታ መንፈስ ልብሴን ሌባ እንደወሰደው በእርግጥ ነግሮኛል አልኋቸው፡፡ በጣም ተከራከሩኝና እንዲያውም በዚህ ዘመን እንዲህ ያለ ድምጽ አይተላለፍም አሉኝ፡፡ አስከትለውም ነገ ወደ አዲስ አበባ እሄዳለሁ እግረ መንገዴን ጋሼ ረጋሳ ዘንድ ሄጄ ልብስህን አመጣልሃለሁ አሉኝ፡፡ የሌለውን ከየት ያመጣሉ? እኔ እኮ ልብሴ ቢጠፋ ለእኔ ጉድለት እንደሆነ አውቃለሁ፣ ግን ልብሴ የለም ስለዚህ ይርሱት እባክዎን አልኋቸው፡፡

የታዘዝሁት ሂድና ልብስ ግዛ ስለነበረ ቅዳሜ ቀን ወደ አዲስ አበባ ሄድኩኝና አገልጋይ ረጋሳን አገኘኋቸው፡፡ እሳቸውም መጽሐፍ ቅዱስ ከፍተው ኢዮብ ላይ ለማንበብ ተዘጋጁ፡፡ ጋሼ ምንም የሚያጽናና መልእክት አያስፈልገኝም፡፡ እኔ ጌታ አጽናንቶ ነው የላከኝ አልኋቸው፡፡ ምንድን ነው የምትለው? አሉኝ፡፡ ልብሴን ከእጅዎ ሌባ እንደወሰደብዎ ጌታ ነግሮኛል ስላቸው ሁለታችንም ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደብንና በየልሳኖቻችን ጮኽን ጸልየን ጌታን አመሰገንን፡፡

አዎን ነገሩ እውነት ነበር፡፡ ገና አዲስ አበባ ሲገቡ ነበር ሌባ ከአገልጋይ ረጋሳ እጅ ልብሴን የመነተፈው፡፡ አሁንም እንሂድና ልብስ እንግዛ ብያቸው ወደ ፒያሳ ሄደን ቆንጆ ቆንጆ ልብሶች ገዛሁና ተመለስሁ፡፡ ሚሽነሪውም ሁኔታውን ባረጋገጡ ጊዜ ተደናገጡ፡፡ እንዴት ነው የሚሆነውን ነገር የምታውቀው? አሉኝ፡፡ እኔም ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሰፊው አብራርቼ አስረዳኋቸው፡፡ ይህ ስጦታ ዕውቀትን መናገር የሚባል ሲሆን ግለሰቡ በአካባቢው

ሳይኖር ወይም በርቀት ያለውን ሁኔታ በመንፈስ መረዳትን የሚያገኝበት ነው። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን። አሜን!

ከላይ የገለጽኋቸው በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመገብኘቴ በፊትና በኋላ የነበረውን የሕይወቴን ሁኔታ ነው። ገና ከወጣትነቴ ጀምሮ የነበረው መንፈሳዊ ረሃቤ የመጨረሻ ርካታ ያገኘው መንፈስ ቅዱስ በላዬ ከወረደ በኋላ ነው። በቅድመ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጴንጤዎችን አልቃሾች እያልሁ አሳደድሁ፡ ልቅሷቸው ግን እኔንም የጸንጠቆስጤው እሳት ትሩፋት ተካፋይ አደረገኝ። እኔም ልቅሶው ውስጥ በመግባቴ በተራዬ በብዙ ስደትና መከራ ውስጥ አለፍሁ። ከዳንሁባትም ቤተ ክርስቲያን ተሰድጄ ነበር የወጣሁት። ያ! የጥንቱ ልቅሶ በሚልዮን የሚቆጠሩ ወገኖችን አፈራ። ዛሬም ለጠፉት እናልቅስላቸው። የተስፋው ቃል በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና /ሐ.ሥ. 2፡39/።

በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የገለጽኋቸው ድንቆችና ታምራቶች በአፍላው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሰሞን የተደረጉትን ለመግለጽ እንጂ ጰራቅሊጦስ አብሮኝ በቆየባቸው ዘመናት ያደረጋቸውማ ተወስተው አያልቁም። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን። አሜን! ወገኖቼ እውነት እንግዲህ ጰራቅሊጦስ ነው። ከቅድመ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በፊት ያሳለፍኩትን እርካታ ቢስ ሕይወት በምዕራፉ ውስጥ ገልጫለሁ እሳቱ ከመጣ ወዲህ ግን ወይ ንቅንቅ ወይ ፍንክች። ይህን ስል ፈተና አልደረሰብኝም አይደለም የምለው። ይሁን እንጂ በፈተናዬ ሁሉ ድል እየሰጠኝ፣ ስወድቅ እያነሳኝ፣ እሳት እሳት እያለ እያስጮኸኝ ጌታዬ አቁሞኛል። አሁንም ምን ትጠማለህ ብትሉኝ፣ መልሴ እሳት ነው! ሃሌ ሉያ!

አንተስ ምን ትጠማለህ? አንቺስ እህቴ? የጰራቅሊጦስ መምጣት የተጠማን ለማርካት፣ ምድረ በዳ የሆነን ሕይወት





ለማለምለም፣ ሃዘንን ወደ ደስታ ለመቀየር፣ በውስጥህ አብሮ ለመኖርና ቀብቶ ሊጠቀምብህ ነው። ባላችሁበት ሥፍራ ሆናችሁ ጥሩት እሳቱ ይጎበኛችኋል። መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ!

9

# የመገለጥ ሚስጥር

መገለጥ ማለት ሽፋንን ማንሳት ክርስቶስ በአሕዛብ ላይ የነበረውን የጨለማ ሽፋን እንደገፈፈ ማለት ነው /ሉቃ. 2:32/:: [6]የግሪኩ ቃል "አፖካሉፕሲስ" የሚል ሲሆን አሕዛብን ሸፍኖ የነበረው መጋረጃ መገፈፍ ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር ዕውቀት ወደ ሰው ሲተላለፍ ማለት ነው /ኤፌ. 1:17/:: ሌላው የግሪክ ቃል ደግሞ "ጌላ" የሚል ሲሆን ትርጉሙም ተሸፍኖ የነበረውን መግለጥ፣ ሚስጥር ሆኖ የነበረው ሲተነተን ማለት ነው::[7] የእግዚአብሔርን አእምሮ በመግለጥ ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ መስጠት /1 ቆሮ. 14:6-26/:: ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ተቀበለው ምሪት ማለት ነው /2ቆሮ. 12:1-7/::

መገለጥ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውስጥ የሚካተት ጠቃሚ ርዕስ ነው:: ብዙ ሰዎች መገለጥን ይፈሩታል:: አንዳንዶችም ከፍርሃታቸው ወይም በርዕሱ ላይ ባላቸው ውሱን ዕውቀት ምክንያት ከጥንቆላ ሥራ ጋር ሊያዛምዱት ይሞክራሉ:: እግዚአብሔር ቃሉን የሰጠን ሙሉ በሙሉ ተቀብለን ሥራ ላይ

---

[6] Vine's Expository Dictionary of New Testament. (Lynhburg, VA, The Old-Time Gospel Hour, 1952.) 974.
[7] Young's Analytical Concordance to the Bible. (Grand Rapids, Michigan. WM Erdmans Publishing Co., 1975) 814.

እንድናውለው እንጂ በዓለም ዕውቀትና ፍልስፍና እንድንተረጉመው ወይም አላስፈላጊ ነው ብለን እንድንጥለው አይደለም::

ስለ መንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የተነበየው ኢዩኤል በመጨረሻው ዘመን ስለሚሆኑ ነገሮች በግልጥ ያስረዳናል:: በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሲፈስስ የሚገለጡ ክስተቶች *"ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌቻችሁ ህልምን ያልማሉ፣ ጎልማሶቻችሁም ራእይን ያያሉ"* (ኢዩ. 2:28) ይላል:: ይህ ትንቢት ፍጻሜ ባገኘበት ዕለት ሐዋርያው ጴጥሮስ ካቀረበው የመልእክቱ ክፍል ውስጥ ኢዩኤልን መጥቀሱ ይታወቃል /ሐ.ሥ. 2:16/:: እርሱም የተናገረው በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ አማኞች ስለሚገለጥላቸው ሁኔታ ነው::

መገለጥ ኤሎሂም ለግለሰብ፣ ለቤተሰብ፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሕዝብ መመሪያ የሚሰጥበት መንገድ ነው:: እግዚአብሔር በእነዚህ መንገዶች ድምጹን እያሰማ ፈቃዱን ለሰዎች የሚያሳውቅበት መንገድ መገለጥ ይባላል:: የዕብራውያን ጸሐፊ እግዚአብሔር ለአባቶቻችን በጥንት ዘመናት በተለያየ መንገድ እንደተናገረ ይገልጽልናል /ዕብ. 1:1-2/:: መንፈስ ቅዱስ ለጌታ ልጆች የሚናገርበት በርካታ መንገዶች አሉት:: በተለይም ፈቃዱን የሚያስታውቅበት፣ የሚያስፈልገንን ስለ መስጠት፣ ስለ ጥበቃና ምሪት ለመስጠት በሕልም፣ በራእይ፣ በተምሳሊቶች ይናገረናል::

ያዕቆብ ወንድሜ ይገለኛል ብሎ ፈርቶ ወደ አጎቱ ቤት ወደ ሦርያ ሲሸሽ በበረሃ ውስጥ አደረ:: በውድቅት ሌሊት በተኛበት ሥፍራ በሌሊት ራእይ (ህልም) ታላቁን አምላክ (ያህዌን) ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየው:: መላእክትም ምድር ላይ በተተከለው መሰላል ሲመላለሱ አየ:: የአብርሃም አምላክ እንዲህ ሲል ተናገረው:-

> *"የተኛህባትን ምድር ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ ዘርህ እንደ ምድር አሸዋ ይበዛል በምዕራብና በምስራቅ በሰሜንና በደቡብ ትሰፋለህ የምድር አሕዛብ ሁሉ*





> *በአንተና በዘርህ አማካኝነት ይባረካሉ:: ... ወደዚህችም ምድር እመልስሃለሁ"* (ዘፍ 28:13-15)::

ዛሬም ኢዩኤል እንደተነበየው በመጨረሻው ዘመን ላይ ላለን አማኞች ጸራቅሊጦስ በህልምና በራእይ ይገልጥልናል::

## 9.1 መገለጥ በሕልም

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስለሚናገርባቸው አያሌ መንገዶች መጽሐፈ ኢዮብ ላይ የተመዘገበውን ብናነብ:-

> *"እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናግራል ሰው ግን አያስተውለውም በሕልም በሌሊት ራእይ አፍላ እንቅልፍ በሰዎች ላይ ሲወድቅ ... የሰዎችን ጆሮ ይከፍታል"* (ኢዮ. 33:14-16)

ይላል:: ስለሆነም ጌታ ሃሳቡን የሚገልጥበት አያሌ መንገዶች አሉት::

ዮሴፍ ገና የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት በነበረ ጊዜ ሕልም አለመ:: ሕልሙም ክብዙ ዘመን በኋላ ፍጻሜ አገኘ /ዘፍ. 42:5-11/:: ዮሴፍ ያየው ሕልም ለመፈጸም አስራ ሦስት ዓመት ቢወስድም አልቀረም ተፈጽሟል:: ሕልሙ ሲፈጸም ደግሞ ወንድሞቹ ብቻ አይደሉም ግብጻውያንና እህል ለመሸመት ከአካባቢውና ከሩቅ አገሮች የመጡ ሕዝቦች ሁሉ ሰግደውለታል::

የእግዚአብሔር ሰው ዳንኤል ሕልምን በማየትና በመተርጎም ከፍተኛ ስጦታ የነበረው ሰው ነበር /ዳን. 7:1/:: ሌላው ቀርቶ ንጉሥ ናቡከደናፆር ያየው ሕልም ጠፍቶበት ትርጉሙን ጭምር ሕልሜን ያላመጣ ይገደላል ብሎ ትእዛዝ አወጣ:: ዳንኤል ሕልሙን

ከነትርጉሙ ለማምጣት ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ከብዙ ጸሎት በኋላ "*ለዳንኤልም ሚስጥሩ በለሊት ተገለጠለት*" (ዳን. 2:19) ይላል።

ጌታ ሕልምን ከአደጋ ለማዳን ሲል ይሰጣል። የጌዲዎንን ሕይወት ብንመለከት ከኤሎሂም ዘንድ ተልኮ የመጣው መልአክ እስራኤውያንን ከምድያማውያን እጅ እንዲያድን ሊነግረው ነበር /መሳ. 6:14/። ጌዴዎን ግን ሁኔታውን ላለመቀበል ብዙ ምክንያቶችን ሰጠ። አምላክ ሊያረጋግጥለት ለአንድ ሰው ሕልም አሳየው። ሰውዬው ያየው ሕልምም አንዲት የገብስ ቂጣ ተንከባላ ብዛ ቸው እንደ ባሕር አሸዋ የሆነውን የምድያማውያንንና የአማሌቃውያንን ድንኳን መትታ ድምጥማጡን እንዳጠፋች ነበር /መሳ. 7:13-14/። ጌዴዎን ሕልሙንና ፍችውን በሰማ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰገደ /መሳ. 7:15/። ሕልሙ ማረጋገጫ ሆኖለት ነበር ሚሊሽያ ምልመላ ውስጥ እስከመግባት ድረስ በውስጡ ከፍተኛ መንፈሳዊ ቅስቀሳ የተካሄደው። ጌዴዎን ቢያንስ ቢያንስ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሚሊሽያ አጅቦት ነበር። ይሁን እንጂ በጌታ ቃል መሰረት በሶስት መቶ ሰዎች ብቻ የድል ባለቤት ለመሆን በቃ።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከረሃብ ያዳነው ሕልምን ለፈርዖን ትርጉምን ለዮሴፍ በመስጠት ነበር /ዘፍ. 41:14-32/። ይህ ሕልምና ትርጉም ያስከተለው ውጤት ነበር እስራኤላውያን ወደ ግብፅ ሄደው እንዲበዙ በአምላካቸው ታምር ሕዝብ እንዲሆኑ ምክንያት የሆነው። ስለሆነም ሕዝቡን ከጥፋትና ከረሃብ ያዳነበት መንገድ ሕልም ነበር። መንፈስ ቅዱስ ሕልምና ራእይን በመጨረሻው ዘመን እሰጣለሁ ያለው ለእኛ ነው። እንዲህ ያለው ስጦታም ለጥበቃ፣ ለምሪትና ለጌታ ቸርነት ለእኛም ያስፈልገናል።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ሕልም ለምሪት ለጥበቃ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ለመግለጽ ሥራ ላይ ውሏል። የድንግል





ማርያም እጮኛ የነበረው ዮሴፍ መጽነሷን ባወቀ ጊዜ በሚስጥር ሊተዋት በማሰብ ላይ እያለ ሕልምን አለመ። በሕልሙም ውስጥ እጮኛህን ለመውሰድ አትፍራ እርሷ የጸነሰችው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው ሲል ገለጸለት። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ወንድ ልጅ እንደምትወልድና ስሙን ኢየሱስ (የሹአ) ብሎ መጥራት እንዳለበት ጭምር ነገረው። የስሙም ትርጉም ሕዝቡን ከኃጢአት የሚያድን ማለት ሲሆን ኤሎሂም በሕፃኑ ውስጥ ያለውን ዓላማ ገልጦለታል /ማቴ. 1:20-22/።

የሕልም መገለጥ ለማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ሰብዓ ሰገል ኮከብ በጠፋባቸው ጊዜ መሲህ የተወለደበትን ለመጠየቅ ወደ ሄሮድስ ቤተ መንግሥት ሄደው ነበር። ንጉሡም ሁሉን ከመረመረ በኋላ እንግዲህ ሂዱ ስትመለሱ በዚህ ኑና ሥፍራውን ንገሩኝ እኔም ሄጄ እሰግድለታለሁ አለ። የምሥራቅ ጠቢባን ግን ሕፃኑን ካገኙ በኋላ እግዚአብሔር በሕልም በመጡበት መንገድ እንዳይመለሱ አስጠነቀቃቸው። እነርሱም እንደተነገራቸው መንገድ ለውጠው ሄዱ /ማቴ. 2:12/። በዚህ የሕልም መገለጥ ምክንያት ሕፃኑ ኢየሱስ አድጎ ተልእኮውን ሳይፈጽም እንዲገደል ሰይጣን ያሰመው ዓላማ ከሸፈበት።

ከጰንጠቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በኋላም የሌሊት ራእይ ለሐዋርያው ጳውሎስ ተደጋግሞ ይገለጥለት ነበር። እነዚህንም በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መመልከት ይቻላል /ሐ.ሥ. 16:9; 18:9-10፤ 23:11፤ 27:23/

ኤሎሂም ለነቢያቱ በሕልም ወይም በራእይ እንደሚገለጥ ይናገራል /ዘኍ. 12:6-8/። ይሁን እንጂ እጅግ ትሁት ለሆነው ሙሴ ግን ፊት ለፊት አነጋግረዋለሁ እንዲያውም ፊቴን ያያል ብሎ ተናግሯል። እንግዲህ የሕልም መገለጥ የአምላካችንን ሃሳብ፣

ፈቃዱንና ምሪቱን የምንቀበልበት ስለሆነ ስጦታውን መሻት አለብን:: መቼም ሕልም የማያይ ሰው የለም:: ይሁን እንጂ ለራሳችን፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለአገርና ለወገን የሚጠቅመውን ለማየት መጸለይ መልከም ነው::

## 9.2 መገለጥ በራእይ

ራእይ ከሕልም የሚለይበት ተቀባዩ በእንቅልፍ ውስጥ አይደለም ያለው:: ወይ በጸሎት፣ በአምልኮ፣ ቃሉን በግሉ ሲያጠና፣ በጎዳና፣ በረጅም ጉዞ (በመርከብ በመኪና በአውሮፕላን) ላይ ሆኖ፣ ወይም አደገኛ ሁኔታ ላይ ሆኖ ሊሆን ይችላል:: ይህ ከሕልም የሚለየው በሥጋዊ ዓይን የሚታይ መልአክ፣ ሁኔታ፣ እንዲሁም በጆሮ የሚሰማ ሊሆን ይችላል::

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ባየው ራእይ ውስጥ የተካተተው የጴጥሮስ በኢዮጴ፣ በባህሩ አጠገብ፣ በቁርበት ፋቂው በስምዖን ቤት መሆን ነው /ሐ.ሥ. 10:5-6/:: ቆርኔሌዎስም እንደተናገረው መልእክተኞችን የላከው በዚያው አድራሻ ነበር:: መልእክተኞቹም ሄደው ያገኙት በራእዩ መመሪያ መሰረት ነበር:: ራእይ የሚያሳየን አምላካችን ስለሆነ በቅርብም በሩቅም ያለውን ያውቃል::

ጴጥሮስ በጾም ጸሎት ላይ ሆኖ በተመስጦ ውስጥ እንዳለ "ራእይ ዓየ" ይላል /ሐ.ሥ. 5:11/:: ጴጥሮስ የራእዩን ነገር እያሰላሰለ እያለ መንፈስ ቅዱስ *"እነሆ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል ስለዚህ ተነስተህ ውረድ የላክኋቸውም እኔ ስለሆንሁ ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ"* አለው (ሐ.ሥ. 10:10-16)::

ወገኖቼ ጴጥሮስ የጴንጤቆስጤው የእሳት ጥምቀት ትሩፋት ተከፋይ ከሆኑት አንጋፋ ነበር:: እርሱም በእሳት ልሳን የሚጸልይ፣





በሽተኞች የሚፈውስ፣ መናፍስትን የሚለይ፣ በመገለጥ ሙላት ያገለገለና ታምራትን ያደረገ ሰው ነበር:: ራእይንና መገለጥን አልጠላም እንዲያውም መልአክ መጥቶ ከተኛበት እስር ቤት ፈትቶ አውጥቶታል /ሐ.ሥ. 12:6-11/:: እኛ ራእይን ለምን እናጣጥላለን? የጰራቅሊጠስን እሳትና የራእይን መገለጥ ልንለያያቸው አንችልም:: ገና የመንፈስ ቅዱስን ረድኤት ያላገኙት የቆርኔሌዎስ ሦስቱ መልእክተኞች ልክ እንደተነገራቸው ኢዮጴ ስምዖን ደጅ ቆመው በር ማንኳኳትና ጴጥሮስን እንፈልጋለን ማለታቸው ሊያስገርመን ይገባል /ሐ.ሥ. 11:11/:: ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ምሪት የሚሰጥበትን የራእይ መገለጥ ሳንንቅ ተግተን ስጦታውን እንፈልግ::

## 9.3 ምን ታያለህ?

ወገኞቼ እናንተ ምን ታያላችሁ? ብዙ ጊዜ ሰዎች ይደውሉልኝና ፓስተር ቅዠት አስቸገረኝ አባብ ሲያሯሩጠኝ አደረ፣ አንድ ጥቁር አውሬ ማጅራቴን ነክሶኝ ሲያስጮኸኝ አደረ፣ ተራራ ስቧጥጥ አንድ የሆነ ሰው ቁልቁል ከአፋፍ ላይ ሲወረውረኝ አየሁ፣ በሕልሜ የኔ ካልሆነች ሴት ጋር ስማግጥ አየሁ፣ ሴቷም እንዲሁ አባክህን ጸልይልኝ? ጌታ ከዚህ ነፃ እንዲያወጣኝ እፈልጋለሁ ይሉኛል:: የኤሎሂም ቃል *"መልካም ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ"* ይላል (ሮሜ 12:2):: የጌታ ፈቃድ መልካም ነገር እንድናይ ነው::

እኔ መስማት የሰለቸኝ ሰይጣን እንዲህ ረግጦኝ እንደዚህ አሽቶኝ አስለቅሶኝ የሚል እሮሮ ነው:: የጌታ ቃል *"ልጆች ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ እነርሱንም አሸንፋችኋቸዋል ምክንያቱም በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል"* ነው

የሚለው (1ዮሐ. 4:4 አ.መ.ት.)። ስለሆነም እርገጠው እንጂ አይርገጥህ፤ እነቂው እንጂ አይነቅሽ፤ አንከባይው እንጂ አያን ክባልሽ አንቺ አሸናፊ ነሽ።

የጌታ መልአክ ዘካርያስን ለጭን ከእንቅልፍ እንደሚያነቃ አነቃውና ምን ታያለህ? አለው /ዘካ 4:1-2/። ነቢዩም ያየውን የወርቁን መቅረዝ በአናቱ ላይ ያለውን ማሰሮ ሰባቱን ቧንቧዎች ሲል መለሰ። ቁጥር ሁለት ላይ የራእዩን ትርጉም ገለጸለት። ምና ልባት ራእይ ጠፍቶብህ የምትማረው ትምህርት ምን እንደሆነ፣ ስለምታገቢው ባል፣ ስለምታገባት ሚስት ስለ ሥራና ስለ አገል ግሎት ዝብርቅርቅ ባለ ሁኔታ ውስጥ ትሆኑ ይሆን? ወገኖቼ የሚያነቃው የኤሎሂም መንፈስ በውስጣችሁ ነው ያለው። እርሱ ለሕይወታችሁ ጉዳይ ሁሉ ራእይን ይሰጣችኋል።

እግዚአብሔር አሞጽን ራእይ አሳየውና ምን ታያለህ በል? አለው እርሱም ቱንቢ አያለሁ አለው /አሞ. 7:7-8/። በእስራኤል ላይ ስለሚመጣ ቁጣ ነበር ያሳየው። ለምን አሳየው ብለን ብንጠይቅ ከቁጣ እንዲያመልጡ እንዲሰብክላቸውና እንዲጸልይላቸው ነው። እንደገናም /አሞ. 8:1-2/ ራእይ አሳየውና ምን ታያለህ? ይለዋል። ወገኖቼ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚሰጠን ራእይ ለእኛ ለቤተሰባችን ለምድራችን ለምንኖርባት አገር በረከትን የሚያመጣ ሲሆን ይች ላል። ይህን መንፈስ ቅዱስ ለሕዝቡ የሚናገርበትን መንገድ አንዝ ጋው ክፍት እናድርገው።

## 1) የምታየውን ትረዳዋለህ?

ትልቁ ችግራችን በሕልምም ሆነ በራእይ የምናየውን መረዳት አለመቻላችን ነው። እንዲያውም ያየነውን ሕልም ወዲያው ነቅተን ካልጻፍነው በስተቀር እንረሰዋለን። ሰይጣን ደግሞ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት አቅጣጫ እንድንስት ለማድረግ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስንስማማና ቃሉን በጥልቀት





ስናውቅ መገለጦችን እንረዳለን። መገለጥን የሚሰጥ አምላክ ትርጉምን ደግሞ ይሰጣል። ምን ታያለህ? ያላቸውን ነቢያት ያሳያቸውን ነገሮች ትርጉም ነግሯቸዋል። የቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅና ጉዳይ አስፈጻሚ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ለእኛም የሕልምና የራእይ ትርጉም ይሰጠናል።

ዮሴፍ ለፈርዖን ሕልሞቹን ተረጎመለት። ባይተረጉምለት ኖሮ የረሃቡ ዘመን ሲመጣ ፈረዖንና ሕዝቡ ራሳቸው በረሃብ ያልቁ ነበር። በዮሴፍ የመጣው ትርጉም ግን ረሃብ ለመታቸው አገሮች ሁሉ ግብፅ መፍትሄ እንድትሆን አደረገ /ዘፍ. 41:25-26/። እግዚአብሔር ሚስጥር አድርጎ በምሳሌ፣ በስዕል፣ በመልአክ፣ በእሳት የተናገረውን ነገር መንፈሳዊ ሰው መመርመርና መረዳት አለበት /ምሳ. 25:2/። ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ጥልቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ነገር ይመረምራል ይላል። ለእኛም በመንፈሱ በኩል እንደገለጠልን ያስምርበታል /1ቆሮ. 2:10፣ 13፣ 15/። ለዚህ ነው መገለጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ያልኋችሁ። መገለጥ መንፈሳዊ ስጦታ ስለሆነ በብርቱ ፈልጉት።

ትርጉም ላይ ብዙ ጸሎትና ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የመሰለን ትርጉም ላይ ማረፍ የለብንም። እንዲያውም ስጦታው ወዳላቸው ሰዎች ሄዶ ማካፈልና አብሮ ጸልዮ መልስ ማግኘት ይሻላል። ምክንያቱም አንዱ ቃል ወይም ምሳሌ በብዙ አቅጣጫ ሊፈታ ስለሚችል ነው። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያሉትን እንመል ከት፦

- ኢየሱስ ፦ የይሁዳ አንበሳ ይባላል /ራእ. 5:5/
- ጴጥሮስ፦ ሰይጣን እንደ አንበሳ ይዞራል ይላል/1ጴጥ. 5:8/
- ሰለሞን፦ ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ያለ ፍርሃት ይኖራል ይላል /ምሳ. 28:1/

በዚህ ላይ እንደተገለጸው በሕልሙ ወይም በራእይ አንበሳ ያየ ሰው ትርጉሙን ምን ሲለው ነው? ከልተጠነቀቅን የተዛባ ትርጉም

እንስጠዋለን:: ጠለቅ ብለን ሶስቱም ያሉትን ስንመረምረው ግን ጴጥሮስና ሰሎሞን እንደ አንበሳ ነው ያሉት ባለ ራእዩ ዮሐንስ ግን ጌታ ኢየሱስን አንበሳ ነው ያለው:: ሃሌ ሉያ!! ለዚህ ነው ቃሉን በጥልቀት ማወቅ ያለብን::

## 2) መገለጥ ዛሬ ይሠራል?

የጌታ ቃል *"እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም"* ይላል (ሚል. 3:6):: የማይለወጥ አምላክ ዛሬም ራሱን፣ ሃሳቡን፣ ፈቃዱንና ዓላማውን ለልጆቹ ይገልጣል:: ወገኖቼ እግዚአብሔር ያለ መገለጥ ሕይወት አያመላልሳችሁ:: መገለጥ ከሌለ ምን ሕይወት አለ? ቃሉም ከልተገለጠልን ቃል ብቻ ይሆናል:: መንፈሳችን የሚዳሰሰው ግን መገለጥ ሲመጣ ነው:: በጴንጠቆስጤ እለት በድጋሚ የተሰበከው እንዲህ ነው የሚለው፤ *"በመጨረሻው ቀን መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ ጎልማሶቻችሁ ሕልም ያልማሉ"* (ሐ.ሥ. 2:17)::

ከማንም ይልቅ በመጨረሻ ዘመን ላይ ያለነው እኛ ነን:: ስለዚህ እነዚህ የመገለጥ ስጦታዎች በየዕድሜ ክልላችን ይሰጡናል ማለት ነው:: ቅድመ ዝግጅቱ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ነው:: አሞጽ ሲናገር:- *"አንበሳው አገሳ የማይፈራ ማን ነው? ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ ትንቢት የማይናገር ማን ነው?"* አለ (አሞ. 3:8)::

## 3) መገለጥ በሚዛን

የመጣውን መገለጥ ሁሉ ዝም ብለን እንቀበላለን ማለት አይደለም:: ጌታ ቃሉንና መንፈሱን መመዘኛ አድርጎ አስቀ ማጦልናል /1ቆሮ. 14:29/:: ሐዋርያው ጳውሎስ *"ሁሉን ነገር ፈትኑ መልካም የሆነውን ያዙ"* ይላል (1ተሰ. 5:22):: መቼም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ማስተላለፊያ ዕቃዎች ፍጹም ስላልሆንን ፍጹም





የሆነው መልእክቱ በዕቃው ምክንያት ቆሽሾ ሊያልፍ ይችላል:: ስለሆነም ዕቃዎቹ ሰብዓዊ ፍጡር ስለሆንን በሚተላለፉ መገለጦች ውስጥ ስህተት ሊኖሩ ይችላል ማለት ነው:: ፍጹም የሆነ አገልግሎት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ብቻ ነው::

ስህተት አለ ተብሎ ደግሞ ስጦታዎቹን ማጥላላት እንዲያውም መገለጥ የሚባል ነገር እንዳይጠራ ማለት ጸረ መንፈስ ቅዱስ አቋም ነው:: ማንኛውም ነገር በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ስለሚጸና በቃሉ ስጦታዎችን ወይም መልእክቱን መመዘን አስፈላጊ ነው:: የምንመዝነው መልእክቱን ያስተላለፉትን ሰዎች አይደለም መልእክታቸውን ነው:: ስህተት ከተገኘም እንኳ አገልጋዮቹን እናቅናቸው እንጂ አንግፋቸው፤ እንጠግናቸው እንጂ አንስበራቸው፤ አንተም ለራስህ ተጠንቀቅ ቃሉ አይለይህ::

# 10

# መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓቶች

ሁሉ ነገር ሥርዓት አለው ሊኖረውም ይገባል:: ተፈጥሮን እንኳን ብንመለከት ሁሉ ነገር በሥርዓት ይሠራል:: በአካላችን ውስጥ ያሉ ብልቶቻችን በተመደበላቸው ሥርዓት ነው ተግባ ራቸውን የሚያከናውኑት:: የትራፊክ ደንቦች ለአሽከርካሪዎች ሥርዓት ናቸው:: ያ ሥርዓት ባይጠበቅ ብዙ አደጋ ሊከሰት፣ በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጥፋት ሊደርስ ይችላል:: እኛም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን እድገትና ሂደት ሥነ ሥርዓት ያስፈልገናል::

## 10.1 በመንፈስ መመላለስ

በመንፈስ መመላለስ በመንፈሳዊ ሕይወት ሂደት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ሥነ ሥርዓት ነው:: አለዚያ ጸጋ አያድግም አገል ግሎት ውጤት አይኖረውም መንፈሳዊ ውድቀት ሊመጣ ይችላል:: በመንፈስ ብንመላለስ ግን ጌታን ደስ እናሰኘዋለን ባርኮቱም በየዕለቱ ይበዛልናል::

መንፈስ ቅዱስ የመጣው በውስጣችን ሆኖ ሊመራን ነው:: ይሁን እንጂ በራሳችን ዕቅድ፣ በለመድነው መንገድ ራሳችንን

የምንመራ ሁሉ ፈቃዳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ማስረከብ ይኖርብናል:: በዓለም ውስጥ መምራት የሁሉ ፍላጎት ነው:: ይሁን እንጂ መሪው ወዴት እንደሚያደርስህ እግዚአብሔር ይወቀው:: መንፈሳዊ ሰው የጌታን ድምጽ እየሰማ መሪውን ይከተላል::

፯

በመንፈስ መመላለስ ማለት መንፈስ መሆን ማለት አይደለም:: ግን የራስን ፈቃድ ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት ማለት ነው:: ድምጹን ማዳመጥና መከተል በእርሱ መኖር ማለት ነው:: ኤሎሂም ጰራቅሊጦስን የሰጠን በመንፈስ መመላለስ እንዲያስችለን ነው:: በመንፈስ የሚመላለስ ደግሞ በመንፈስ ይኖራል /ገላ 5:25/:: በመንፈስ የሚመላለስ የሥጋን ሥራ አያደርግም /ገላ. 5:19-23/:: በመንፈስ የሚመላለስ የመንፈስን ነገር ይሠራል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችም በሕይወቱ ይገኛሉ /ገላ. 5:22-23/::

## 10.2 ስጦታን በአግባቡ መጠቀም

ወደ ኋላ ተመልሰን ከማናስተካክላቸው ሁኔታዎች መካከል አንዱ በአገልግሎታችን ውስጥ ፈጥረን የምናልፈው ብልሽት ነው:: ይሁን እንጂ ብልሽቱ እንዳይቀጥል እርማት አድርገን ማለፍ እንችላለን:: በአንድ ወቅት ላይ ጋዜጠኞች ታዋቂ ወንጌላዊ የሆኑትን ዶ/ር ቢል ግርሃምን ብዙ ጥያቄዎችን ከጠየቋቸው በኋላ እንደገና ልጅ ቢሆኑና አገልግሎት ቢጀምሩ ምን ያደርጋሉ? አሏቸው ወንጌላዊውም ብዙ ጊዜ በጸሎት ላይ አጠፋለሁ ሲሉ መለሱ ይባላል:: መንፈሳዊ ስጦታን በአግባቡ ስለ መጠቀም በምክር መልክ ከዚህ ቀጥዬ በነጥብ አስቀምጣለሁ::

1. በጾምና በጸሎት መትጋት/ ከሰጪው ጋር ጊዜ መውሰድ::
2. አገልግሎታችን ለጌታ ክብር ማምጣቱን ማረጋገጥ::
3. ስጦታ ስላለህ ከሁሉ የተሻልህ አይምሰልህ/ ትሁት ሁን::
4. የምትናገረውና የምታደርገው አንድ ይሁን (integrity)::





5. ፕሮግራም ይዘህ እንደሆነ በቅድሚያ ሳታሳውቅ አትስርዝ::
6. በፍቅር /በደስታ/ በርኅራኄ አገልግል::
7. ተዘዋዋሪ አገልጋይ ከሆንህ ትንሽ ትልቅ ጉባኤ ብለህ አትምረጥ::
8. ብዙ አትናገር ብዙ ግን አዳምጥ::
9. ለምታገለግለው ሕዝብ ምሳሌ ሁን::
10. በእምነት ተመላለስ::
11. ጌታ ያልከፈተውን በር አታንኳኳ::
12. የሌሎችን ጸጋ አክብር::
13. ስለ ሦስተኛ ሰው ከማንም ጋር አታውራ::
14. ቃሉን ብላ::
15. በተሰጠህ ጸጋ በድፍረት አገልግል::
16. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬችዎን በውስጥህ አሳድግ::
17. ራስህን ሁን እንጂ እንደ እገሌ መሆን አትሞክር::

## 10.3 የመንፈስ አንድነትን መጠበቅ

መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚሰጡት ለአካል ጥቅም ነው:: የእያንዳንዱ ሰው አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ማነጽ አለበት:: በሃሳብ፣ በዕውቀት ደረጃ፣ በአገልግሎት ጸጋ፣ በችሎታ ልንለያይ እንችላለን:: ይሁን እንጂ የአንድ አካል ብልቶች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም:: አንድነትን ከሚቀጩ ሁኔታዎች ገለል ማለት አለብን:: ከዚህ ቀጥለን አንድ የሚያደርጉን ሁኔታዎችን ከቃሉ በነጥብ ላሳያችሁ::

| | |
|---|---|
| 1. አንድ አካል ነን | ሮሜ. 12:4-5 |
| 2. በአንድ መንፈስ ተጠምቀናል | 1ቆሮ. 12:13 |
| 3. አንድ መንፈስ ጠጥተናል | 1ቆሮ. 12:13 |
| 4. በአንድ መንፈስ ታትመናል | ኤፌ. 1:13-14 |

5. አንድ ተስፋ አለን ቲቶ. 2:13
6. አንድ ትንሣኤ አለን ሮሜ. 8:18-25
7. አንድ ጌታ አለን 1ቆሮ. 1:13
8. አንድ ራስ አለን ኤፌ. 5:22-23
9. አንድ እምነት አለን ሮሜ. 1:5
10. አንድ ጥምቀት አለን ኤፌ. 4:5
11. አንድ አባት አለን ኤፌ. 4:6

ከላይ የተጠቀሱት አንድ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው። ስለሆነም የአካልን አንድነት ለመጠበቅ ሁላችንም ጥረት ማድረግ አለብን።

## 10.4 ከጸረ ቅባት ኃይላት መጠበቅ

የተቀቡ ሰዎችን ሰይጣን በረቀቀ ጥበቡ በመዋጋት ቅባታቸውን ለማስጣል ጥረት ያደርጋል። በረከሰ ሃሳቡ ተስፋ በማስ ቆረጥና የግልንም ደኅንነት እስከሚጠራጠሩ ድረስ መዋጋቱ አይቀሬ ነው። የተቀቡ ሰዎች ለሰይጣን መቅሰፍቶች እንደሆኑ ሰይጣን በሚገባ ስለሚያውቅ። ሳልቀደም ልቅደም በሚል ፍልስፍናው ለማጥፋት የሚችልበትን መንገድ ሁሉ ይሞክራል። ከባሰም ስደትን በማስነሳት በእስር፣ በግርፋት፣ በሞትና በተለያዩ ሰይጣን ሰራሽ ችግሮች የአመጽ እሳቱን ይለኩሳል።

ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጠንቅ የሚሆነው፣ ከስሜታችን ጋር በተያያዘ ጉዳይ በፈተና ላይ ስንወድቅ ነው። በተለይም ባለንበት ዓለማዊ ኅብረተሰብ ውስጥ አገልጋይም ሳይቀር የሚፈተንበት ጊዜ አለ። ፈተናዎቹን ማወቅ ደግሞ ጥንቃቄ ለማድረግ ይጠቅመናል። ዋና ዋናዎቹ ፈተናዎችም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ✓ ዝሙት
- ✓ ገንዘብ
- ✓ ትዕቢት





በአሜሪካ አገር ውስጥ በቤተ ክርስቲያን እነዚህ ከፍተኛ ችግሮች ናቸው። በእነዚህ ችግሮች ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ክብሯን አጥታለች። ታላለቅ የወንጌል አገልጋዮች በእነዚህ ወጥመዶች ምክንያት ሥፍራቸውን አጥተዋል። ዘመናዊው ሰው ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ወደ ሌሎች የመዝናኛ ሥፍራዎች መሄድን የመረጠበት ጊዜ ነው። በአሜሪካ ውስጥ እንደ ሌሎቹ ከመቶ ጋብቻ ውስጥ ሃምሳው በፍቺ ያከትማል። በትዳር ውስጥ ብዙ የታማኝነት ጉድለት አለ።

### 1) ዝሙት

ዝሙት ጸረ ቅባት ከሆኑት ኃይላት መከከል የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል። የሳምሶን ሕይወት ለአንድ አፍታ ተመልክተን ብናልፍ ለምናደርገው ጥንቃቄ አስተዋጽኦ ያደርግ ይመስለኛል። መንፈስ ቅዱስ በሚያስፈልገው ሰዓት በላዩ ላይ እየወረደ ብዙ አስደናቂ ድርጊቶችን ፈጽሟል። ጦርነት የሚያደርገው ከፍልስ ጥኤማውያን ጋር ብቻ ሳይሆን ከእንስሳ፣ ከዋና የከተማ ቅጥር በሮችና ታላላቅ ያዳራሽ ምሰሶዎችም ጋር ነበር። ያን ጀግና ወደ ጠላቶቹ ሰፈር ያመላለሰው የነበረው ሊቆጣጠር ያልቻለው የፍትወት ሕይወቱ ነበር (መሳ. 14:7-8፣ 15፤16:1-2፣ 4-20)። በተለ ከፈበት ኃጢአተኛ ባሕርይ የተቀባው ሰው ዓይኖቹን አጣ። ጸጋው ሁሉ ተገፍፎ አምላኩ ተሰየው። ወገኖቼ የተቀባ ሰው ፍላጎቱን መቆጣጠርና ሕይወቱን መጠበቅ አለበት። አለበለዚያ የሳምሶን ዕጣ ነው የሚደርስበት።

ሰሎሞን እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ የተገለጠለት፣ የኤሎሂም ታቦት የሚያርፍበትን መቅደስ የሠራ ትልቅ የተቀባ ንጉሥ ነበር። እግዚአብሔር በሞገስ በጥበብ በኃብት አበለጸገው። ዝናው ዓለምን ሁሉ ሞላ። የእርሱን ጥበብ ለማየት ነገሥታት ስጦታ እየያዙ ወደ እርሱ ይጎርፉ ነበር። ከዝናው ጋር ገንኖ የታየው የዝሙት

ሕይወቱ ነበር። ሰሎሞን ሰባት መቶ ወይዛዝር ሚስቶችና ሶስት መቶ ቁባቶች እንደነበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል /1ነገ. 11:3/። ብዙዎቹም የእስራኤልን አምላክ የማያውቁ ባእድ ሴቶች ስለነበሩ እነርሱን ለማስደሰት ሲል የየአገራቸውን ጣኦት አቆመላቸው /1ነገ. 11:6-10/። ይህን በማድረጉም የአባቱ አምላክ ተቆጣና ከእርሱ በኋላ መንግሥቱ እንዲከፈል አደረገ።

ወገኞቼ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችን ወይም የተቀባ አገልጋይ መሆናችን ከእግዚአብሔር ቃል በላይ አያደርገንም። እንዲያውም የተቀባ ሰው ለሌሎች ምሳሌ መሆን ይገባዋል። ቅድስናና እግዚአብሔርን መፍራት የተቀቡ አገልጋዮች ሲከተሉት የሚገባ የሕይወታቸውና የአገልግሎታቸው መመሪያ ነው። የጌታም ቃል *"ከዝሙት ሽሹ"* ይላል (1 ቆሮ. 6:18)።

## 2) ገንዘብ

በመሰረቱ ገንዘብ ቢኖረን ኃጢአተኞች ነን ማለት አይደለም። የሰሎሞንን ሕይወት ስንመለከት በእርሱ ዘመነ መንግሥት ገንዘብ አይቆጠርም ነበር። ምክንያቱም ንጉሡ በግዛቱ ውስጥ ገንዘብን እንደ ድንጋይ አበዛው ይላል /2ዜና 9:20-27/። ጥያቄው የተሰጠህን ገንዘብ ምን አደረግህበት ነው? እግዚአብሔር ከሰጠን ገንዘብ በወንጌል ሥራ ላይ ማዋል የሚጠበቅብን ነገር ነው። ሐዋርያትም እንኳ ለአገልግሎታቸው ገንዘብ ይሰበስቡ ነበር። በፋንታው ግን ገንዘብን አምላክ ስናደርገው ከፍተኛ ችግር ነው።

ኤልሳዕ ከተቀባና ከተጠራ በኋላ ለዘመናት ኤልያስን ያገለግል ነበር። ባለብዙ ንብረት ቢሆንም እንኳ ለደረሰው መለኮታዊ ጥሪ ወደ ኋላ አላፈገፈገም። ጥሪው ኤልያስን የሚተካ ነቢይ፤ ኑሮው ግን እጅ አስታጣቢና ተላላኪ ነው የሆነው። ይሁን እንጂ ይህ





በመሆኑ ያሳየው ቅሬታ የለም። አንድ ቀን ኤሎሂም አሰበውና የጠየቀውን እጥፍ ቅባት ጠቅልሎ አስረከበው /2ነገ. 2:14-15/።

እርሱ በበኩሉ በእግሩ ተተክቶ የሚያገለግል ሰው ግያዝን እያሰለጠነ ነበር ያለው። የሞተ ሰው ለማስነሳት መመሪያ ሰጥቶ የላከው ግያዝን ነበር። ለንዕማን ስለ ለምጹ ፈውስ መልእክት ያመላለሰው ግያዝ ነበር። ከሱነማዊቱ ሴት ጋር በነበረው ቃለ ምልልስ የነቢዩ አፈ ቀላጤው ግያዝ ነበር። ሁሉን እያሳየው ለቅባት አገልግሎት እያዘጋጀው እያለ ተሰውሮ ሄደና ዋሽቶ ከንዕማን እጅ ገንዘብ ተቀበለ /2ነገ. 5:20፣ 22-33/። ግያዝ የፈጸመው ድርጊት በዕውቀት መገለጥ ወደ ኤልሳዕ ስለመጣ ግያዝን ወዴት እንደ ሄደ ቢጠይቀው እዚህ ነበርሁ ብሎ ዋሸ። አንድ ኃጢአት ሌላ ኃጢአትን ይወልዳል። ሲቀበል ዋሽቶ፣ ለጌታውም ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ውሸት ተናገረ። መፋቅረ ንዋይ ነበር ግያዝን ከቅባት አገልግሎት ልምምዳዊ ትምህርት ቤት ያስወገደው። በነቢዩ እርግማን ምክንያት በሕይወት ዘመኑ ለምጻም ሆነ።

ከዚሁ ጋር አያይዘን የይሁዳን ሕይወት ብንመለከት ችግሩ ገንዘብ ነበር /ዮሐ. 12:4-6፣ ማቴ. 27:3/። ከአስራ ሁለቱ አንዱ ሆኖ የተቆጠረው ለቅባት አገልግሎት የተዘጋጀ ሰው በገንዘብ ምክንያት ለሶስት ዓመት ተከትሎ አብሮት የነበረው ጌታውን ሸጠ። አሟሟቱም በጣም ያሳዝናል። የተቀባ ሰው በኃጢአቱ ምክንያት ቅባቱ ሲወሰድበት እንደ ማንኛውም ተራ ሰው ለመሆን ዝቅ ይላል። እኛም እንደነዚህ ካሉት ሕይወት እየተማርን ልንጠነቀቅ ይገባል።

የሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎት ባልደረባ የነበረው ዴማስም ችግሩ ይህንኑ ይመስላል /2ጢሞ. 4:10/። ቅባትን ከሚቀጩ ነገሮች ሕይወታችንንም ሆነ አገልግሎታችንን መጠበቅ ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቃል *"የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ስር ነው አንዳንዶች ባለ ጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሳ ከእምነት*

*መንገድ ስተው ሄደዋል ራሳቸውን በብዙ ሥቃይ ወግተዋል"* ይላል (1ጢሞ. 6:10 አ.መ.ት):: አምላካችን ሆይ እርዳን!

## 3) ትዕቢት

ቅባትና ትዕቢት ሁለቱ ተቃራኒ ኃይላት ናቸው:: ቀቢው አምላካችን ፈቃዳችንን አይጋፋም:: ይሁን እንጂ የቃሉን መመሪያ ሰጥቶናል:: ጳራቅሊጦስ ሊረዳን ከመጣበት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በትህትና መመላለስን እንድንመርጥ ነው:: ለምንድን ነው የተቀቡ ሰዎች የትዕቢትን መንገድ የሚመርጡት ብለን ብንጠይቅ? በእጃቸው የሚደረገው የቅባት አገልግሎት ከራሳቸው የመነጨ ሲመስላቸው ነው:: ያን ጊዜ ከሰዎች ክብርን ለራሳቸው ይቀበላሉ:: ጌታ በማለት ፋንታ እኔ ማለት ይጀምራሉ:: ይህ ደግሞ በጣም አደገኛ መንገድ ነው::

በውስጣችን ሊኖርና መንፈሳዊ ኃይልን ለማመንጨት የመጣው ጳራቅሊጦስ ነው የምታደርገውን ሁሉ እንድታደርግ የረዳህ:: የጌታም ቃል *"ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግና ማድረግን በእና ንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና"* ይላል (ፊል. 2:13):: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ተጠቅሞ ምንም ዓይነት ድንቅና ታምራትን ቢያደርግም እንኳ ክብርን ለጌታ ስጥ:: ሉቃስ እንዲህ ሲል ጽፏል *"እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ"* (ሉቃ. 17:10)::

በትዕቢት ምክንያት ከቅባት አገልግሎት የተገለሉ ሕይወታቸውንም ያጡ ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ንጉሥ ሳኦል ነው:: ሳኦል ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ ክብርን ለእግዚአብሔር ማምጣት ተወ፣ የአምላኩን ትእዛዝ ከመከተል አዘነበለ /1ሳሙ. 15:17-23/:: ከዚያ





ትዕቢትና እንቢተኝነት በኋላ ቀባሁህ ያለው አምላክ ናቅሁህ በፋንታህ ሌላ ሰው ቀባሁ አለው ቁጥር 26 ይመልከቱ::

ወገኖቼ ዘወትር በጸሎቴ ውስጥ የማካትተው ልመና አለኝ:: ይኸውም ጌታ ሆይ ቅባትህን ከእኔ ላይ አትውሰድ የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጌታ ሆይ ቅባትህን በሕይወቴ ውስጥ ጨምር ነው:: ማናችንም ብንሆን ያለጌታ ቅባት ራቁታችንን ነን:: ለምንም አደጋ፣ ለውርደትና ሞትም እንኳ የተጋለጥን እንሆናለን:: ለዚህ ነው ሕይወትንም ሆነ ቅባትን ከሚቀጩ ከሶስቱ ጸረ ቅባት ኃይላት መጠንቀቅ ያለብን:: ጌታ ሆይ እርዳን!

ጳራቅሊጦስ አስችሎህ በእጅህ ሽባ ሊተረተር፣ እውር ሊበራ፣ ካንሰርና ኤድስ ሊነቀል ይችላል:: የሞተ ሰው እንኳን በአገልግሎትህ ሊነሳ ይችላል:: እርሱ ፈጣሪ ነው ብዙ አስደናቂ ነገሮችን በእጅህ ሊያደርግ ይችላል:: ክብርን ግን ለቀባህ እምላክ አሳልፈህ ስጥ:: ሰዎች ጥሩ ለዘመረ፣ አጋንንት ላወጣ፣ በሽተኞችን ለፈወሰ፣ ማምለክ ደረጃ ድረስ ሊሄዱ ይችላሉ:: አንተ ግን እንደ ዮሐንስ *"እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ይገባል"* በል (ዮሐ. 3:30):: ይህን የትህትና ጎዳና ስትከተል ቅባትህ ያድጋል:: ትናንት በአገል ግሎትህ ከታየው ያለፈ እንድታደርግ ጳራቅሊጦስ ይረዳሃል:: አሜን!

11

# ይህ የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ነው!

ዘመናት በእግዚአብሔር ዘንድ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው:: ጌታ ለሰው ልጆች ጥቅም መልካም ነገር የሚያደርገው በዘመን ውስጥ ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ያላገኙትን በረከት እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ላይ ዕድሜን ጾታን ሳይለይ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሱን እንደሚያፈስስ በነቢዩ ኢዩኤል ተናገረ /2:28-29/::

ትንቢቱ ከክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ በጰንጠቆስጤ ቀን ፍጻሜ አግኝቷል:: ሐዋርያት በጰራቅሊጦስ መምጣት ሕይወታቸው ረሰረሰ፣ ደስታ ሞላባቸው፣ ተቀብተው ማገልገል ጀመሩ:: *"እንጃ ይህ ምን ይሆን"* ብለው በሚያዩትና በሰሙት ነገር መገረም ለያዛቸው አይሁድ ጴጥሮስ ብድግ ብሎ በነቢዩ ኢዩኤል የተነገረው የኤሎሂም መንፈስ ነው የፈሰሰው ሲል በድፍረት ተናገረ /ሐ.ሥ. 2:17/::

በሰሙት ሰብከትና ባዩት ነገር ልባቸው የተነካው አይሁዶች ምን እናድርግ ብለው ቢጠይቁ *"ንስሃ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ"* አሏቸው (ሐ.ሥ. 2:38):: በሚቀጥለው ቁጥር ስንመለከት፣ የተስፋው ቃል የሚያካትተው

እነርሱን፣ ልጆቻውንና ጌታ የሚጠራቸው በሩቅ ያሉትን ሁሉ እንደሆነ ተበሰረላቸው።

ይህ ሦስተኛው ሃሳብ እኛንም አካተተ ማለት ነው። ምክንያቱም እኛም ተጠርተን ወደ ጌታ መጥተናል። ጌታ የጠራው አሕዛብ የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ደኅንነትን እንዲቀበል ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቅም ጭምር ነበር። እንዲያውም ጴጥሮስ እግዚአብሔር ይህን ስጦታ ለእነርሱም ከሰጠ መከልከል የምችል እኔ ማን ነኝ ይላል /ሐዋ.ሥ 11:17/። ወገኖቼ ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ይፈሳል። የሚያምን ሁሉ የአብን ተስፋ ሊቀበል ይችላል።

## 11.1 መንፈስ ይሙላባችሁ

ለሕይወታችንም ሆነ ለአገልግሎታችን መንፈስ ቅዱስን መቀበልና መሞላት አማራጭ የሌለው እውነታ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ የቀድሞ ሥጋዊ ባሕርያችን ሁሉ ለቆ ይሄዳል። ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ ይለወጣል። አንድ ጊዜ ዕድሜው ስምንት ዓመት የሆነ ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወዲያው በልሳን ጸለየ። በማግስቱም ከእናቱ ጋር ጸለየና በውስጡ ብዙ ለውጥ ተሰማው። ልጁ በመገረም መስታወት ፊት ቆመና ራሱን ከየ በኋላ እናቱን እማዬ ውስጤ በጣም ተለውጧል ፊቴ ግን ለምን አልተለወጠም? አላት።

ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ጰራቅሊጦስ ቢመጣላችሁ ይሻላል ብሎ የተናገረው እውነት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከመጠመቅ በኋላ ፍቅር ፍቅር፣ ሰላም ሰላም፣ ደስ ደስ ያሰኛል። ያስቃል፣ ያዘልላል፣ ጸልይ ጸልይ ያሰኛል፣ ያዘምራል። እውነተኛ ለውጥ የሚታየው እርሱ መጥቶ በልባችን ዙፋን ላይ ሲቀመጥ ነው። ሃሌ ሉያ!





መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ሊመጣ ይችላል። ይህን የሚስማመዱ ሰዎች ዛሬም አሉ። እኔ ራሴ የተጠመቅሁት በእሳት ነበር። ሲመጣ ከንፈሬ ላይ ሲያርፍ በዓይኖቼ ዓይቻለሁ። በጰራቅሊጦስ መምጣት ሕይወቴ ነው የተቀየረው። አንድ ጊዜ በናዝሬት ከተማ አማኑኤል መንፈሳዊ ማህበር በዚህ ርዕስ ላይ አገለግል ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉትን ቁሙ ብዬ ስጸልይላቸው ብዙ አዋቂዎችና ልጆች ተሞሉ። አንዲት አፏን የምትጠርግ የአስራ ሶስት ዓመት ልጅ አየሁና በሁኔታው በጣም ተገርሜ ልጅቱን አምጡልኝ አልሁ። አፍሽን የምትጠርጊው ምን ሆነሽ ነው? ብዬ ብጠይቃት፣ በልሳን መናገሯን ቆም አድርጋ ሾል ያለ እሳት ከሰማይ መጥቶ አፌን ቅብት አደረገኝ አለች።

በሌላ ጊዜ ደግሞ አዋሳ ላይ አንዲት ልጃገረድ በጣም እየጮኸች እባካችሁ ለምን ዝም ትላላችሁ ቤቱ ተቃጠለ እኮ ስትል ብዙ ሰዎች ሳቁ። እኔም ሁኔታው ገባኝና ዝም በሉ ልጅቱ ያየችውን ነው የምትናገረው አልኳቸው። በሌላ ጊዜ አስመራ ላይ በ1997 ዓ.ም ከሩሴድ ሳካሂድ አንድ የዘጠኝ ዓመት ልጅ አፉንም ልቡንም ይጠርጋል። ምን ሆነሃል ብዬ ብጠይቅ ሃዊ! ሃዊ! እያለ የጮኻል። “ሃዊ” ማለት በትግርኛ እሳት ማለት ነው። ሰጁም እሳት በልቡና በአፉ ላይ እንዳረፈበት ነው የሚናገረው ብለው ተረጎሙልኝ። ወገኖቼ ዛሬ የሚያስፈልገን ያ! ሃዊ ነው። አቤቱ ጌታ ሆይ ሃዊ ላክልን! በአምቦ ከተማ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አዛውንት ሴት ራሳቸውንና ሰውነታቸውን እየጠረጉ በኦሮምኛ “ኢቢዲ ዋቃዮ ነረት ኩፌ” አሉ። የእግዚአብሔር እሳት በላዬ ላይ ወደቀብኝ ነው ያሉት።

ወገኖቼ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ለሰው ዘር ሁሉ ነው ይሰጣል የተባለው። ቆዳህ ምንም ቀለም ይሁን፣ የቱንም ቋንቋ ተናገር፣ ሥልጣንህ፣ ዕውቀትህ፣ ዕድሜህና ፆታህ ምንም ይሁን

የሚያስፈልግህ እሳት ነው:: መንፈስ ይሙላብህ! መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ሲመጣ በሕይወትህ ውስጥ መቃጠል ያለበትን ያቃጥላል፣ ይቀድስሃል፣ ይቀባሃል፣ ይለውጥሃል:: ሃሌ ሉያ! ጌታ ኢየሱስ *"እኔ የመጣሁት በምድር ላይ እሳት ለመለኰስ ነው አሁንኑ ቢቀጣጠል ምንኛ ደስ ባለኝ"* አለ (ሉቃ. 12:49 አ.መ.ት):: ወገኔ ምድጃው ልብህ ስለሆነ ትንሿን ልብህን ለመንፈስ ቅዱስ ብትከፍት እሳቱን ይለኩስብሃል::

የሙሴን ሕይወት የገለባበጠው፣ ያሟጠጠ ተስፋውን ያደሰውና የሕዝብ መሪ ያደረገው የቁጥቋጦው እሳት ራእይ ስለመጣለት ነበር:: አንተም በናፍቆት ወደዚህ ራእይ ና! ጌታ ሆይ ቁጥቋጦው እኔ ነኝ እሳትህን በውስጤ ለኩስ በለው፤ ሕይወትህን ያቀጣጥለዋል:: ሃሌ ሉያ!

መንፈስ ቅዱስ ወደ አንተ እንደ ዝናብ እንደ ጎርፍ እንደ አውሎ ነፋስ እንደ ወይን ጠጅ ሊመጣ ይችላል:: እንዴትም ይምጣ የመጣው ጰራቅሊጦስ ሊረዳህና ሊቀባህ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ ወገኖቼ:: በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ቅድመ ዝግጅቶች ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| 1) ክርስቶስን መቀበል | ሐ.ሥ. 2:36-37 |
| 2) መጠማት | ኢሳ. 44:3፣ ዮሐ. 7:37-39 |
| 3) የማያቋርጥ ጸሎት | ዘካ. 10:1፣ ሉቃ. 11:13 |
| 4) ማመስገን | ኢዩ. 2:23 |
| 5) ኑዛዜ | ምሳ. 1:23፣ ኢሳ. 57:15 |
| 6) እምነት | ገላ. 3:2 |

አማኝ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞላው እንዴት ነው? ጌታ በአንድ ብቻ ሳይሆን በበዙ መንገዶች የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ተግባራዊ ያደርጋል:: እነዚህም መንገዶች ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው::





| | |
|---|---|
| 1) ምእመናን በአንድ ልብ ሲጸለዩ ሐ. ሥ. 2:1-4 | |
| 2) እጆችን በመጫን | ሐ.ሥ. 8:15-17፣ 9:17፣ 19:6 |
| 3) ቃሉ ሲሰበክ | ሐ.ሥ. 10:44 |
| 4) በውሃ ጥምቀት ላይ | ማቴ. 3:16 |

## 11.2 በልሳን መናገር

በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክት እንደሆነ ግልጥ ባለ መልኩ በቃለ እግዚአብሔር ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን:: እግዚአብሔር ለተቀባዩ በልሳን መናገርን ምልክት አድርጎ ሰጥቶታል:: ይህን ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሦስት ቦታዎች ላይ ተጠቅሶ እናነባለን /ሐ.ሥ. 2:4፣ 10:44-46፣ 19:6/::

በጰንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ *"በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው"* ይላል:: በእለቱም ምልክት ሆኖ የተሰጣቸው በልሳን መናገር ነበር:: ከጰንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ በፈሰሰ ጊዜ ሁሉ ይህ ሞዴል ሆኖ እንደቀረ እናያለን:: በሰማርያ ከተማ እንኳን በአዳዲሶቹ አማኞች ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ሲጭኑ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው ይላል /8:16-18/:: ሲሞን ያየው ነገር ስለነበረ ነው እኔ ገንዘብ እሰጣችኋለሁ እጄን የምጭንበት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ይህንን ስጦታ ስጡኝ ብሎ የለመነው:: እግዚአብሔር አንዴ የሰጠው ምልክት በልሳን መናገር ነው::

ሐዋርያው ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ገና አፉን ከፍቶ ስለ ጌታ ሞትና ትንሣኤ ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ሲናገሩ ተደመጡ /10:44-46/:: ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ የሚወርድ ነገር ይሰማዋል፣ የመዳሰስ፣ የሙቀት፣ እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ያለ ንዝረት፣ ሰውነት ውርር

የሚያደርግ፣ ወይም ደስ ደስ የሚያሰኝ ሁኔታ ይሰማዋል:: እነዚህን ምልክት መስጠት ለእግዚአብሔር ከባድ አይደለም:: የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሐዋርያው ጳውሎስ እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው:: የእነርሱ ደግሞ ይደንቃል በልሳን ተናገሩ ትንቢትንም ተናገሩ:: ስለሆነም ጌታ የተወልን የመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሞዴል ይህ ነው:: የሚሞላው ግለሰብ ሲወርድበት ይሰማዋል፣ ሌሎች ደግሞ በአዲስ ቋንቋ ሲናገር ይሰሙታል::

ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት እንዳልሆነ የሚከራከሩ ሰዎች አሉ:: የሚጠቅሱትም የሰማርያ ሰዎችን ነው:: ይሁን እንጂ ሲሞን በገንዘብ ሊገዛ የወደደው የእጅ መጫን አገልግሎት ያስከተለውን አስደናቂ ሁኔታ በልሳን ሲናገሩ ሰምቶ ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም:: ሌሎችም የሚጠቅሱት ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 9:17 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ በልሳን አልተናገረም ይላሉ:: ይሁን እንጂ ጳውሎስ ከሁሉ የበለጠ በልሳን እንደሚናገርና በመንፈስ እንደሚዘምር አስምሮበታል /1ቆሮ 14:18/:: ታዲያ ያኔ ካልተሞላ መቼ ነው የተሞላው? እንዲህ ነው እንደዚያ ነው ብሎ ከመከራከር ራስን አዋርዶ በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት መፈለግ የስጦታው ተቀባይ ያደርግዎታል::

ክሩሴዶችና ሪቫይቫሎች በየሥፍራው ሳካሂድ ከሚከሰቱ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የሚያስደንቀኝ፣ ጌታ ምንም ልዩነት ሳያደርግ መንፈስ ቅዱስን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ሲያፈስስ ማየት ነው:: በሕፃናት ላይ እንኳ ሳይቀር መንፈስ ቅዱስን በሙላት እያፈሰሰባቸው በልሳ ይናገራሉ:: እንዲያውም ይህን ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ከአስራ ሶስት ዓመት በፊት አዲስ አበባ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር:: ከአገልግሎት በኋላ ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስጸልይ ብዙ ሰዎች ተሞልተው በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ መጸለይ ጀመሩ:: እነርሱንም ወደ መድረክ አውጥቻቸው በየልሳኖቻቸው ጌታን ያከብሩ ነበር:: ከነዚህም መካከል ከመቶ





የሚያልፉ ዕድሜአቸው ከስምንት እስከ አስራ ሶስት ዓመት የሚደርሱ ወጣቶችና ልጆች ይገኙባቸው ነበር::

ልጆቹ ሁሉ እያለቀሱ በልሳን ሲናገሩ ጉባኤው በእልልታ ድምጽ ቤቱን ሞላው:: እኔም በሁኔታው ተደናግጬ ዞር ብዬ ጌታ ሆይ ሕፃናትም በመንፈስ ቅዱስ ይሞላሉ እንዴ አልሁት? ጌታም አዎን ልጄ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ነው እኮ ያልሁት ሲል መለሰልኝ:: በልቤ ውስጥ ይካሄድ የነበረው ፍርሃት አዲስ ነገር አመጣብን ያስብለኛል የሚል ሲሆን ጌታ በቃሉ እንደተናገርው እንዳደረገ ሲገልጽልኝ እጅግ ደስ አለኝ:: ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በሁሉም ላይ ይወርዳልና መንፈሳዊ ጥማት በውስጥዎ ይደግ::

አንዳንድ ግለሰቦች ፓስተር ለይፉ በልሳን ለመሞላት እፈልጋለሁ ጸልይልኝ ይላሉ:: በልሳን አይደለም የምንሞላው ጌታ መንፈስ ቅዱስን ነው የሚያወርድብን:: የወረደብን መንፈስ "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት" ይባላል:: ሲመጣ ደግሞ ከአብ ዘንድ ስለ እኛ የምልጃ ጸሎት የሚያደርግበትን የራሱን ቋንቋ ይዞ ነው የሚመጣው:: ለመናገር የአንተን አፍ ይጠቀም እንጂ ቋንቋው ግን በውስጥህ በኃይል የገባው የመንፈስ ቅዱስ ነው:: ስለዚህ ልሳን ስጠኝ ወይም በልሳን ሙላኝ አይባልም:: ከልሳን ጋር ጨምሮ ሌሎችም ድንቅ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክቶች ይኖራሉ እነርሱንም በቃላት ባስቀማጣቸው:-

1) ልዩ የሆነ ክብርና አምልኮ ለጌታ ማቅረብ
2) የነፍሳት ፍቅርና የመመስከር ፍላጎት መጨመር
3) ቅዱሳንን መውደድ
4) የጸሎት ሕይወት እድገት
5) የእግዚአብሔር ቃል ረሃብ

6) የቅድስና ሕይወት ዕድገት
7) በሰይጣንና መናፍስቱ ላይ የተዋጊነት ባሕርይ መጨመር

ወገኖቼ መንፈስ ይሙላባችሁ:: ሰውና ሰይጣን በማይሰሙት በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ አዘውትራችሁ ጸልዩ:: ይህን የሚለማመድ ክርስቲያን ራሱን ያንጻል /1ቆሮ. 14:2፣ 39/:: በይሉኝታ ምክንያት ራሳችሁን በልሳን ከመናገር አትከልክሉ::

አንዳንድ ሰዎች የኔ ልሳን አንድ ቃል ብቻ ነች ሰይጣን ደግሞ ከሰው ኮርጆሽ ነው ይሰኛል ይላሉ:: አንድ ቃልም ይሁን አንድ ድምጽ ከመንፈስሽ ውስጥ የወጣ እስከ ሆነ ድረስ ጌታ ይሰማዋል:: ሁለተኛ ደግሞ መጠንቀቅ የሚስፈልገው ሰይጣንን በማናቸውም ሁኔታዎቻችን ላይ አማከሪ አለማድረግ ነው:: እርሱ ከሆነ ሳይጠራ ሹክ ማለት ልማዱ ነው:: እንዲያውም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ለሰይጣን ደምጽ ጆሮውን መዝጋት አለበት::

## 11.3 በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ

በመንፈስ ቅዱስ የተመላ ሰው በመንፈስ ቅዱስ የሚቀጣጠልን ሕይወት ይለማመዳል:: በፋንታው ግን ብዙዎች ድሮ ሕይወቴ ጥሩ ነበር አሁን ግን እንደ ድሮ አይደለሁም ምን ትመክረኛለህ ይላሉ:: የተሞላንበት መንፈስ ሁኔታችንን ወይም ስሜታችንን እያየ የሚ ለዋወጥ አይደለም:: በመንፈስ የሚቃጠል ሰው የጽድቅንና የቅድስናን ኑሮ ለመኖር መወሰን አለበት:: ለተወሰነው ውሳኔ ደግሞ መጨከን ያስፈልጋል:: ዘወትር ሕፃን መሆን እሽሩሩ መባል የለብንም:: በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ አለብን እንጂ::

ሰው በመንፈስ የሚቃጠል ሲሆን እግዚአብሔርን መጠማቱ እየጨመረ ይሄዳል:: ምክንያቱም የጌታን ክብር ያየ ሰው ክብሩን አይጠግብም:: ለዚህ ዓይነቱ መጠማት ሙሴ ጥሩ ምሳሌያችን ነው





/ዘጸ 33:17-23/:: በመንፈስ የሚቃጠል ሰው በራሱ ፈቃድ አይነዳም መንፈስ ይነዳዋል እንጂ:: ዳዊት የተቀባ ሰው ነበር፣ የጦር ስልቶችን ሁሉ ያውቃል፣ ግን ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ፈቃድ ይጠይቃል /1ሳሙ 30:8/::

በመንፈስ የሚቃጠል ሰው ያለ ማቋረጥ ይጸልያል:: የጠፉ ነፍሳት ስለሚያሳዝኑት ይመስክራል:: በመንፈስ ስትቃጠል አም ላክህ በታምራት ያስደንቅሃል:: በመንፈስ የሚቃጠል ሰው በአምላኩ ላይ አጥብቆ ይታመናል ጌታን በደስታ ያመልካል ሁኔታዎች ባይ ሳኩ እንኳ ያመሰግናል:: በመንፈስ የሚቃጠል ሰው መንፈሳዊ ነዳጁን ሁል ጊዜ ይሞላል:: የእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት የአንድ ጊዜ ልምምድ ብቻ አይደለም:: በመንፈስ ቅዱስ የሚቃጠል ሰው አሁንም ጌታ ሆይ አፍስስብኝ ይላል:: ዳዊት ሦስት ጊዜ ነው የተቀባው:: ቅባት አንዴ ብቻ ቢሆን ኖሮ ሳሙኤል የቀባውና መንፈስ ቅዱስ በኃይል የወረደበት ይበቃው ነበር /1ሳሙ. 16:13/:: በፋንታው ግን ኬብሮን ላይ ሊነግሥ ተቀባ (2ሳሙ. 2:4):: እንደገና በእስራኤል ሁሉ ላይ ሲያነግሡት ቀቡት (2ሳሙ. 5:3):: ሐዋርያት በድግግሞሽ መንፈስ ቅዱስ ሲያርፍባቸው ይስተዋላል:: በአጭሩ የእነርሱም ሦስት ጊዜ ተመዝግቦ እናነባለን::

ኤሎሂም መልካም ነው ስለሆነም ስንጠይቀው መንፈሱን በላያችን ያፈስዋል:: በምድጃ ውስጥ የሚነድን እሳት አመቺ ሁኔታ ከልፈጠርንለት በስተቀር እሳቱ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ለመዛመት ወይም ለመጥፋት ይዳረጋል:: እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም ማድረግ ያለብን አራት ነገሮች አሉ እነርሱም:-

- አንጨት በምድጃ ውስጥ ጨመር (ተሞላ)
- አመዱን ከሚነደው እሳት ላይ አራግፍ (ንስሐ ግባ)
- እንጨቱን ቆስቁሰው (ቃሉን ብላ)
- እፍ በል (ተንበርከክ)

የእግዚአብሔር ቃል *"መንፈስን አታጥፉ"* ይላል (1ተሰ. 5:19):: ለመሆኑ ሰው እንዴት የመንፈስ ቅዱስን እሳት ያጠፋል:: የመጀመሪያው ሁኔታ በግል ሕይወታችን የምንለማመደው ኃጢአት ነው መንፈስን የሚያጠፋው:: የተሰወረ ኃጢአት በሕይወትህ ካለ ቶሎ በንስሃ አስወግደው /1ዮሐ. 2:1/:፡

በሁለተኛ ደረጃ የማስቀምጠው በስደት ምክንያት፣ በይሉኝታ ምክንያት፣ ከማመቻመች የተነሳ፣ ወይም በዓለምና በሰይጣን ተጽእኖ ምክንያት የተሰጠህን ጸጋ አትቅበር ጢሞቴዎስ በውስጡ ያለውን እሳት ቀብሮ ነበር:: ጳውሎስ እጁን በመጫን እንዳነሳሳው ይስተዋላል /2ጢሞ. 1:6/::

የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከሚያዳፍን ስብከት፣ ትምህርት፣ ቤተ እምነቶች፣ ቤተ ክርስቲያን፣ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ጭምር ራስህን ጠብቅ:: በውስጥህ ያለውን እሳት ከሚያዳፍንና መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚበላ ማኅበራዊ ኑሮ ከመሰለ ግንኙነት ራስህን ጠብቅ:: ቀባሪ አታሳጣኝ ከተባለ የኅብረተ ሰብ ተጽእኖ ራስህን ጠብቅ:: መንፈሳዊ ሕይወትህ እየሞተ ወደ ፊት ሥጋህ ሲሞት የሚሞሽልህ ሙሾ፣ የሚደቃልህ ደረት የሚነበብልህ ዲስኩር የሚፈይድልህ ነገር የለም:: እህቱ መልእክቱ ለአንቺም ነውና ተጠንቀቂ!

ሌሎች እሳትን የሚያጠፉ ሁኔታዎች መንፈስ ቅዱስን መስደብ፣ መንፈስ ቅዱስን ማታለልና መንፈስ ቅዱስን መቃወም የመሳሰሉት ናቸው:: አንተ ግን ከእነዚህ ሁሉ ራስህን ጠብቅ:: እነዚህን ከሚያደርጉና የጸጋ ሥራን ከሚያላሉ ግለሰቦች ተለይ:: አንተም እነዚህን ሁኔታዎች ታደርግ ከሆነ ንስሃ ግባና ተመለስ::

በመንፈስ የሚቃጠል ሰው ሁል ጊዜ ለእሳት ይጮኻል:: የእሳቱ ነቢይ የተባለው ኤልያስ የዘወትር ጩኸቱ እሳት ነው::





ኤልያስ እሳት ባለ ቁጥር እሳት ይወርዳል:: ዝናብ ሲል ዝናብ ይዘንባል:: የኛንም መስዋዕት የሚበላ እሳትና ድርቀታችንን አስወግዶ የሚያረሰርሰን ዝናብ ያስፈልገናል:: ወገኖቼ እሳት! እሳት! እሳትህን ላክ! ብለን እንጩህ::

ወደ ጥንቱ የመንፈስ ቅዱስ አሰራር እንመለስ:: ጌታ ተስፋ እንደሰጠን ገና ይወርዳል:: አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ይለቀቃል:: የዳዊት ቅባት እየታደሰ እንደሄደ ጌታ የእኛንም ሕይወት በሪቫይቫል እሳት ያድሰዋል:: አሜን ጌታ ሆይ እሳትህን ላክልን!

## 11.4 መንፈስን አታጥፉ

እየነደደ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ እሳት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደረግንለት በስተቀር መጥፋቱ አይቀሬ ነው:: ይህ ማስጠንቀቂያ በጣም አስፈላጊ ነው:: ቃሉ በግሪክ ስቤኑሚ "Sbennumi" የሚል ሲሆን ትርጉሙ እሳትን ወይም እሳት ላይ የተጣደን ነገር ሙቀት እንዳያገኝ ማድረግ ወይም እሳቱን ጨርሶ እንዳይነድ ማድረግ ማለት ነው::[8] የመንፈስ ቅዱስን እሳት ማጥፋት ማለት ሪቫይቫልን ማቆም ማለት ነው:: ይህን ቅዱስ እሳት ማጥፋት ማለት ለቤዛ ቀን የታተሙበትን መንፈስ ማሳዘን ማለት ነው:: እንዲህ ያለው ድርጊት ደግሞ በሕይወት ላይ መፍረድ ማለት ነው:: ለመሆኑ የመንፈስ ቅዱስን እሳት እንዴት ነው የምናጠፋው? ጥቂት ነጥቦችን ከታች እንመልከት::

1) መንፈስ ቅዱስን በመሳደብ ማቴ.12:31
2) መንፈስ ቅዱስን በማታለል ሐ.ሥ. 5:3-9
3) መንፈስ ቅዱስን ማክፋፋት ዕብ. 10:29
4) መንፈስ ቅዱስን በመቃወም ሐ.ሥ. 7:51

[8] Vine's, 922.

5) ጸጋን በመቅበር/ ቸል ማለት 1ጢሞ. 4፡14፣ 2ጢሞ.1፡6-7
6) የሌሎችን ጸጋ በመተቸት 1ተሰ. 5፡20
7) የስህተት ትምህርትን መከተል 2ጢሞ. 2፡16-18

፣

ከእነዚህም ሌላ የቅዱሳንን ቅም በማጥፋት፣ስደትና መከራ ላይ በመጣልና በክፉ ወሬና አሉባልታ በሌሎች ውስጥ ያለውን እሳት ማጥፋት ይቻላል፡፡ ሰውን መፍራት ሌላው የመንፈስ እሳት የሚጠፋበት መንገድ ነው፡፡ ሰው ምን ይለኛል እየተባለ ሕይወትን ለቅዝቃዜና ለድንዛዜ መዳረግ ይቻላል፡፡ ቃሉ እንደሚለው በእር ግጥም ሰውን መፍራት ወጥመድን ያመጣል፡፡ ጢሞቴዎስን እን ላለን እንጂ ስንቶቻችን ጸጋችንን ጥለን የማሕበራዊ ኑሮ ላይ በማተ ኮር እንኖራለን? ብዙዎች ነቢያቶች የነበራችሁ፣ ሰባኪዎች የነበ ራችሁ፣ አጋንንትን ታወጡ የነበራችሁ፣ የነፍሳት ፍቅር ያቃጥ ላችሁ የነበረ ዛሬ የት ወድቃችኋል? መንፈስን አታጥፉ! ወገኖቼ እሳቱን እንደገና አቀጣጥሉ! ለመሆኑ እንዴት ነው እሳቱን እንደገና ማቀጣጠል የሚቻለው?

1) የተሰወረ ኃጢአት ካለ ተናዘዝ
2) የይቅርታ ሕይወት ተለማመድ
3) በትክክል ኑር/ ተራመድ
4) የሌሎችን ጸጋ አክብር
5) እሳት እሳት እያልክ ጨኽ
6) ትንቢትን አትናቅ
7) መንፈስ ቅዱስን አክብር



# 12

# የተቀባ ትውልድ ማፍራት

የቅባት አገልግሎት የሰይጣንን ሥራ በማፈራረሱ ምንም አማራጭ የማይገኝለት የጰራቅሊጦስ የጸጋ ሥራ ነው፡፡ የቅባት አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር ሕልውና ያመጣናል፡፡ የሰሎሞን መቅደስ ተሰርቶ ሲያልቅ ሌዋውያንና ካህናት ነጭ በፍታ ለብሰው እየዘመሩ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አመጡት፡፡ በወቅቱ አንድ አዲስ ሁኔታ ተከሰተ፡፡ እርሱም ቤቱን የክብር ደመና ሞላው /1ነገ. 8:10/፡፡ የብሉይ ኪዳን አገልግሎት የመለኮት ክብር እንዲገለጥ ካደረገ የአዲስ ኪዳን የጰራቅሊጦስ ክብር ደግሞ በመካከላችን ሊገለጥ ይገባል፡፡

የጌታ ቃል *"የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለም"* ይላል (1ቆሮ. 4:20)፡፡ ስለሆነም ጌታ ተተኪውን ትውልድ ያለ ኃይል አገልግሎት አይተወውም፡፡ የቅባት አገልግሎት የሚወረስ፣ ከአንዱ ወደ ሌላ የሚተላለፍ ስለመሆኑ በቃሉ ላይ እናነባለን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ተስፋ በተነገረበት ቃለ እግዚአብሔር ውስጥ፣ ወደ ልጆች፣ ዘርና ወደ ሌሎችም እንደሚተላለፍ ተጠቅሶ እናነባለን /ኢሳ. 44:3፣ ኢዩ. 2:28፣ ሐ.ሥ. 2:39/፡፡ ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ቅባት መሰጠት አንድ ትውልድ

ላይ የሚያቆም ሳይሆን ወደ መጪው ትውልድም ይተላለፋል ማለት ነው::

## 12.1 ተቀብሎ ማቀበል

ና

በሁሉ ነገር ምሳሌአችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ከአባቱ ቅባትን ተቀበለና ተወዳዳሪ የሌለው የኃይል አገልግሎትን አገለገለ:: ለሦስት ዓመት ተኩል ሲያስተምራቸው የነበሩት አስራ ሁለት ሐዋርያት ቅባትን ከእርሱ የወረሱ ናቸው:: ጌታም ከአባቱ ስለ ተቀበለው ሥልጣን ከነገራቸው በኋላ ታላቁን ተልእኮ በኃላፊነት ሲሰጣቸው ይስተዋላል /ማቴ. 28:19-20/:: በልምምድም ሲያሰለጥናቸው እርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ህመምተኞችንም እንዲፈውሱ የመንግሥትን ወንጌል እንዲሰብኩ ሥልጣን ሲሰጣቸው እናነባለን /ማቴ. 10:1/::

የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው ለድሆች ወንጌል እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል /ኢሳ. 61:1/ ያለው ጌታ ተቀብሎ ጸጋውን፣ ልምምዱን፣ ሥልጣኑን ለደቀመዛሙርቱ ሲያቀብል እናያለን:: እነርሱንም እንኳ ደቀመዛሙርት አድርጉ ሲል አስተላልፉ ማለቱ ነው:: ሕይወታችን በምድር ላይ ዘላለማዊ አይደለም:: ለዚህ ነው ለመጪው ትውልድ የቅባትን አገልግሎት ማቀበል ያለብን:: የተቀባው ጳውሎስ ለብዙ ረዳት ሐዋርያቱ የቅባት አገልግሎት አቀብሎ አልፏል:: በተለይም ጢሞቴዎስን እየነቀነቀ ነው በውስጡ የተዳፈነውን እሳት ያቀጣጠለው:: እርሱንም እንኳን ለሌሎች አቀብል ይለዋል:: እስቲ ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን አደራ ከታች ባለው ሰንጠረዥ እንመልከት /2ጢሞ. 2:2/::





| ትውልድ 1 | ትውልድ 2 | ትውልድ 3 | ትውልድ 4 |
|---|---|---|---|
| ጳውሎስ | ጢሞቴዎስ | የታመኑ ሰዎች | ሌሎች |

ሰንጠረዥ 3 - ለትውልድ ማስተላለፍ

ለምንድን ነው የሪቫይቫልና የመንፈስ ቅዱስ የኃይል አገልግሎት ከምዕራቡ አገር ሊጠፋ የቻለው? መልሱ በእኔ ግምት የቀድሞዎቹ የኃይል አገልጋዮች እሳቱን በውል ለሚቀጥለው ትውልድ ስላላቀበሉ ነው:: እኛም ይህ አደጋ እንዳይደርስብን፣ ተተኪውን ትውልድ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚሠራ በትምህርትም ሆነ በልምድ ማሳየት ይጠበቅብናል:: ይህን ሳያደርጉ ያለፉ አገልጋዮች ቅባታቸውን ይዘው በመሞታቸው ታሪክ ሲወቅሳቸው ይኖራል::

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለን የጠለቀ ግንኙነት የምንማረውና የምናስተላልፈውም ብዙ ልምምድ አለ:: ምናልባትም በሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የማይገኙ፣ መጻሕፍትም ያልተጻፈባቸው ልምምዶች ይኖራሉ ብዬ አምናለሁ:: የጸራቅሊጦስን የኃይል ድርጊቶች የምንማርበት አንዱ መድረክ የኃይል አገልጋዮች ካካበቱት የግል ልምምድ ነው:: ጌታም በምድር አገልግሎቱ ደቀ መዛሙርቱን ያስተምራቸው ነበር፣ እንዲያገለግሉ ይልካቸው ነበር፣ ተመልሰው ራፖር እንዲሰጡት ያደርግ ነበር:: ስለዚህ አባቶች ማቀበል ልጆች ደግሞ መቀበል አለባቸው:: ወገኖቼ የቅባትን አሠራር ዕውቀት በመቀባበል ወደ በለጠ ልምምዶች እንገባለን:: ስለሆነም ለተተኪው ትውልድ በማሳየት እናስተላልፈው፤ ተተኪው ትውልድ ደግሞ ለመማር ፈቃደኝነቱ ይኑራችሁ:: እናንተም የነገ አቀባዮች መሆናችሁን አትዘንጉ::

## 12.2 ተቀብለው ያቀበሉ

ሙሴ በዕድሜው መርዘም ምክንያት ተቀምጦ መጦር የነበረበት አረጋዊ ሰው ነበር። ጉልበትን የሚያድሰው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ዳሰሰውና ሕዝብን ከባርነት ቤት የሚያወጣ ታላቅ ተልእኮ ከአባቶቹ አምላክ ሊረከብ ቻለ። በቁጥቋጦው እሳት ቅባት ምክንያት ጌታ አርባ የአገልግሎት ዘመን አዘጋጀለት። ሙሴ በከፍተኛ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሆኖ ነው ኢያሱን ለቅባት አገልግሎት ያዘጋጅ የነበረው። ኢያሱ ጥሩ ተዋጊ መሆኑን ስለሚያውቅ ወደ ጦር ሜዳ በኃላፊነት ያሰልፈው ነበር።

አንድ ቀን ኤሎሂም *"መንፈስ ያለበትን ሰው የነዌ ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን ጫንበት"* ብሎ ተናገረው (ዘኍ. 27:18)። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር የሚለው በአንተ ውስጥ ያለውን ኃይል ወደ እያሱ አስተላልፍ ነው (impart)። በጌታ እይታ ያንን የተመረጠ ሕዝብ መምራትና የተስፋይቱን ምድር ማውረስ የሚችለው ኢያሱ ብቻ ነበር። ከዚህ ድርጊት የተነሳ የሆነውን ብናይ *"ሙሴም እጆቹን ስለጫነበት የነዌ ልጅ ኢያሱ የጥበብን መንፈስ ተሞላ"* (ዘዳ. 34:9)። ይህ የተላለፈ ቅባት ነበር ኢያሱን በድንቅና በታምራት አጅቦ የተስፋይቱን ምድር ለእስራኤላውያን እንዲያወርስ ያደረገው። የዘመኑ ሙሴ ሆይ እጆችህን በመጫን ልታስተላልፍ የምትችለውን ኃይል እስተውልና አስተላልፍ። የዘመኑ ኢያሱ ሆይ በአባትህ እጅ መጫን ወደ አንተ ሊያልፍ የሚችለውን ቅባትና በረከት አስተውል።

በመሰረቱ ሙሴ ቅባትን የሚያስተላልፍ ሰው ነበር። እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያ ተከትሎ በውስጡ ያለውን የቅባት አገልግሎት በሰባ ሽማግሌዎች ላይ አስተላልፏል /ዘኍ. 11:16-17፣ 24-30/። እንዲያውም ኤሎሂም መንፈሱን በሰው ሁሉ ላይ እንደሚያፈስስ ከኢዩኤል በፊት የተነበየው ሙሴ ነበር /ዘኍ. 11:29/።





ኤልያስ ቅባት ወደ ሌሎች በማስተላለፍ ሌላው ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ሰው ነበር። በመሰረቱ ኤልያስ በጌልጌላ፣ በቤቴልና በዮርዳኖስ የነቢያት ልጆች ትምህርት ቤቶች ነበሩት። የሚማሩትም ትንቢት መናገር፣ ራእይን ማየትና የኤሎሂምን ሃሳብ መረዳት ነበር። ስለ ኤልያስ በየከተማው የነበሩ ሃምሳ ሃምሳ ተማሪዎች ሁሉ በዚያን ዕለት እንደሚነጠቅ በመንፈስ ተረድተው ለኤልሳዕ ገልጠውለታል /2ነገ. 2:3፣5/። ኤልያስ በምትኩ ነቢይ እንዲሆን ኤልሳዕን በጌታ ምሪት እርሻው ድረስ በመሄድ መጎናጸፊያውን የጣለበት ቅባትን ለማስተላለፍ ነበር /1ነገ. 19:19-20/። በመጨረሻ በእሳት ሰረገላ ሲወሰድ የቅባት ኃይል የሚሠራበትን መጎናጸፊያውን ከሰማይ ወረወረለት።

የኤልያስ ቅባት በኤልሳዕ ላይ ማረፉን የዮርዳኖስ ወንዝ ትእዛዙን ሰምቶ በመከፈል አረጋገጠለት። የነቢያት ልጆችም የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ማረፉን ተረዱና ለነቢይ የሚገባውን የክብር ሰላምታ አቀረቡለት። የኤልሳዕ ቅባት እጅግ የሚያስደንቅ መሆኑን የእርሱን አገልግሎት ታሪክ ያዘለውን ሁለተኛ ነገሥት የመጀመሪያዎቹን አስራ ሁለት ምእራፎች ማንበብ ጠቃሚ ይሆናል። ኤልሳዕም ራሱ ቢሆን ሌሎችን ቀብቷል በተለይም እንደ ኢዩ ያለውን ታላቅ ሰው እንዲቀባና በኤልዛቤልና አክአብ ቤት የመንጥር ዘመቻ ላይ ትንቢትን የሚፈጽም ንጉሥ ያደረገው እርሱ ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ ቅባትን ወደ ሌሎች በማስተላለፍ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ አገልጋይ ነበር። ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ *"ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንድናካፍላችሁ ላያችሁ*

*እናፍቃለሁና"* ይላቸዋል (ሮሜ. 1፡11)። *መንፈሳዊ ስጦታ የሚያ* ካፍላቸው እነርሱ ዘንድ በመገኘት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በትንቢት የተነገረልህን ባንተ ያለውን ጸጋ ቸል አትበል ይለዋል /1ጢሞ. 4፡14/። ከንባቡ እንደምንረዳው ወጣቱ አገልጋይ ስጦታውን ቸል ያለ ይመስላል። ጳውሎስ በመቀጠል እጆቼን በመጫን ባንተ ያለውን ጸጋ አነሳሳለሁ በማለት ይቀሰቅሰዋል /2ጢሞ.1፡6/። ያለፈውንም ሲያሳስበው በትንቢት ስላንተ አስቀድሞ እንደ ተነገረልህ ይልና ያስታውሰዋል /1ጢሞ. 1፡18/። አያችሁ ጌታ በሕይወት ዘመናችን ሊጠቀምብን እንደሚፈልግ ተናግሮን ሊሆን ይችላል። ሁኔታውን ልንዘነጋ፣ ወይም በአለታዊ ኑሮችን በመጠመድ ምክንያት ቸል ልንል፣ ወይም በስደት ምክንያት ራስን ገለል ማድረግ ላይ ልንሆን እንችላለን። በዚህ ጊዜ ነው ቀስቃሽ የሚያስፈልገን። ጌታ ስለኛ የተናገረውን በእርግጥ ይፈጽማል። ዛሬ ጌታ የረሳህ የሚመስልህ ወንድሜ ሆይ ራእዩ ወደ ፍጻሜ ይመጣል የዘገየ ቢመስልህም እንኳ አይቆይም ንቃ። ጌታ ይጠራሃል!

ጌታ እስኪመጣ ድረስ ትውልድ ይመጣል ትውልድ ይሄዳልና ይህን የከበረ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ለመጪው ትውልድ ከአሠራሩ ጭምር ማውረስ ይገባናል። ተተኪ የቅባት አገልግሎት ትውልድም የቅባትን አገልግሎት መሻትና እንደ ኤልሳዕ ለመቀበል መጓጓት አማራጭ የሌለው እውነታ ነው። አሜን የተቀባ ትውልድ ይነሳ!

## 12.3 ጌታ እስኪመጣ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጰራቅሊጦስ መምጣት ለደቀ መዛሙርቱ ሲነግራቸው ስለምን እንደሚናገር መረዳት አልቻሉም ነበር /ዮሐ. 14፡16፣ 15፡26፣ 16፡7/። የመጀመሪያው አጽናኝ የሆነው ጌታ ኢየሱስ *"ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ወደ*





*እናንተ እመጣለሁ"* አላቸው (ዮሐ. 14፡18)። ዛሬ ጌታ በመንፈሱ አማካኝነት በውስጣችን ይኖራል። ለምንድነው በውስጣችን የሚ ኖረው? የማዳን ሥራውን ለመግለጥ፣ ፍቅሩንና ርኅራሄውን ለመስ ጠት፣ የሰዎችን ቀንበር ለመስበር በውስጣችን ይኖራል።

የኃይል አገልግሎት ሥራ መሥራቱን መቀጠል አለበት። ሃይማኖት አያስፈልገኝም በሚል በዚህ ዓለማዊ ትውልድ መካከል የቅባቱ ኃይል የካንሰር፣ የኤች አይቪን፣ የአጋንንትን፣ ቀንበር እየሰበረ ብዙዎችን ወደ መንግሥቱ መማረክ አለበት። ስለሆነም ጌታ ቀብቶ የሚጠቀምባቸውን ሰዎች ይፈልጋል። አንባቢ ሆይ! ከፍተኛ ጥሪ አለህ። ትፈለጋለህ! እንዲያውም ልንገርህ ለመቀባት ተጠርተሃል። ሃሌ ሉያ!

ሙሴ እንደተጠራ፣ ኢያሱ እንደተጠራ፣ ኤልሳዕ እንደተጠራ፣ ሰባው ሽማግሌዎች እንደተጠሩ፣ ሐዋርያት እንደተጠሩ፣ ጢሞ ቴዎስ እንደተጠራ፣ አንተም አንቺም ተጠርታችኋል። ሐዋርያው ጳሎስ እንዲህ ይላል *"በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፣ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው"* (2ቆሮ. 1፡21-22)። የቅባት አገልግሎት ጌታ እስኪመጣ ድረስ ይቀጥላል። በመጨረሻው ዘመን ላይ የጸጋ ሥራ እንደሚቀጥል ሐዋርያው ጳውሎስ በማስረገጥ ይነግረናል (1ቆሮ. 1፡7)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማሰርና ለመፍታት የሚችለውን ቁልፍ ሰጥቶን ነው የሄደው። ስለሆነም ያልተመቻመቸና የለየለት የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በትጋት እናቅርብ። ጌታ ሆይ እርዳን! አሜን!!

## 12.4 የሚደረጉ ጥንቃቄዎች

ማንኛውም አገልግሎት ብርቱ ጥንቃቄን ይጠይቃል። ሁሉን ነገር በሥርዓት ካልመራነው በስተቀር ሂደቱን መቆጣጠር አዳጋች

መሆኑ የማያጠራጥር ነው። የቅባት አገልግሎት ተተኪዎች ከዚህ የሚከተሰውን ጥንቃቄ እንድታደርጉ እመክራለሁ።

## 1) አትቸኩል

ችኮላ ጠቃሚ ከሚሆንበት ጊዜ ይልቅ ጎጂ የሚሆንበት ያመዝናል። በተለይም በሕይወቱ ውስጥ ጌታ ጥሪ ያኖረበት ሰው ራሱን ለመንፈሳዊ መሪው እያስገዛ ጌታ ሂድ ብሎ የሚያሰማራውን ቀን መጠበቅ አለበት እንጂ ጥሶ መሄድ የለበትም። የመጠራት ጊዜ እንዳለ ሁሉ ሂድ የሚባልበት ጊዜ ደግሞ አለ። ይህ መቼም የማይዋጥ ቢመስልም ኤሎሂም ግለ ሰቡን የሚባርከው በዚህ መንገድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ማቅረብ እችላለሁ።

ኢያሱ ጥሪ የነበረው ሰው ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም። በጦርነት ላይ ዋና ተዋጊና አዋጊ ሆኖ ያገለግል የነበረው ኢያሱ ነበር። እግዚአብሔር የሚገለጥበትን ድንኳን ይጠብቅ የነበረው ኢያሱ ነበር። ሙሴ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ወደ ተራራ ሲወጣ እስከተወሰነ ክልል ድረስ አብሮት የሚጓዘው ኢያሱ ነበር። በጉልበትም ሆነ በቁመና እንዲሁም በአነጋገር ስልትና በወጣትነት ከሙሴ መሻሉ የማያጠያይቅ ነበር።

ወጣቱ ኢያሱ ባማሩ ቃላት እስራኤላውያንን ተናግሮ ከዛሬ ጀምሮ እኔን ተከተሉ ሙሴ ስላረጀ ሊመራችሁ አይችልም ቢል ኖሮ የሚከተሉት ሰዎች አያጣም ነበር። ግን አልቸኮለም ጌታ በኃይል የሚያስነሳውን ጊዜ ይጠባበቅ ነበር። አንተም ቸኩለህ ራስህን ከመሾም ተቆጠብ። በዚህ መንገድ ሥልጣኑንም ሆነ ተከታዮችንም ማግኘት ትችላለህ። ግን ሂደቱ ፈር የለቀቀ በመሆኑ መንፈሳዊ በረከት አይገኝበትም።

ወገኖቼ ከኢያሱ ሕይወት በዚህ ነጥብ ላይ የምንማረው ትምህርት አለ። አንድ ጊዜ እንኳ በሥልጣን ሽኩቻ ውስጥ ገብቶ





ሕይወቱን አላመሰቃቀለም። ጌታ ከቀባህ ማንም ከአገልግሎት ሊያግድህ አይችልም። ስለሆነም በትክክለኛው ቀን መሰማራቱ ይመረጣል። ቸኩለህ በምትወስደው ርምጃ ብዙ የምትፈይደው ቁም ነገር የለም። የቅባት አገልግሎት ብርቱ ጥንቃቄን ስለሚጠይቅ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እየተስማሙ መጓዝ ይመረጣል።

ዳዊት የሥልጣን ጥማት ያልተጠናወተው ባለመቸኮልም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሌላው ሰው ነው። ዳዊት ንጉሥ ለመሆን መቀባቱ እውን ነው /1ሳሙ. 16:12-13/። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ርቆ ክፉ መንፈስ በሚያሰቃየው ወቅት ከስቃዩ ጸጥታን ያስገኝለት የነበረው ዳዊት ነበር። እንዲያውም ሳኦል ዳዊትን ስለወደደው ጋሻ ጃግሬው አደረገው። መሳርያ ታጥቆ የንጉሡን ሕይወት ለመጠበቅ ክቡር ዘበኛ የመሆን ዕድል ገጥሞት ነበር። ዳዊት እንደሚነግሥ ቢነገርለትም እንኳ ዙፋን ላይ በአቋራጭ ቂጥ ለማለት መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ሙከራ አላደረገም።

ዳዊት ሳኦልን ገድሎ ሥልጣን የሚጨብጥበት ሌላ አጋጣሚ አግኝቶ ነበር። ሳኦል ሠራዊት አሰልፎ ዳዊትን በሚያሳድድበት ወቅት እስከተኛበት ሥፍራ መጥቶ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚ አብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሳም በማለት የልብሱን ጫፍ ብቻ ቆርጦ ሸሸ /1ሳሙ. 24:4-19/። እግዚአብሔር የቀባውን ሰው ራሱ ቀቢው በቦታው ላይ ሲያስቀምጠውና ሲያነሳው ይሻላል። ዳዊት ግን ከሳኦል ሞት በኋላ ነገሠ፣ ለአርባ ዓመታትም መንግሥቱ ጸናለት። የሚቀባ፣ የሚሾምና የሚያሰማራ ራሱ ጌታ ስለሆነ፣ ለትክክለኛው ጊዜ ጌታን መጠበቅ በሰውም ሆነ በእግዚ አብሔር ዘንድ ያስከብራል። አገልግሎትም ስኬታማ የሚሆነው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ስለዚህ በታላቅ አደራ አትቸኩል እያልሁ እመክራለሁ። በችኮላ ውስጥ ሌሎችንም ወንድሞችና እህቶች ረግጦ በማለፍ

ጉዳት አምጥቶ በግል ሕይወትም ምሬት ውስጥ መግባት ይቻላል። የንጉሣችንን ሃሳብ አገልግሎ ለማለፍ ትክክለኛው መንገድ አለመቸኮል ነው።

ተቀብቶ የተጠራው ኤልሳዕም አልቸኮለም አንተም አት ቸኩል። ያንን ሁሉ ጥንድ በሬ ሊያስማራ የሚችል ሰፊ እርሻ ጥሎ የወጣው ተተኪው ትውልድ በኤልያስ እጅ ላይ ውኃ ሲጨምር፣ ሎሌ የሚያደርገውን ሁሉ እያደረገ ኤልያስን ሲያገለግል ኖረ። የሚያውቁት ሁሉ ቤተ ዘመዱም ጭምር የታለ ታዲያ ነቢይነቱ ብለው ሳያወሩበት አልቀሩም። ኤልሳዕ በልቡ ሰሌዳ ላይ መዝግቦ የሚጠባበቀው የጌታ ቀን አለ። ኤልያስም ከእርሱ ሳይ ወስድ የሚፈልገውን እንዲለምን ሲነገረው፣ ምንም ሳያመነታ በአንተ ላይ ያለው ቅባት በእኔ ላይ እጥፍ ሆኖ ይሰጠኝ ነበር። ይህን ጥያቄ ለስንት ጊዜ እንዳሰላሰለው ባይታወቅም በውስጡ መቆየቱ ይታመናል።

ኤልሳዕ ሰዓቱ ሲደርስ በእጥፍ ቅባት ተቀብቶ ግለሰቦችን፣ ቤተ ሰቦችን፣ ህብረተ ሰቦችን፣ ነገሥታትን፣ አገለገለ። ጦር ሳያስከትት የጠላትን ጦር ማረከ፣ በተፈጥሮ ሕጎች ላይ እንኳ ሥርዓታቸውን እየለወጠ ለሰዎች የሚጠቅሙ በርካታ ታምራቶችን አደረገ። ከአገሩ ድንበር አልፎ በመሄድ የነገሥታትን ሹም ሽር አወጀ፣ ሞትን በእምነት በመቃወም የሞተውን አስነሣ። ከሞተ በኂላም እንኳ አጽሙም የነካው ሙት ሰው ተቀስቅሶ ወደ ቤቱ ገስግሶ ገባ። አለመቸኮል ትክክለኛ የእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያስገባል። አንተም አትቸኩል ወዳጄ፣ ጌታ እጅህን ይዞ የልቡ ፈቃድ ውስጥ ያስገባሃል። ወደትክክለኛ የቅባት አገልግሎት ለመግባት ትክክለኛውን ወቅት ማግኘት አስፈላጊ ነው።





## 2) ነቢይን አታታልል

አጠገቡ ስትሆን እንደ አንተው ሰው ነው። እንደኔው ነው በምትለው ነቢይ ውስጥ ግን የመለኮት ቅባት ሲለቀቅ የማይታየውን ያያል፣ የማይደመጠውን ያዳምጣል፣ ከመናፍስት ዓለም ጋር ልዩ የሆነ ንክኪት እንዳለው ግልጽ የሚሆንበት ወቅት አለ። ሰው ነው ብለህ ሸውደህ ማምለጥ የምትችል አይምሰልህ። ለህሊናህም ቢሆን መልካም አይደለምና ነቢይን አታታልል። ወንድም ግያዝ ለቅባት አገልግሎት የሚዘጋጅ ሰው ነበር። እንዲያውም በነቢይነት የል ምምድ ትምህርት ቤት ውስጥ እየሰለጠነ ነበር ያለው።

ጄኔራል ንዕማን በተፈወሰበት ቀን የፈውሱን መገለጥ ከነቢዩ እየተቀበለ የሚነግረው ግያዝ ነበር። ግያዝ ነበር የሱነማዊቱ ሴት የልጅ በረከት ሲሰጣት በእርሷና በነቢዩ መካከል አፍ ሆኖ የተባለውን የሚያስተላልፈው። ግያዝ ነበር የሞተውን የሱነማዊቱን ልጅ ለመቀስቀስ የነቢዩን በትር ይዞ የሮጠውና ራሱ አጠገብ አድርጎ እንዲነሳ የጠበቀው። ግያዝን የመፋቅረ ንዋይ ፈተና ግብ ግብ በገ ጠመው በዚያች ቀውጢ ቀን ነበር የታሰበለትን የቅባት አገልግሎት እንዳይጨብጥ ዕገዳ የተጣለበት። ከንእማን ላይ ድርጎ ሲቀበል ነቢዩን ያታለለ መስለው እንጂ በመገለጥ ራእይ ኤልሳዕ ተመል ክቶት ነበር። ለትልቅ ሥፍራ የታጨው ምስኪን ሰው ለራሱም ሆነ ለዘሩ የሚሆን የለምጽን እርግማን ተቀብሎ ከአገልግሎት ቢሮው ተሰናብቶ ወጣ /2ነገ. 5፡20-27/። ነቢይን ማታለል እንዲህ ያለ ችግር ላይ ይጥላል።

ለቅባት አገልግሎት ተተኪዎች ባይሆኑም ነቢይን ያታለሉ ሰዎች ምንም መቅኖ የላቸውም። በድርጊታቸው ምክንያት ወይ ለራሳቸው ወይም ለሌሎች ሕይወት ጠንቅ የሆኑበት ጊዜ በጌታ ቃል ላይ ተመዝግቧል። የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ኢዮርብአም

ወንድ ልጁ ሲታመምበት ሚስቱን ተነሺና ማንነትሽን ሳታስታውቂ ልብስሽንም ሁሉ ለውጠሽ ትነግሣለህ ብሎ ወደ ነገረኝ ወደ ነቢዩ አኪያ ስጦታን ይዘሽ ሂጂ። በታመመው በልጃችን ላይ የሚሆነውን ይነግርሻል አላት። ሴቲቱም እንደተመከረችው ሆና መጣች። እንዲያውም ነቢዩ በእርጅና ምክንያቿ ዓይኖቹ ስለፈዘዙ አያይም ነበር። እግዚአብሔር ግን ለነቢዩ የኢዮርብአም ሚስት ስለ ልጇ ለመጠየቅ እንደምትመጣ ነገረውና እንደሚሞት ንገራት አለው። ሴቲቱም ገና ስትገባ አንቺ የኢዮርብአም ሚስት ስትሆኚ ለምን ራስሽን ሰውረሽ መጣሽ አላት። ወዲያውም ብርቱ ወሬ ለአንቺ አለኝ ሲል ልጇ እንደሚሞት ነገራት። ነቢዩ እንደተናገረው ገና ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጁ ሞተ /1ነገ. 14:1-18/።

ሐናንያና ሰጺራ ለሞት ቅጣት የተዳረጉት የጌታን ባሪያ ጴጥሮስን ስለዋሹ ነበር። በመሰረቱ ገንዘባቸውን ሁሉ አምጥቶ የማስረከብ ግዴታ አልነበረባቸውም። ይሁን እንጂ ሐዋርያውን ሸውዶ በማለፍ ቸሮች ናቸው ተብለን ትልቅ ስም እናተርፋለን ብለው ገመቱ። ሁሉን አዋቂ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ግን አጋለጣቸው። ወገኖቼ በተለይ በቅባት አገልግሎት ውስጥ ያለ ነቢይ በድንገት በእርሱ ላይ የሚለቀቀውን ቅባት ስለማናውቅ ጠንቀቅ ማለት ውብ ነው። ለቅባት አገልግሎት እየተዘጋጀህ ከሆንህ እነ ዚህን የጥንቃቄ ነጥቦች በልብህ ያዛቸው ይጠቅሙሃል።

### 3) ቅባትን አክብር

ጸራቅሊጦስ እንደወደደ ሰዎችን ለተለያየ ዓይነት አገልግሎት ይቀባል። እነዚያን መንፈስ ቅዱስ የቀባቸውን ሰዎች ማክበር ማለት የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ማክበር ማለት ነው። የኤልያስ መጎናጸፊያ ተረካቢ እሆናለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው ኤልያሴ ነው በሚለው ሰው ውስጥ ያለውን ቅባት ማክበር አለበት። ከዚህ ሰው ጥቅም አገኛለሁ በሚል ሃሳብ ብቻ ሳይሆን የጌታ እጅ በሕይወቱ የሚሠራን ሰው





የዕድሜና የፆታ ልዩነት ሳያደርግ በውስጡ ካለው ቅባት የተነሳ ብቻ ያን ሰው ወይም ሴት ማክበር አስፈላጊ ነው።

የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ስናከበር በግለ ሰቡ ውስጥ ያለው ኃይል ይለቀቅና የብዙዎች ቋጠሮ ይፈታል። አንድ ጊዜ በአገል ግሎት ላይ ሆኜ አጋንንትን ስገስጽ ብዙ እርኩሳን መናፍስት የነበሩባቸው ሰዎች እያስቀዘፋቸው ተዘርረው መሬት ላይ ወደቁ። ከወደቁት መሃል አንድ ረጅም ወፍራም ሴት በመናፍስት ኃይል ከመትንከባለልበት ሥፍራ ተነስታ ከስብሰባው መሃል ወጥታ ለማ ምለጥ ሮጠች። እኔም ሴሎቹን የወደቁትን ትቼ እርሷን እየ ተከተልሁ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውደቅ ስል፣ መጨረሻ ወንበር ላይ በትዝብት ተቀምጦ በሚመለከት ሰው ላይ ወድቃ ያም ሰው ከነወንበሩ ተገልብጦ መሬት ላይ ተንከባለለ።

የሁለቱንም ሰዎች መደምደሚያ ልጨርስላችሁና አጋንንት የነበረባትን ሴት መልሼ በማምጣት ከውስጧ ብዙ እርኩሳን መናፍስትን አስወጣሁ። ያም ሰው አብሮኝ ወደ ፊት በመምጣት ከወደቁት ውስጥ መናፍስትን አውጥቼ ከጨረስሁ በኋላ ለመናገር ፈቃድ እንድሰጠው ጠየቀኝ። እኔም ፈቅጄለት ሲመስክር በጊዜው የሚሠራውን ቅባት ልክ አይደለም፣ ይህ በአእምሮ ላይ የሚያ ደርጉት ጨዋታ ነው እያለ በመተቸት ላይ እንደነበረ እያነባ መስከረና ጌታን ተቀበለ። ዛሬ የቅባትን አገልግሎት የሚተቹ የማያምኑ ብቻ አይደሉም አማኞችም፣ ሽማግሌዎችና ፓስተሮችም አሉ። በበኩሴ ውሳኔዬ በተቺዎች ምክንያት ትጥቅ አልፈታም ነው። ሃሌ ሉያ!

የማስብና የመናገር ነፃነት ባለበት ዘመን ላይ የምንኖር አማኞች ለአእምሮአችን የፈለገውን እንዲያስብና የተሳሳተ ድርጊት

ውስጥ እንዲያስገባን መፍቀድ የለብንም። ቃለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል *"ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም"* (ማቴ. 12:31)። የማይገባችሁ አሠራር ቢኖር እንኳ ከመተቸት ይልቅ ጌታ ሆይ አባክህ ይህን ግለጥልኝ ብሎ መጸለይ ይመረጣል።

ይህን ምዕራፍ ከመዘጋቴ በፊት ጌታ በመንፈሱ አማካኝነት ያለውን ልገልጥላችሁ እወዳለሁ። ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች ልጆቼን እቀባለሁ። በሚመጡት ዘመናት አዳዲስ የተቀቡ ልጆቼ ይነሳሉ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ድንቅና ታምራትን የማደርግባቸው ዕቃዎቼ ይሆኑኛል። ይህን የምነገርህን ጻፍና አስተላልፍ፣ አስተምረውና ስበከውም እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም።

እንዲህ ይላል የታመነው አምላክ ከምድራችሁ በከፍተኛ ቅባት ወደ ጎረቤት አገሮች የሚላኩ፣ ወደ መካከለኛው ምስራቅም የሚላኩ፣ ወደር በሌለው ኃይል ድንጋይ የሆነውን የሕዝብ ልብ የሚፈረካክሱ ልጆቼ ይነሳሉ። ወደ ምድራችሁ ቱሪስቶች እጄ የሚሠራውን ድንቃ ድንቅ ለማየት ይጎርፋሉ ይላል እግዚአብሔር። በመጪው ዘመናት የማስነሳቸው ልጆቼ ተናገሩ ያልኋቸውን ቃሌን ይናገራሉ፣ የምገልጥላቸውንም ያስረዳሉ፣ በዚህም ምክንያት ምድራችሁ ትባረካለች፣ ተፈጥሮ እንኳ ትእዛዛችሁን ሰምቶ ይታዘዛል፤ ይሁን የምትሉትን የማደርግበት ቃላችሁን የማጸናበት ዘመን መጣላችሁ። ልጆቼ ሆይ! እንግዲህ ጸልዩና ጊዜውን አፋጥኑ ይላል ሁሉን ቻይ የሆነ እግዚአብሔር።

ወገኖቼ ጌታ ሚልዮን አገልጋዮችን እንኳ ቀብቶ ቢያስነሳ ደስታዬ ከፍ ያለ ነው። ያለውን ከፍተኛ ሥራ ሳስተውል ጌታ ሆይ





ልጆችህን እየቀባህ አስነሳ ማለት የዘወትር ጸሎቴ ነው። በሃገራችን ጌታ የለቀቀው ጸጋ እጅግ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም አፍሪካ ይጠብቀናል፣ እስያና አውሮፓ ይጠብቁናል፣ ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ይጠብቁናል፣ አውስትራልያና ደሴቶች ይጠብቁናል። እንዴት አድርገን ዓለምን እንደርሳለን አትበሉ። ድሮ ጌታ ከመካከላችሁ ወደ ውጭ አገር ሚሲዮናውያን አድርጌ የምልካችሁ አላችሁ ሲል፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነቢያትን ይህን ከየት አመጣኸው? ከስጋህ ነው እንጂ ምን ገንዘብኑሮን ነው ሚሽነሪ የምንልከው? እያሉ ይገስጹአቸው ነበር።

ዛሬ በውጭው ዓለም አገሬውን ወይም ተሰዶ የወጣውን ሕዝባችንን የሚያገለግሉ ብዙ የወንጌል ባሪያዎቸ አሉ። ስደት በሚልዮን ለሚቆጠር ሕዝባችን ወደ ውጭ አገር ለመፍለስ ምክንያት ሆኗል። የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ፣ በየትኛውም አገር ሁለት አማኝ የሆኑ አበሾች ከተገናኙ ቤተ ክርስቲያን ይመሰርታሉ። ይህ እንግዲህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ዓለም ሁሉ ይጠብቃቸኋል የተባለውም ትንቢት ይፈጸማል። *"ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"* (መዝ. 68:31) ለመቀባት ተጠርተሃል! እህቱ አንቺም ለመቀባት ተጠርተሽል! ለከፍተኛ የኃይል አገልግሎት ተዘጋጁ!

# መደምደሚያ

እዚህ ገጽ ላይ ከደረሱ ጰራቅሊጦስን አንብበው ጨርሰዋል ማለት ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ መረዳትን ለማግኘት ደጋግሞ ማንበቡ ጠቃሚ ይሆናል። ጰራቅሊጦስን ለመድረስ የበቃሁት የረጅም ጊዜ ልምምዴን ከቃሉ ጋር በማገናዘብ ነው። በግል ሕይወቴ ውስጥ መንፈሳዊ ርካታ በማጣት ያሳለፍሁትን የምድረ በዳ ሕይወት በመጽሐፉ ውስጥ ጠቅሻለሁ። አንድ ጊዜ ጰራቅሊጦስ ውስጤ ከገባ በኋላ ግን ወይ ንቅንቅ ወይ ፍንክች። እርስዎም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወትን ይለማመዱ በድል ለመኖርም ሆነ ለኃይል አገልግሎት መንፈሳዊ ጉልበት ያገኛሉ።

መንፈስ ቅዱስን የምንቀበለው በእምነት ነው። አንድ ሕፃን ልጅ ወላጆቹን ዳቦ የሚለምነው ይሰጡኛል ብሎ አምኖ ነው። ወላጆቹም ልጃቸው የጠየቀውን ይሰጡታል። ልብስ ግዙልኝ ቢላቸው ደግሞ ልጁን ለማስደሰት የጠየቀውን ከማድረግ አይመለሱም። ሰው ይህን ማድረግ ከቻለ አባታችን የሆነው እግዚአብሔር ደግሞ መንፈስ ቅዱስን አትረፍርፎ ያፈስስልናል። ጌታ ሲያስተምር *"እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" አለ (ሉቃ.11:13)።* አንዳንድ ግለሰቦች ስለሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እውነት መሆን ይጠራጠራሉ። አባታችን ክፉ ነገር አይሰጠንም የሚሰጠን ጰራቅሊጦስን ነው።

ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኋላ የሚከሰተው ተቀብቶ ማገልገል ሲሆን የቅባት አገልግሎት ምንጩ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። ጌታ ጰራቅሊጦስን የላከልዎ እርስዎን ጠቃሚ ዕቃ አድርጎ ሊጠቀምብዎት መሆኑ አያጠራጥርም። ስለሆነም ወደሚቀጥለው መንፈሳዊ ደረጃ ለማለፍ ራስዎን ያዘጋጁ። ጌታ ራሱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ መልክ ከወረደበት በኋላ ነበር የቅባት አገልግሎት የጀመረው። ለዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የተለየ መንገድ የለውም። የኃይል አገልግሎትን እንድናገለግል አገዛ ሊሰጠን ጰራቅሊጦስ መጥቷል!

ጌታ በሰጠኝ ጸጋ አገልግሎቴ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ የተመረኮዘ ነው። ወገኖቼ ወደ ጌታ ኪማቀርበው ዕለታዊ ጸሎት አንዱ "ጌታ ሆይ ከዚህ ያነሰ ወንጌል በሰበክሁ ቀን አባክህ ወደ ቤቴ ውሰደኝ" ማለት እንደሆነ በሃቅ ለገልጽላችሁ እወዳለሁ። የጰራቅሊጦስን የኃይል አገልግሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብንቀንሰው መልእክታችን ጉልበት ያጣል፣ የሰዎች የሕይወት ቋጠሮ አይፈታም፣ የተሰጠን መለኮታዊ ሥልጣን ሥራ ላይ አልዋለም ማለት ነው። ዲስኩሩንማ ማንም ይደሰኩረዋል በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ግን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መስጠት አለበት። እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ኃይልን በመግለጥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማገልገል አማራጭ የሌለው እውነታ ነው /ሮሜ. 15፡18-19/።

የጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ድንቅና ታምራትን ያካተተ እንደነበረ በመጽሐፉ አካል ላይ በሰፊው ተተንትኗል። ፈለጉን የተከተሉ ሐዋርያትም በጰራቅሊጦስ እየተደገፉ የጨለማውን ሥራ ገረሰሱና አለፉ፤ በሽተኞችን ፈወሱ፤ ሙታንንም እስከማስነሳት ድረስ የተቃና የወንጌል አገልግሎት ሰጥተው አለፉ። የስይጣንን





ውሸት እምቢ በማለት ራስን ለቅባት አገልግሎት ማዘጋጀት ጥበበኛነት ነው። የጰራቅሊጦስ ሥራ የማይዋጥላቸው ክርስቲያኖች እንደሚያስቡት የኃይል አገልግሎት ከሐዋርያት ጋር ሞቶ አልቀረም። በሌላ በኩል ደግሞ የሐዋርያነት ምልክት ሳይታይ ራሳቸውን ሐዋርያ ብለው የሚጠሩ አሉ። ኃይሉ በውስጣችን ሳይገለጥ ሐዋርያና ነቢይ መባልም ጥቅም የለውም። እንዲህ የሚለው ቃል የታመነ ነው፣ *"ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው"* (ዕብ. 13፡8)። ዛሬም ጌታ ውጤት የሚታይበት የኃይል አገልግሎት ይሰጣል!

እርግጥ ነው መንፈስ ቅዱስ በምድራችን ከፈሰሰ ወዲህ ትውልድ ተለውጧል። አዲስ አመለካከት፣ አዲስ አሠራር፣ አዳዲስ ዝማሬና ሙዚቃ ሌሎችም ልዩነቶች አሉ። የአሠራር ልዩነት ይኑር እንጂ ወገኖቼ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አልተለወጠም፤ ቃሉም አልተለወጠም፤ መንፈሱም አልተለወጠም። የኢያሱ አሠራር ከሙሴ የተለየ ነበር። ይሁን እንጂ የሁለቱም አገልግሎት ነፃ የሚያወጣና የሚያወርስ ነበር። ሙሴ ውኃውን በበትሩ መታው ኢያሱ ግን ካህናቱን ታቦቱን ተሸክመው በውኃ ውስጥ እንዲቆሙ አዘዘ። የሁለቱም የአደራረግ ውጤት ማሻገርና ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ነበር። አዲሱ ክርስቲያን ትውልድም በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ያስፈልገዋል። ቀንበርን የሚሰብረው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነው!

መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቂ ትምህርት አግኝተዋል ብዬ አምናለሁ። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት እያደረጉ ለመኖር እርስዎ ለራስዎ ይወስኑ። መንፈስ ቅዱስ እንዲጠቀምብዎ ከፈለጉ ጉልበትዎን ለጸሎት፣ ሕይወትዎን ለቅድስና፣ ፈቃድዎን ለእግዚአብሔር፤ እግርዎን ለመልካም ዜና፣

ያስረክቡና መልካሙን ሩጫ ይሩጡ። በቀኑ መጨረሻ ላይ ድሉ የእርስዎ ይሆንና *"መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"* ይባላሉ (ማቴ. 25፡21) እያልሁ አሳስብዎታለሁ። በሚቀጥለው መጽሐፌ እስከምንገናኝ በሰላም ይሁኑ!

***ሰይፉ ከበደ***
*ዲቨይን ፓወር ሚኒስትሪ*
*መስራች፣ ፕሬዝደንትና ፓስተር*



## ዋቢ መጻሕፍት
## Selected Reading


- Bennett, Dennis & Rita, The Holy Spirit And You. South Plainfield, New Jersey: Bridge Publishing Inc., 1971.
- Bickersteth, Edward Henry, The Holy Spirit. Grand Rapids, Michigan: Kregel Publications, 1979.
- Duffield, Guy P. & Van Cleave, Mathaniel, M. Foundation Of Pentecostal Theology. Los Angeles, CA: L.I.F.E. Bible College, 1991.
- Gee, Donald, Pentecostal Experience. Springfield, Missouri: Gospel Publishing House, 1993.
- Stamps, Donald C., The Full Life Study Bible N.I.V. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House, 1984.
- Sumrall, Lester, The Gifts & Ministries of the Holy Spirit. Tulsa, Oklohoma: Harrison House, 1982.
- Towns, Elmer L., The name of the Holy Spirit. Ventura, CA: Rega Books, 1994.
- Vin's, Expository Dictionary Of New Testament. Lynhburg , VA: The Old Time Gospel Houx, 1952.
- Wesley Duewel L., Ableze For God. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publisher House, 1989
- Young's, Analytical Concordance to the Bible. Grand Rapids, Michigan: WME Erdmans Publishing Co, 1975.

## ደራሲው ከዚህ ቀደም የጻፏቸው መጻሕፍት

1. ተአምራት
2. ሰይጣን ሲጋለጥ
3. የፈውስ ኪዳን

## ጥያቄ ቢኖርዎት

የጸሎት፤ ምክር፤ መጽሐፍ ለማዘዝ ወይም ለማናቸውም ጉዳይ አድራሻችን ከዚህ በታች የተመለከተው ነው።


**Our Address:**

**Seifu Kebede**
**Tsigiewengel Tekleab**

**DIVINE POWER EVANGELISTIC MINISTRIES**
21152 E. Greenwood Pl., Aurora, CO 80013
Tel. (303) 693- 1241 •Fax (720) 222-1538
E-Mail: divinepower94@yahoo.com
www.divinepoweronline.com